# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የድኅረ - ምረቃ መርሃ - ግብር

# በርቱሣ፤ ባህላዊ የግጭት አፈታት በሸኮ ብሔረሰብ

በ

መንግስቱ ፍስሐ አበበ

ነሐሴ 1999 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረ-ምረቃ መርሃ-ግብር

# በርቱሜ፣ ባህላዊ የግጭት አፈታት በሽኮ ብሔረሰብ

በ

መንግሥቱ ፍሰሐ አበበ

ነሐሴ 1999 ዓ.ም
አዲስ አበባ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

# በርቱማ፤ ባህላዊ የግጭት አፈታት በሸኮ ብሔረሰብ

በ


## መንግሥቱ ፍሰሐ አበበ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የድህረ ምረቃ ትምህርት መርሃ ግብር

ስነ-ትምህርት ኮሌጅ

የሕብረ ባህልና ልሳነ-ብዙ ትምህርት


ለኤም.ኤ.ዲ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ፅሑፍ


ነሐሴ 1999 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
# የድህረ-ምረቃ ትምህርት መርሃ-ግብር
# የሕብረ ባህልና ልሳነ ብዙ ትምህርት

## በርቱማ፤ ባህላዊ የግጭት አፈታት በሸኮ ብሔረሰብ

በ

መንግሥቱ ፍስሐ አበበ

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ | ፊርማ
--- | ---
የትምህርት ክፍሉ ሊቀመንበር | 
አማካሪ | 
ፈታኝ (የውስጥ) | 
ፈታኝ (የውጭ) | 

## ማውጫ


ገጽ

መታሰቢያ ........................................ I

ምስጋና ........................................ II

አጠቃሎ ........................................ III

ሙዳየ ቃላት ........................................ IV

**1.መግቢያ ........................................ 1**

1.1 የጥናቱ ዓላማ ........................................ 3

1.2 የጥናቱ አስፈላጊነት ........................................ 3

1.3 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ........................................ 4

1.4 የጥናቱ ዘዴ ........................................ 6

1.5 የጥናቱ ወሰን ........................................ 6

1.6 በጥናቱ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች ........................................ 7

1.6.1. በጥናቱ ሂደት ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች ........................................ 7

16.2. የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች ........................................ 7

**2. የሸኮ ብሔረሰብ ማህበረ-ባህላዊ ዳራ ........................................ 9**

2.1 ስነ-ምህዳራዊ ገፅታ ........................................ 9

2.2 ማህበራዊ እኮኖሚያዊ ህይወት ........................................ 1

2.2.1 እኮኖሚያዊ ህይወት ........................................ 1

2.2.2 ማህበራዊ መዋቅር ........................................ 12

2.3 ቋንቋና እምነት ........................................ 19

2.3.1 ቋንቋ ........................................ 19

2.3.2 እምነት ........................................ 19

2.4 የሸኮ ብሔረሰብ ባህላዊ ተቋም አወቃቀር ........................................ 20

2.4.1. ኮይናብ ........................................ 2

2.4.2 ቡርጃብ ........................................ 22

2.4.3. ኢያዝ(የጎግ መሪዎች) ........................................ 2

2.4.4. ቃልቻ ........................................ 2

3. ከሰማ ድርሳናት ........................................ 25

3.1 የግጭት ብያኔ ........................................ 25

3.2 የግጭት ትወራዊ ቅኝት ........................................ 25

3.3 የግጭት መንስኤዎች ........................................ 26

3.3.1 የሀብት ክፍፍል ........................................ 26

3.3.2 የፍላጎት አለመጣጣም ........................................ 27

3.3.3. የእሴቶች ግጭት ........................................ 27

3.4 የግጭት አፈታት ዘዴዎች ........................................ 28

3.4.1 በዓለም አቀፍ ........................................ 28

3.4.2 በአፍሪካ ........................................ 30

3.4.3 በኢትዮጵያ ........................................ 33

4. በርቁማ፣ ባህላዊ የግጭት አፈታት በሸኮ ብሔረሰብ ........................................ 40

4.1 የሸኮ ብሔረሰብ የአስተዳደርና የፍትህ ሥርዓት ........................................ 40

4.2 የግጭት አይነቶችና የአፈታት ሥርዓት ........................................ 42

4.2.1 የነፍስ ግድያ ........................................ 42

4.2.2 የጎሣዎች ግጭትና አፈታቱ ........................................ 56

4.2.3 ግሽ/ጠለፋ/ ........................................ 61

4.2.4 የባልና ሚስት ግጭት አፈታት ........................................ 66

4.2.5 በስርቆት የሚፈጠር ግጭት ........................................ 70

5. የበርቁማ ባህላዊ የግጭት አፈታት ፋይዳዎች ........................................ 75

5.1 ማጠቃለያ ........................................ 77

5.2 የመፍትሔ አቅጣጫዎች/ይሁንታዎች/ ........................................ 79

ዋቢ መጻሕፍት ........................................ 80

አባሪዎች




ምንጭ፡- የኪ ወረዳ ግብርናና
ገጠር ልማት ጽ/ቤት

# መታሰቢያ

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ በ 1992 ዓ.ም በያሬና ግንባር በለጋ ዕድሜው ለተቀጨው ወንድሜ ለአፈጋው ፍሥሐ፣ በኑሮ ውጣ ውረድ ሲንከራተት በጅምር ለቀረው ወንድሜ ለኮስትር ፍስሐ፣ እንዲሁም የትምህርት ጥማቸውን ሳይወጡ እልህ አርግዘው በአጭር ለቀሩት ጓደኞቼ ለከፍያለው ሰብስብ አበበ፣ ለተስፋዬ አያሌው ወርቁና ለስለሺ ጌታሁን ወሌ መታሰቢያ ይሁንልኝ።

# ምስጋና

ጥናታዊ ጽሑፉ ተስተካክሎ አሁን ላለበት ደረጃ እንዲደርስ ውድ ጊዜያቸውን መስዋዕት በማድረግ ጠቃሚና ሙያዊ ሀሳቦችን ለለገሱኝ አማካሪዬ ዶክተር ጌታቸው ሳህለ ማሪያም ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡

የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ድህረ-ምረቃ መርሃ-ግብር ለጥናቱ የሚያስፈልገውን ወጪ ለመሸፈን የገንዘብ ድጋፍ ስላደረገልኝ እንዲሁም የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለጥናቱ የሚያስፈልጉትን መረጃዎች ለመሰብሰብ የትብብር ደብዳቤ በመፃፍ ስለተባበረኝ አመሰግናለሁ፡፡

በመረጃ አሰባሰብ ሂደት ለተባበሩኝ ለየኪ ወረዳ ም/ቤት፣ ለየኪ ወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት፣ ለመረጃ አቀባዮቹ በሙሉ፣ በተለይም ደግሞ ሀብታሙ ስጠኝ፣ ሻሻ ወሽከሬ፣ ከርከስ ኡፋ፣ ካማ ከርሽን፣ ሽሙፈጂ፣ ኡርማ ዚቲ፣ ደሣለኝ ሞቺ፣ ፈትሻ ሾሻ፣ አባሸዋ ቆርጫ፣ ፀጋዬ አሊ፣ መንግሥቱ አሊና በሽሻ ቀበሌ ለጉደር አካባቢ ነዋሪዎች ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ካሣሁን አበበ ሽፋው፣ እሸቱ አደም በለጠ፣ ተሾመ ኃይሌ መሉ፣ ደስታ ዳሪቶ፣ ትንደድ ገሠሠ ካማ፣ ምህረቱ ምትኩ፣ አቡሌ ታደሰና መዓዛ አሊ በሞራል፣ በገንዘብና በማቴሪያል ከፍተኛ እገዛ ስላደረጉልኝ ለእነሱ ያለኝ ከበሬታና ምስጋና ከፍ ያለ ነው፡፡

ከትምህርት ጅማሮ እስከ ፍፃሜው ከጎኔ ሳይለዩ አይዞህ በርታ በማለት ቤተሰባዊ ድጋፋቸው ያልተለየኝ ትዕግስት አሊ፣ አማኑኤል መንግሥቱ፣ አዜብ መንግስቱ፣ እታገኝ በውዴና የሚያምረው ጆርጊን በእጅጉ አመሰግናለሁ፡፡

ይህንን ጥናት በኮምፒዩተር በመፃፍ ለተባበረችኝ አለም ዳባ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

# አጠቃሎ / Abstract/


ይህ ጥናት የሸኮ ብሔረሰብ በርቱማ /ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓትን/ አጠቃላይ ሂደት በመግለጽ ላይ ያተኮረ ነው። በሸኮ ብሔረሰብ ከቀላል ግለሰባዊ ፀቦች አንስቶ እስከ ከባድ የነፍስ ግድያ የሚዘልቁ ቡድናዊ ግጭቶች ይከሰታሉ። ለግጭቶቹ መፈጠር ዋና ምክንያት የሚሆኑት ከሴት፣ከመሬት፣ከስርቆትና ከትሣዎች አለመግባባት ጋር የተያያዙ ናቸው። ጥናቱ ገላጭና የይዘት ትንተና ስልትን የተከተለ ነው።

በርቱማ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ግጭትን ለማስወገድ የሚጠቀመው ስልት ማስታረቅን ነው። የእርቅ ሥነ-ሥርዓቱን የሚያስፈፅሙት የጎሣ መሪዎች፣ቡርጃብና የአካባቢ ታዋቂ ሽማግሌዎች ናቸው። እነዚህ አካላት በግጭት ውስጥ የገቡትን ግለሰቦች ወይም ቡድኖች በማቀራረብ አጥፊው ተቀጥቶ ተበዳዩ እንዲካስ በማድረግ በግጭቱ ምክንያት የተቋረጠው ግንኙነት ታድሶ ኑሯቸውን በሰላማዊ መንገድ አጠናክረው እንዲቀጥሉ ለማድረግ የሚችሉ መሆናቸውን ጥናቱ ያሳያል።

ከመደበኛ የህግ ሥርዓት ይልቅ በባህላዊ መንገድ ግጭትን የሚያስወግዱት የሸኮ ብሔረሰቦች ፍትህ ፍለጋ ከአካባቢያቸው ርቀው አይሄዱም። በዚህም ምክንያት የሰው ጉልበት፣ የጊዜና የገንዘብ ብክነት አይገጥማቸውም። ማህበረሰቡ ለጎሣ መሪዎች፣ ለቡርጃብና ለአገር ሽማግሌዎች ትልቅ ክብር ይሰጣል። ምክርና ተግሳጻቸውን ይቀበላል። በእርቅ ስነ-ስርዓት ወቅት የሚሰጡትን ውሳኔ ተቀብሎ ተግባራዊ እንደሚያደርግ ጥናቱ ያመለክታል።

በሸኮ ብሔረሰብ በበርቱማ ባህላዊ የግጭት አፈታት የሚቃለሉ ግጭቶች በርካታ ቢሆኑም ጥናቱ በነፍስ ግድያ፣በጠለፋ፣በባልና ሚስት መካከል፣ በሀብት ስርቆትና በጎሣና በጎሣ መካከል በሚፈጠሩ አለመግባባቶች የሚከሰቱ ግጭቶችንና የእርቅ ሥርዓቶች ላይ ያተኮረ ነው። በእነዚህ ግጭቶች ላይ በሚፈፀሙ የእርቅ ስነ-ስርዓቶች ላይ የሚደረጉ የካሳ ክፍያዎች በአጥፊው ላይ ብዙ ጫና እንደሚያመጡ ጥናቱ ያመለክታል።

የሚፈጠሩ ግጭቶችን ለመፍታት በሸኮ ብሔረሰብ የተቋቋሙት ባህላዊ የግጭት ማስወገጃ ተቋማት አደረጃጀት የሚከተሉት ስርዓትና ደንብ እየተጠና በመንግሥትም ሆነ በፖሊሲ አውጪዎች ዕውቅና ቢሰጠው ጠቃሚ እንደሆነ፣ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት ከቀበሌ እስከ ክልል ባለው የመንግሥት አደረጃጀት ተዋቅረው ከዘመናዊ ህግ ስርዓት ጋር በጥምረት ቢሰሩ እንደሚጠቅም፣ ባህላዊ እሴቶች የማህበረሰቡን አባላት ተስማምተውና ተከባብረው በሰላም እንዲኖሩ ከማድረጋቸውም ሌላ ለአካባቢው ልማት አስተዳደርና ፀጥታ መከበር ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳላቸው በማሳየት የሚጠናከሩበት መንገድ መፈለግ እንዳለበት የሚጠቁም የመፍትሔ ሃሳብ ቀርቧል።

# ሙዳየ ቃላት

| ሸኮኛ | አማርኛ |
|---|---|
| 1. ወማባብ | ንጉሥ |
| 2. ኢያቡ | የጎሣ መሪ |
| 3. ፍቾቃ | ጠንቋይ፣ ቃልቻ፣ |
| 4. ክበሲጓታ | ደጅ ቀዬ |
| 5. ገሽ | ጠለፋ |
| 6. ይኑ | አንጀት |
| 7. ጌብሁ | በርደ |
| 8. ደብም | ድብደባ፣አካል ላይ ጉዳት ማድረስ |
| 9. ሾቡደብም | የከረረ ጠብ፣ የነብስ ግድያ የሚፈፀምበት |
| 10. ቡሩ | እርግማን፣ የጎሣ መሪ፣ ቡርጃብና ያገር ሽማግሌ ከህዝብ ጋር ተሰብስበው የሚያከናውኑት ውግዘት |
| 11. ቡርቱማ | እርቅ፣ የተጣላን ማስታረቅ |
| 12. ኪጃ | ከቦቆሎ እሸት የሚዘጋጅ ባህላዊ ምግብ |
| 13. ቀርደ | ቀዝቃዛ ተክል እንደድ መሰል ቅጠሉ ደንዳና ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ውስጥ የሚበቅል |
| 14. እዐ | ዘምባባ መሰል ተክል ሰርጢ (ትልቁ) |
| 15. ባበ | ሽማግሌ፣ በዕድሜ የገፉ አዛውንቶች |
| 16. ቡጫ | ዘለፋና ስድብ፣ዛቻ፣ ማስፈራራት |
| 17. ቶሪ | እግር ላይ የሚደረግ ቃጭል |
| 18. ሸንን | ክራር |
| 19. ማሪ | ጨሌ |
| 20. ቱርቡ | ክበሮ |
| 21. ጥካ | ጎደሬ ሥሩ ለምግብነት የሚያገለግል |
| 22. ኮቺ | የሀረግ ስር የመሰለ ለምግብነት የሚያገለግል |
| 23. እማ | የአህያ እግር የመሰለ ለምግብነት የሚያገለግል በሀረግ ላይ የሚያፈራ |
| 24. ሸኮንታ | ነማ |

25. ቡርጃብ — የአስታራቂ ዘር፣በሽኮ ብሔረሰብ ዕርቅ ሲፈፀም መሃላን የሚያስፈፅም፣ የእርቅ ማስፈፀሚያ ቁሳቁሶችን በመጠቀም ባህላዊ ህጉ በሚፈቅደው መሠረት በተዋናይነት የሚያስፈፅም።

26. ኮይናብ — የንጉሥ ዘር፣ የብሔረሰቡ ቁንጮ የበላይ

27. ቢያቅን — ጦር

28. ጊያሱ — ጋሻ

29. ጪጊሞ — ከቡና ቅጠል የሚዘጋጅ ባህላዊ መጠጥ

30. ፈሩ — ከቀንድ የተሠራ መጠጫ /ባላባቶችና ትልልቅ ሰዎች የሚጠቀሙበት

31. ተካ — ጠጅ

32. ጠሩ — እንጀራ

33. (ኮና) ኖና — ወተ /የተቀመመ/

34. ባዣ — ህብረት አንድነት

35. ጊኑ — ጪጊሞ ከቡና ቅጠል የሚዘጋጅ መጠጥ

36. ፈረ — መስኮት

37. ፈንሱጊኒ — ከቅል የሚሰራ ሹል ነገር ሆኖ ሰፊና ቀዳዳ ያለው

38. ፈቲ — ፋንፋ ቀሽንት አንድ ቀዳዳ ያለው

39. ቡዊ — የመዚቀ መግረያ ከፊቲ ጋር አብሮ የሚቀርብ

40. ኢሙ — ቀጭንና ጠንካራ ስርጢ ስውቃቢ ቦታ የሚዘጋጅበት

41. ዘርጳቡይ — ነጭ ድንቢጥ ወፍ

42. ካምዱ — ሥራያ ያልጀመረ ወይፈን

43. ቡጪጊያብ — ጠበኛ

44. ሹተማ — ከዘመዱ ጋር ግብረስጋ ግንኙነት የፈፀመና ልጅ የወለደ

45. ጋሞ — የታችኛው ጥርስ ሳይበቅል የላይኛው ጥርስ ተድሞ የበቀለበት ህፃን

46. ሸክን — የጠር አበባ ሳታይ የወለደች ሴት

47. እንቾብ — በቤተሰብ ቁጥጥር ሥር እያለች ባል ሳታገባ የወለደች ልጅ/ሴት/

48. ኮብም — ጫካ

49. ቦርዶ — ከጤፍና ብቅል በማቀላቀል የሚዘጋጅ ጠላ

# 1. መግቢያ

የአፍሪካ ህዝቦች በራሳቸው ባህላዊ የአስተዳደር ተቋማት፣ ሥርዓቶችና ደንቦች አማካይነት በመካከላቸው የሚከሰቱትን ግጭቶች በማቃለል ዘላቂ ሰላምን ያሰፍናሉ፡፡ ኑሮአቸውን ያለስጋት ይመራሉ፡፡ ዕድገታቸውን ያፋጥናሉ፡፡ በኢትዮጵያም ውስጥ የሚገኙ ልዩ ልዩ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ባቋቋሟቸው ባህላዊ የአስተዳደርና የፍትህ ተቋማት ደንቦችና ሥርዓቶች እየተጠቀሙ ሰላምን ያረጋግጣሉ፡፡ ዘላቂና አስተማማኝ ልማትን ለማምጣት ይጥራሉ፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች ከዕለታዊ ጠብ እስከ ነፍስ ግድያ የሚዘልቁና በቤተሰብ፣ በተቋም፣ በቡድን፣ በጎሣና በሀገር ደረጃ የሚከሰቱ ግጭቶች አሉ፡፡ እነዚህም ግጭቶች ማህበረሰቡ ባቋቋመው ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት እየረገቡና እየተቃለሉ ቆይተዋል፡፡ ተቋማቱ እስከሁንም ድረስ እየተሰራባቸው ነው፡፡ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት የአፈፃፀም ሥርዓታቸው ከመደበኛው የህግ ሥርዓት በተለየ መንገድ ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃላዊ ተላልፎ የሚከናወን ነው፡፡ እነዚህ በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉት ባህላዊ እሴቶች ግጭቶችን በመፍታት ዘላቂ ሰላምን የማረጋገጥና ልማትን የማፋጠን ድርሻቸው የጎላ ነው፡፡

ከዘመናዊው የፍትህ ሥርዓት አፈፃፀምና አሠራር ውጭ በተለየ መንገድ የሚከናወኑት ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት የማህበረሰቡን ወግ፣ ባህልና እምነት መሠረት አድርገው ስለሚያካሄዱ በህዝቡ ዘንድ ተቀባይነት አላቸው፡፡ ስለሆነም በግለሰቦች፣ በቤተሰብ፣ በቡድንና በጎሣዎች መካከል የሚከሰቱትን ግጭቶች የማርገብና የመፍታት ብቃት አላቸው፡፡ ብዙ የህብረተሰብ ክፍሎች የየራሳቸው የግጭት መፍቻ ተቋማት አሉዋቸው፡፡ በነዚህም የግጭት መፍቻ ተቋማት የተለያዩ ስልቶችን እየተጠቀሙ ሰላማቸውን ያረጋግጣሉ፡፡ የዩኒት ስሜትን በመላበስ የሚከናወነው ባህላዊ ተቋም ለባህሉ ባለቤቶች ስነ-ልቦናዊ እርካታን ያጎናጽፋል፡፡

በማህበረሰቡ ምርጫና እምነት ላይ ተመስርቶ የሚከናወነው ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋም ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው፡፡ ይህንንም የባህሉ ባለቤቶች ስለሚያምኑበት አዘውትረው ይገለገሉበታል፡፡ ይሁን እንጂ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘይ በሀገራችን ህገ መንግስት ዕውቅና አግኝቶ በህገ መንግሥቱ ሰነድ ላይ ተካቶ አይታይም፡፡ ዘላቂ ሰላምን እያሰፈነ ለሀገር ዕድገትና ልማት ጉልህ አስተዋጽኦ የሚያበረክተው ባህላዊ እሴት ተቀባይነት አግኝቶ ከመደበኛው የፍትህ ሥርዓት ጎን ለጎን በአጋዥነት ቢሠራ ጥሩ ውጤት ይኖረዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህ ጥናት በሸኮ ብሔረሰብ ግጭትን በመፍታት ሂደት ላይ ከፍተኛ ሚና ባለው በርቱማ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ላይ የሚያተኩር ነው፡፡

ይህ ጥናት በአምስት ምዕራፎች ተከፋፍሎ የቀረበ ነው፡፡ የመጀመሪያው ምዕራፍ በአፍሪካም ሆነ በኢትዮጵያ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት ያላቸውን ፋይዳ ይዳስሳል፤ ማህበረሰቡ በየኔነት ስሜት ጠብቆ እንዳቆያቸውም ያመላክታል፡፡ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ አስፈላጊነት፣ የጥናት ወሰን የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች የተገለፁት በምዕራፍ አንድ ሥር ነው፡፡

በምዕራፍ ሁለት ውስጥ ጥናቱ ትኩረት ስላደረገው አካባቢ መልከዓ-ምድራዊ አቀማመጥ በመረጃ የተደገፈ ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡ የህዝቡ ብዛት፣ አደረጃጀት፣ አኗኗር ቋንቋና እምነት ተዳሷል፡፡ እነዚህም ዳራዊ መረጃዎች ስለማህበረሰቡ ማንነት ፍንጭ የሚሰጡ በመሆናቸው ከባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ ጋር ተያያዥነት አላቸው፡፡

በምዕራፍ ሦስት የተካተቱት ጉዳዮች የግጭት ምንነት ትውሮችና የአፈታት ዘዴዎችን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ምዕራፉ ስለግጭት ምንነት የተለያዩ ብያኔዎች ትውሮች መኖራቸውን ያመላክታል፤ የግጭት አፈታት በአለም አቀፍ፣ በአፍሪካና በኢትዮጵያ ደረጃ የማህበረሰቡን ባህላዊ እሴቶች ትኩረት ባለመከተላቸው ስኬታማ እንዳልሆኑ ያሳያል፡፡ ከትውሮቹ የተገኘው ግንዛቤም ባህላዊ የግጭት አፈታት ከመደበኛው የፍትህ ሥርዓት ጋር ጎን ለጎን ቢተገበርና ዕውቅና ቢሰጠው ጠቀሜታው የጎላ ነው የሚል ሀሳብ ይዟል፡፡ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት በአፍሪካና በኢትዮጵያ ግጭትን እንዴት እንደሚያስወግዱ በምሳሌ የተደገፈ መረጃ ቀርቧል፡፡

ምዕራፍ አራት «በርቴማ፤ ባህላዊ የግጭት አፈታት በሽኮ ብሔረሰብ» ምን እንደሚመስል እንዲሁም የብሔረሰቡ የአስተዳደርና የፍትህ ተቋማት አሠራርን ከብሔረሰቡ አውራ የመረጃ አቀባዮች የተገኘውን መረጃ በማጠናቀር ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ በተጨማሪም ምዕራፉ በሽኮ ብሔረሰብ የሚከሰቱ የግጭት ዓይነቶችና የአፈታት ሥርዓታቸው የተተነተነበት ነው፡፡ በብሔረሰቡ መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶችን በመለየት በአምስት የግጭት ዓይነቶች ላይ ትንታኔ ቀርቧል፡፡ እነዚህም፤ የነፍስ ግድያ፣ ጠለፋ፣ የባልና ሚስት አለመግባባት፣ በጎሣና በጎሣ መካከል የሚፈጠር ግጭትና በሀብት ስርቆት የሚከሰቱ ግጭቶች ናቸው፡፡

በመጨረሻው ምዕራፍ የበርቴማ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ማህበረ ባህላዊ ፋይዳዎች አስመልክቶ፣ የማጠቃለያ ሃሳቦችንና ባህላዊ ተቋሙን የበለጠ ለዘመናዊው አኗኗር ለመገልገል የሚያስችሉ የመፍትሄ አቅጣጫዎች ቀርበዋል፡፡

## 1.1 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት አቢይ ዓላማ የሸኮ ብሔረሰብ ግጭትን በባሕላዊ መንገድ ለመፍታት በሚጠቀሙበት በርቱማ በሚባለው ባህላዊ የእርቅ ሥርዓት ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ ስለሆነም የሸኮ ብሔረሰብ ግጭትን በባህላዊ መንገድ እንዴት እንደሚያስወግድ በመመርመር፤ የባህላዊ ተቋሙ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ፣ አስተዳደራዊና ባህላዊ ሁኔታዎች እንዲሁም ፋይዳውን፣ ባህላዊ ተቋሙ ያለውን ጠቀሜታ በመረዳት ከዘመናዊ የፍትህ ተቋምና አስተዳደር ጎን ለጎን በአጋዥነት እንዲሠራ ዕውቅና መስጠት እንደሚጠቅም፣ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋሙ አሁን ባለበት ሁኔታ በድምፅና በምስል ቀርፆ ማስቀመጥ ጠቀሜታ አለው የሚሉ አላማዎች አሉት፡፡ ጥናቱ እነዚህን አበይት ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ጥረት ያደርጋል፡፡ እነዚህም

1. በሸኮ ብሔረሰብ ለሚፈጠሩ ግጭቶች ምክንያት የሚሆኑ ዋና ዋና ጉዳዮችና መከሰቻዎቻቸው ምንድን ናቸው?
2. የሸኮ ብሔረሰብ ለባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት ያለው አመለካከት ምንድን ነው?
3. ብሔረሰቡ በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰቱትን ግጭቶች የሚያስወግደው በባህላዊ መንገድ ነው፡፡ ከዘመናዊ የፍትህ ሥርዓት ይልቅ ባህላዊ ዳኝነቱን የሚመርጠው ለምንድነው?
4. በበርቱማ የሚፈቱ ግጭቶችና የአፈፃፀም ሥርዓታቸው ምን ይመስላል?
5. የበርቱማ ማህበረ-ባህላዊ ክዋኔ፣ አውዱና ፋይዳው ምንድነው? የሚሉ ናቸው፡፡

## 1.2 የጥናቱ አስፈላጊነት

የሸኮ ብሔረሰብ የግጭት አፈታት ምርምርና ጥናት አልተካሄደበትም፡፡ ስለዚህ ይህ ጥናት ስለ ጉዳዩ ያለውን የእውቀትና የመረጃ ክፍተት ለመሙላት ይረዳል የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡

የሸኮ ብሔረሰብ ተመካክሮና ተቻችሎ ለመኖር የሚያስችሉ ባህላዊ እሴቶች እንዳሉት ማሳየት፤ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች ቀጣይነት ባለው ሁኔታ የማህበረሰቡን ህይወት ለመምራት አስፈላጊዎች እንደሆኑ መጠቆም፣ የህዝብ ባህላዊ እሴቶች እንዲጠበቁና ትኩረት እንዲሰጣቸው በማሳሰብ ረገድ ጥናቱ አስፈላጊነት ይኖረዋል ተብሎ ይታመናል፡፡

በተጨማሪም ከዚህ በታች የተጠቀሱት ነጥቦች የጥናቱን ጠቀሜታ የሚመለከቱ ናቸው።

- የሸኮ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት የሚከተሉት የአፈፃፀም ሥርዓትና ደንብ መገንዘብ ለዘመናዊው የፍትህ ሥርዓት ሊኖረው የሚችለውን ድጋፍ ለመገንዘብ ይረዳል። ኮይናብ፣ የጎሣ መሪዎች፣ ቃልቾች፣ ቡርጃብና ታዋቂ ያገር ሽማግሌዎች ግጭቶች ሳይባባሱ በእንጭጩ የመፍታት ብቃት እንዳላቸው የመንግሥት አካላት ተረድተው ለባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት ትኩረት ሰጥተው በጋራ የሚሠሩበት ሁኔታ እንዲፈጠር ሃሳብ ይሰነዝራል።
- በባህላዊ መንገድ የሚከናወነው የግጭት አፈታት በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት አለው። ማህበረሰቡን በቅርቡ የሚያገለግል በመሆኑም በሰው ኃይል ብክነት፣ በገንዘብ ወጭና በጊዜ አጠቃቀም ላይ ያለው ጠቀሜታ የጎላ ነው። ስለዚህ የመንግሥት አስፈፃሚ አካላት በርቱግ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓትን በማደራጀት ተቋሙ ተጠናክሮ አገልግሎቱን የሚቀጥልበትን መንገድ ለመቀየስ የሚያስችሉ ስልቶችን ያመላክታል።
- የዚህ ጥናት ግኝት በህዝቦች ወግ ልማድና እምነት ላይ የተመሰረተ የልማት፣ የፖለቲካና የባህል ፖሊሲ ለሀገር ብልፅግናና ዘላቂ ሠላምን ለማረጋገጥ ጠቀሜታ እንዳለው በማስገንዘብ ረገድ ፋይዳ ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል።
- ጥናቱ በማህበረሰባዊ ባህልና በሰላም አብሮ መኖር ዘዴዎች ላይ የሚያተኩር በመሆኑ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በብሔረሰቡ አካባቢ ለሚያከናውኑት ጉዳይ የህብረተሰቡን ማህበራዊ ስነ ልቦና ያገናዘቡ ተግባራትን ለማከናወን ሊኖረው የሚችለውን ዘላቂ ፋይዳ ያጤኑ ዘንድ እንደ መነሻ ሆኖ ያገለግላል። ጥናቱ የበርቱግን ባህላዊየግጭት አፈታት ክዋኔ በድምፅና በምስል ቀርፆ ለማቆየትና ለትውልድ ለማስተላለፍ ጠቀሜታ አለው።

## 1.3 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

የጥናቱ አካሄድ ሁለቱን የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎችን ምልከታንና ቃለ መጠይቅን መሠረት ያደረገ ነው። በመስክ ምርምር ወቅት ምልከታና ቃለ-መጠይቅ ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች ናቸው። ይህንንም እውነት Goldistien (1964 : 80-90) "of the several methods and techniques which may be used by the collector in field work, two will serve to supply him with practically all the data necessary for the solution of field problems, these methods includes observation and interview" በማለት ይገልፃል።እኒም መረጃዎችን በምልከታና በቃለ መጠይቅ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች አማካይነት ሰብስቢያለሁ።

ለጥናቱ ወደ መስክ ከመውጣቴ በፊት የግጭት ትውሮች ምንነትና የአፈታት ስልቶች በዓለም፣ በአፍሪካና በኢትዮጵያ ደረጃ ምን ይዘት እንዳላቸው ጥልቅ ንባብ አካሄዷል። ስለ ብሔረሰቡ ማህበረ-ባህላዊ አጠቃላይ ገፅታ ለማግኘትም ተዛማጅ የጽሑፍ መረጃዎችን ለማቀናበር የቤተ መጻህፍት ምርምር አካሄጃለሁ።

በመረጃ አሰባሰብ ወቅት «ተፈጥሮአዊ» (Natural)፣ «አርተፊሻል» (Artificial) እና «ቅንብር ተፈጥሮአዊ» (Induced Natural) የሚባሉ መቼቶች እንዳሉ ፈቃደ (1991: 122-123) ይናገራል። ከእነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ አውዶች መካከል በመጠቀም መረጃዎችን ሰብስቢያለሁ። መረጃውን ለመሰብሰብ አራት ወር ፈጅቶብኛል።

አጥኚው በመስክ ምርምር ባካሄደበት ወቅት የሽኮ ብሔረሰብ በባህላዊ መንገድ ግጭትን የሚፈቱበትን ስርዓት በቅንብር ተፈጥሮአዊ መቼት በተግባር እንዲከውኑ በማድረግ ሁለት የእርቅ ስርዓቶችን በተለያዩ ቀናት በፎቶ ካሜራ የተደገፈ መረጃ ተሰብስቧል፤ በመረጃ አሰባሰብ ወቅት በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች መጠቀም አስተማማኝ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ እንደሚያግዝ Toelkon (1996) ይገልፃል።

የበርቱማ፣ ሥርዓቱን፣ ደንቡንና አፈፃፀሙን እንዲሁም ባህላዊ ዐውዱ የሚኖረውን ፋይዳ በተመለከተ ከጎሣ መሪዎች፣ ከርጃቦችና ታዋቂ የአገር ሽማግሌዎች/አውራ የመረጃ አቀባዮች/ ጋር ቃለ መጠይቅና ውይይት ተካሂዷል። መረጃዎችም በቴፕሪከርደር ተቀርፀዋል።

ለጥናቱ የመረጥኩት አካባቢ ቀደም ሲል በሥራ ምክንያት ለ 16 ዓመት የቆየሁበት ስለሆነ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ለመግባባት ችግር አልፈጠረብኝም። ስለሆነም ይህ በማህበረሰቡ ዘንድ ያለኝ እውቅና የምፈልገውን መረጃ ለማግኘት አንፃራዊ በሆነ መልኩ እገዛ አድርጎልኛል።

በመስክ ሥራዬ የተለያዩ ሰዎች ጋር ተገናኝቼ የጥናቴን ዓላማ በማስረዳት ከመረጃ አቀባዮች ጋር በመስሪያ ቤት፣ በመኖሪያ ቤት፣ በእምነት ቦታዎችና በገበያ ስፍራ ለመተዋወቅ ችያለሁ። አገናኞችም የምፈልጋቸውን የመረጃ አቀባዮች በመኖሪያ ቤታቸው፣ በገበያ፣ በመዝናኛ ቦታዎች፣ በለቅሶ ቤት፣ በእምነት ቦታዎችና በእድር መሰብሰቢያ ቦታዎች በመውሰድ አገናኝተውኛል። የመረጃ አቀባዮቼም ከ 30-92 ባለው የዕድሜ ክልል የሚገኙ ናቸው። ስብጥራቸውም የመንግሥት ሠራተኞች፣ የኃይማኖት መሪዎች፣ ገበሬዎች፣ ባላባቶች፣ የጎሣ መሪዎች ታዋቂ የአገር ሽማግሌዎች ሲሆኑ ሁሉም የሽኮ ብሔረሰብ ተወላጅ የሆኑ ወንዶች ናቸው።

በመስክ ሥራ ላይ ተገኝቼ በአራት ፊልም ፎቶግራፎችን በመቅረጽ፣ በሁለት የቴፕ ካሴት የድምፅ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ችያለሁ። በምልከታና በቃለ መጠይቅ አማካኝነት የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች ከድምፅ ወደ ጽሑፍ በመቀየር ፎቶግራፎችን በማሳተም ለጥናቱ በሚያመች መልኩ እየመደብኩ ትንተና ሰጥቼባቸዋለሁ።

## 1.4 የጥናቱ ዘዴ

በሸኮ ብሔረሰብ የሚከናወነው በርቱማ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ላይ ተመስርቶ የቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ የባህላዊ ተቋሙን አጠቃላይ ገፅታ በማሳየትና በመተንተን የቀረበ ነው። በመሆኑም ገላጭ /Descriptive/ እና የይዘት ትንተና /Content Analysis / የሚሉትን የጥናት ዘዴዎችን ተጠቅሟል።

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት በሸካ መስተዳደር ዞን ሥር በምትገኘው የኪ. ወረዳ ውስጥ በሚከናወነው በርቱማ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ላይ ተወስኖ የቀረበ ነው። ይሁን እንጂ በበርቱማ ሥርዓት ዙሪያ ኮይናብን፣ የጉማ መሪዎችንና ቡርጃብን በተመለከተ ብሔረሰቡ ወጥ የሆነ የአስተዳደርና የፍትህ ስርዓትን የሚጠቀም መሆኑን ለማረጋገጥ አጎራባች ወደ ሆነው ሸኮ ወረዳ በመሄድ የብሔረሰቡን ባህልና ወግ የሚያውቁ ሰዎች ጋር በመገናኘት መረጃ ተሰብስቧል። ኮይናብ የሚገኘው በሸኮ ወረዳ ፊጆቃ በሚባል ቀበሌ መሆኑን ማወቅ የተቻለው ከሸኮ ወረዳ ከሚኖሩ የባህሉ ባለቤቶች ነው። ስለዚህ በተወሰነ ደረጃ በጥናቱ አካትቸዋለሁ። የየኪ ወረዳና የሸኮ ወረዳ ተጎራባች በመሆናቸው የሸኮ ብሔረሰብ ባህላዊ ተቋም በሁለቱም ወረዳ ተመሣሣይነት እንዳለው ለአራት ጊዜ ሸኮ ወረዳ በመሄድ መረጃዎችን ሰብስቤ ተመሳሳይነቱን አረጋግጫለሁ።

በየኪ ወረዳ በተለያዩ አካባቢዎች ብዙ የጉማ መሪዎች፣ ቡርጃቦች፣ ቃልቾች ታዋቂ የአገር ሽማግሎች አሉ። ጥናቱ በ8 ቀበሌዎች ላይ የተመሠረተ ነው። እነዚህ ቀበሌዎች የተመረጡበት ምክንያት የጉማ መሪዎች፣ ቡርጃቦችና ታዋቂ የአገር ሽማግሎች ስለሚገኙባቸው ነው። ስለሆነም ከቆርማ፣ ከዜንኪ፣ ከምቺ፣ ከበጪ፣ ከሸሻ፣ ከዳረሙ፣ ከያናና ቴፒ ከተማ ከሚኖሩ የሸኮ ብሔረሰብ ተወላጆች መረጃ ሰብስቢያለሁ።

በእነዚህ በተመረጡት ቀበሌዎች የጉማ መሪዎች፣ ቡርጃቦች፣ ቃልቾችና የአገር ሽማግሎች ይኖራሉ። እነዚህ ደግሞ የበርቱማ ሥርዓትን በበላይነት የሚያከናወኑ በማህበረሰቡ ተቀባይነት ያላቸውና የተከበሩ ናቸው። በተለያዩ ቀበሌዎች ግጭቶች ሲፈጠሩ የሚያስታርቁ /ግጭቶች

እንዲወገዱ የሚያደርጉ/ ለእርቅ ማስፈፀሚያ የሚያገለግሉ የማስታረቂያ መሣሪያዎች ያሏቸውና በወረዳው ውስጥ የሚከሰቱ ግጭቶችን በመፍታት የሚታወቁ የጎሣ መሪዎች ቡርጃቦች፣ ታልቾችና ታዋቂ ሽማግሌዎችን ለመምረጥ እነዚህን መመዘኛ መስፈርቶች ተጠቅሚያለሁ፡፡ በመሆኑም በቆርጫ፣ በሸሻና በምቹ የሚኖሩ የጎሣ መሪዎችን ቡርጃቦችንና የአገር ሽማግሌዎችን ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች አድርጌያቸዋለሁ፡፡

## 1.6 በጥናቱ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች

### 1.6.1 በጥናቱ ሂደት ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች

ሀ. አንዳንድ የመረጃ አቀባዮች በቴፕሪከርደር ለመቀረጽና ፎቶግራፍ ለመነሳት ፈቃደኛ አለመሆንና መረጃ ለመስጠት አለመፈለጋቸው፡፡

ለ. በድህረ ምረቃ መርሃ-ግብር ለጥናቱ የተፈቀደው ገንዘብ በቂ አለመሆን

ሐ. ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል እና ትንበር ተፈጥሮአዊ መቾት ለመሥራት በመረጥኩት ቀበሌ ላይ ባህላዊ ዳኝነትን በቪዲዮና ፎቶ ግራፍ የተደገፈ ቀረፃ ማከናወንና የመረጃ አቀባዮች ሀሳባቸውን እንዲቀይሩ ማድረጋቸው፡፡

መ. በየኪ ወረዳ በ 1994 ዓ.ም በተካሄደው ጦርነት ሰበብ እና የማካሄደውን የግጭት አፈታት ሥርዓት ከግንዛቤ ማነስ የተፈጠረው አሉባልታ ስጋት በማስከተሉ ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ሥራዬን ማንተቱ

### 1.6.2 የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች

ሀ. በአካባቢው ከሚገኙ ነዋሪዎች መካከል የተማሩትን፣ በመንግሥት ሥራ ላይ ያሉትንና የመስተዳደር አካላትን እንዲሁም የተሻለ ግንዛቤ ያላቸውን የብሔረሰቡን ተወላጆች በመቅረብ የጥናቱን ዓላማና ጥቅሙን በማስረዳት መረጃ አቀባዮች ተረጋግተው ያለ ሥጋት እንዲናገሩና መረጃ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

ለ. ከዩኒቨርስቲው የተፈቀደው ገንዘብ ጥናታዊ ጽሑፉን ለመስራት እንደማያስችል በመገንዘብ ከአምስት ያላነሱ የእርዳታ ድርጅቶችን /NGO/፣ የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት መስተዳደር ጽ/ቤትንና የብሔረሰቦች ም/ቤትን ለጥናቱ ማከናወኛ የሚሆን ገንዘብ ጠይቄ መፍትሔ አላገኘሁም፡፡ ስለዚህ ከራሴ ገንዘብ በማውጣት ለጥናታዊ ጽሑፉ እንዲውል አድርጌያለሁ፡፡

ሐ. የዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል ባለሙያዎች የተለያዩ የመቅረጫ መሣሪያዎችንና በቂ ገንዘብ ስለነበራቸው የባህሉን ባለቤቶች በገንዘብም ሆነ በክዋኔው ላይ ለሚያስፈልጉ የሚበሉና የሚጠጡ ነገሮችን በብዛት ስላቀረቡ ህዝቡ ተደስቷል:: ስለሆነም በቂ መረጃ ሰጥቷል:: ክዋኔውንም በአግባቡና በቅንነት አሳይቷል:: እኔም የቡድኑን መሪ በወቅቱ የተቀረፀውን የቪዲዮ ካሴት እንዲሰጠኝ፣ ፎቶግራፍ ማንሳት እንድችልና ለመረጃ አቀባዮቼ ቃለ መጠይቅ እንዳቀርብ ብጠይቅ ከመመልከት ውጭ ሌላው እንደማይቻል ስለተነገረኝ ክዋኔውን በቦታው ተገኝቼ ተመልክቻለሁ:: ከመስክ ሥራዬ ከተመለስኩ በኋላ ለጥናቱ የሚረዳኝ መረጃ ለማግኘ ት ከተቀረጸው የቪዲዮ ካሴት የተወሰኑትን ለመጠቀም እንዲተባበሩኝ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል የትብብር ደብዳቤ በማፃፍ በቦታው ሄጄ ብጠይቅ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አልሆኑም::ስለዚህ በቪዲዮ ካሴት የተደገፈ መረጃ ማቅረብ አልተቻለም::

በወቅቱ የዋልታ ባለሙያዎች ከወረዳው ከለቀቁ በኋላ በመረጥኩት ቀበሌ ሄጄ መረጃየን ለማሰባሰብ ስሞክር የመረጃ አቀባዮቼ ገንዘብና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን እንደፈለጉ ስለተረዳሁ የምግብና የመጠጥ ግብዣ በማቅረብ የምፈልገውን መረጃ ለማግኘት ችያለሁ::

መ. በአካባቢው ለተፈጠረው አለባልታ ከመስተዳደር አካላት ጋር በመቀራረብና የጥናቱን ዓላማ በማስረዳት እንዲሁም ህጋዊ ደብዳቤ የያዝኩ መሆኔን በማሳየቴ ተግባብተን ችግሩ ተቃሎ መረጃዎችን ስላማዊ በሆነ መንገድ አሰባስቤያለሁ::

# 2. የሸኮ ብሔረሰብ መህበረ-ባህላዊ ዳራ

## 2.1 ስነ-ምህዳራዊ ገፅታ

የየኪ ወረዳ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት በሸካ ዞን መስተዳደር ውስጥ ካሉት ሦስት ወረዳዎችና ሁለት የከተማ ሽግግር አስተዳደሮች አንዷ ናት:: ወረዳዋ 26 ቀበሌዎችና 4 የከተማ ቀበሌዎች አሏት:: የቆዳ ስፋቷ 48871.31 ሄክታር ወይም 488.71 ስኩር ኪሎ ሜትር ሲሆን በዞን ውስጥ ካሉት ወረዳዎች ሰፊ የቆዳ ስፋትና ብዙ ህዝብ የሚኖርባት መሆኗን ከየኪ ወረዳ ገጠር ልማት ጽ/ቤት የተገኘው መረጃ ያስረዳል::

የየኪ ወረዳ በምሥራቅ የከፋ ዞን፣ በምዕራብ የጋምቤላ ክልል፣ በሰሜን የአንደራቻ ወረዳና የከፋ ዞን፣ በደቡብ የቤንቺ ማጂ ዞን የሸኮ ወረዳ ያዋስኗታል::

ቴፒ የወረዳዋ ዋና ከተማ ስትሆን ከአዲስ አበባ 565 ኪሎ ሜትርና ከሸካ ዞን መስተዳደር ዋና ከተማ ከሆነችው ማሻ 87 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች:: የየኪ ወረዳ በሦስት መልክዓ-ምድራዊ አካባቢዎች ትከፈላለች:: እነሱም ደጋ፣ ወይናደጋና ቆላ ተብለው ይጠራሉ:: ደጋ የሆነው ክፍል 2443.55 ሄክታር ሲሆን ወይና ደጋው 12217.75 ሄክታር ነው:: ቆላ ደግሞ 34209.7 ሄክታር እንደሆነ ከሸካ ዞን ፕላንና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ የተገኘውን መረጃ ማየት ይቻላል::

ወረዳዋ ከባህር ወለል ከ 900 እስከ 2000 ሜትር ከፍታ ላይ የምትገኝ ሲሆን አማካይ የሙቀት መጠኗ ከ26-36 ድግሪ ሴንቲግሬድ የዝናብ መጠኗ ደግሞ ከ 1200 እስከ 2200 ሚ.ሊ. ሊትር መሆኑን የቴፒ እርሻ ምርምር ማዕከል መረጃ ያስረዳል::

የመሬት አቀማመጥ ገፅታዋ ወጣ-ገባ፣ ተራራማና ሜዳማ ነው:: ተዳፋታማ መሬትም በከፊል ይገኛል:: ተዳፋታማውና ሜዳማው የመሬት አካል ትንንሽና ትልልቅ ወንዞች አመቱን በሙሉ ይፈስበታል:: ከእነዚህ ወንዞች መካከል ሻይ፣ አቻኒ፣ ብትን ውኃ፣ ደፒ፣ባርኒታ፣ወንጂወጪ፣ ከደቺ፣ ሜኒት፣ በጥቅሉ በቶ ተብሉ የሚጠራው በእንድረስ፣ በሾሻ፣ በፌዴና በጨ አልፎ የሚሄደውን ወንዝ የሚያጠቃልሉ ናቸው::

በወረዳዋ ውስጥ ተፈጥሮአዊ ደኖች ይገኛሉ:: በእነዚህ ደኖች ውስጥም በጣም ትልልቅና ሰማይ ጠቀስ ዛፎች አሉ:: ቀደም ሲል በወረዳዋ ጥቅጥቅ ያሉ ደኖች በብዛት ይገኙ ነበር:: በውስጣቸውም የተለያዩ የዱር እራዊቶች ይኖራሉ:: በአሁኑ ጊዜ በአካባቢው የሚኖሩ ገበሬዎች ገቢ ለማግኘት ሲባል ለከሰል፣ ለማገዶና ጣውላ ምርት ስለሚጠቀሙ ደኖች በከፍተኛ ፍጥነት

እየወደመ ነው። የከተማ ነዋሪዎችም የማገዶ ግብአታቸው በአካባቢው ደን ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ለደኖች መራቆት ሌላው ምክንያት ነው። የአካባቢ ማህበረሰብ ስለ ደን ጥቅም ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ ስለሆነ ከፍጆታ ውጭ የጣውላ ኮንትሮባንድ ሽያጭ ስለሚያከናው የደን ጭፍጨፋውን በተፋጠነ መንገድ ቀጥሏል።

ተሾመ ኃይሌ (1998፣47) ለ B. A ድግሪ ማሟያ በፃፈው ጽሑፍ ከየኪ ወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት የተገኘውን መረጃ ጠቅሶ ከ 1991-1996 ዓ.ም 2000 ኪዩቢክ ሜትር የደን ውጤት ከወረዳዋ ወደ ማዕከላዊ ገበያ መላኩን ገልፆ የደን ጭፍጨፋ ከንውኑ ህጋዊ መስመርን ያልተከተለ የአሠራር ሥርዓት የሌለውና በሚጨፈጨፈው ምትክ ሌላ የማይተከል መሆኑን ጠቁሟል።

በየኪ ወረዳ ከፍተኛ የአየር መዛባት እየተከሰተ ነው። ለዚህም አንዱ ምክንያት የደን ጭፍጨፋ መበራከት ነው። በወረዳው ደን ከማጥፋት ውጭ በምትኩ የደን ተከላ አይካሄድም። የደን መኖር ለሰው ልጅ ህይወት በጣም አስፈላጊ ነው። የዱር አራዊትና አእዋፍም ህልውናቸው በደን ላይ የተመሰረተ ነው።

በወረዳዋ አስገራሚና ጠቃሚ የሆኑ የዛፍ ዓይነቶች የሚገኙ ሲሆን እነዚህም ረጅም ዕድሜ ያላቸውና በሌላ አካባቢ የማይገኙም አሉባቸው። ከዛፍ ዓይነቶች ዋንዛ፣ ቀረሮ፣ ዋርካ፣ ሾላ ጥቁር እንጨት፣ ሰሳ፣ ጎንጃ፣ ቡትጂ፣ ተንጊ፣ መቲ፣ ጎጂባሮ፣ ሽፋ፣ በርከሽ፣ ብሳና ወይራ፣ ገቦ፣ ወዘተ ... የመሣሠሉት ይገኛሉ። እነዚህም ዛፎች ለቀፎ መስቀያ፣ ለቤት መሥሪያ፣ ለከሰል፣ ለቤት ቁሳቁስ መሥሪያ፣ ... የሚያገለግሉ አሉባቸው። ዋንዛ፣ ቀረሮ፣ ጎንጂና ጎጅባሮ ለጣውላ፣ ለቤት መሥሪያ፣ ለማዕዘን፣ ለሽንት ቤት ንጣፍ ስለሚገለገሉባቸው እነዚህ የዛፍ አይነቶች በአደጋ ላይ ያሉ ናቸው።

በየኪ ወረዳ ትልልቅና ትንንሽ የዱር አራዊቶች አሉ። ከእነዚህም ጎሽ፣ አንበሳ፣ ነብር፣ ከርከሮ፣ ጆብ፣ ሚዳቋ፣ ጃርት፣ ጉሬዛ፣ ዝንጀሮ፣ ጦጣ፣ ቀበሮ አሣማ፣ ወዘተ የመሣሠሉት ናቸው። ዝንጀሮ፣ ጦጣ ጉሬዛና ጃርት እንደቅደም ተከተላቸው በብዛት ይገኛሉ። የቤት እንስሳትን በተመለከተ የቀንድ ከብቶች፣ የጋማ ከብቶች፣ በግ፣ ፍየል፣ ዶሮ በብዛት በገጠር አካባቢ የሚገኙ ሲሆን ገበሬዎች በገቢ ምንጭነት ይጠቀሙባቸዋል።

ወረዳዋ ከምትታወቅባቸው አንዱ ቡና በብዛት የሚመረትባት መሆኑ ነው። በዓመት በአማካይ 4200 ቶን ቡና ወደ ማዕከላዊ ገበያ የሚላከው ከየኪ ወረዳ ነው። በልማዳዊ መንገድ ከሚመረተው ቡና አንስቶ በዘመናዊ መልክ በምርምር የታገዘ አተካከልና አመራረቱን ጨምሮ እጅግ ከፍተኛ የቡና ምርት ለማዕከላዊ ገበያ የሚቀርበው ከየኪ ወረዳ ነው። ከቡና ተክል ልማት

ድርጅት፣ ከአስር ያላነሱ ኢንቨስተሮችና ከእያንዳንዱ ገበሬ ብዙ የቡና ምርት ይገኛል:: ሌላው ወረዳዋን ታዋቂ የሚያደርጋት የቅመማ ቅመም ምርት ነው:: በወረዳው 500ሄክታር መሬት በቅመማ ቅመም የተሸፈነ መሆኑን የየኪ ወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ የተገኘው መረጃ ያስረዳል::

እርድ፣ ዝንጅብል፣ ቆንዶበርበሬ፣ የጎማዛፍ፣ ሔል፣ ኮረሪማ ... በብዛት ይመረታሉ:: አቮካዶ፣ ማንጎ፣ ጊሾጣ፣ ሽክኔሩት፣ ፓፓያ፣ ሙዝ፣ ብርቱካን፣ ዘይቱና፣ መንደሪን፣ ሎሚና ሌሎችም ፍራፍሬዎች ለየኪ ወረዳ መገለጫዎቿ ናቸው:: የድንጋይ ማዕድን የሸክላ አፈርና ጠጠር በወረዳዋ ይገኛሉ:: አገልግሎትም እየሰጡ ነው:: ወደ ፊት መጠናት ያለባቸው የማዕድን ሀብቶች እንደሚኖሩ ይገመታል:: በየኪ ወረዳ የቱሪስት መስህብ ሊሆኑ የሚችሉ ዋሻዎችና ፏፏቴዎች ይገኛሉ:: በእርምጭ ቀበሌ የሚገኘው የአቻኒ ፏፏቴ አስደናቂና ማራኪ ነው:: በደገ ቀበሌ ካንቲሜ የሚባል ዋሻ አለ:: እንዲሁም በሰላም በር (ሹማ) ቀበሌ በስፋቱና በጥንታዊነቱ የሚታወቅ ዱሻ የሚባል ዋሻ እንዳለ ከየኪ ወረዳ ምክር ቤት የተገኘው መረጃ ያስረዳል:: እነዚህን ጠቃሚ የሆኑ ዋሻዎችንና ፏፏቴውን በአግባቡ የሚታወቁበትና ለአገልግሎት የሚውሉበት መንገድ እንዲፈጠር የየኑ ባህልና ቱሪዝም እንዲሁም የወረዳው ባህልና ማስታወቂያ ቢሮ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል::

የየኪ ወረዳ ከኃይለ ስላሴ ዘመነ-መንግሥት ጀምሮ በወረዳ መስተዳድርነት ተሰይማ ትኖር ነበር:: በኃይለ ስላሴና በደርግ ዘመነ-መንግሥት በኢሉባቡር ክፍለ ሀገር በሞቻ አውራጃ ሥር ነበረች:: በአሁኑ ጊዜ ተጠሪነቷ ለሸካ ዞን ሆና በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት ሥር እንደምትገኝ ከየኪ ወረዳ ምክር ቤት የተገኘው መረጃ ያረጋግጣል::

## 2.2 ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ህይወት

በ1987 ዓ.ም በተደረገው የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ሪፖርት መሠረት የየኪ ወረዳ ህዝብ ብዛት 85699 ነው:: ከዚህም ከአጠቃላይ የወረዳዋ ነዋሪዎች 75083 የሚሆኑት በገጠር 10616 ደግሞ በከተማ እንደሚኖሩ ተጠቁሟል:: በገጠር የሚኖረው ህዝብ ኑሮው የተመሠረተው በግብርና ነው:: ይህ ቆጠራ ከተከናወነ 12 ዓመት አልፎታል:: አሁን ከየኪ ወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ በተገኘው መረጃ መሠረት በወረዳው 134109 ህዝብ እንዳለ ያስረዳል:: ከዚህም 112848 በገጠር 21261 በከተማ እንደሚኖሩ ይጠቁማል::

### 2.2.1 ኢኮኖሚያዊ ህይወት

በየኪ ወረዳ የሚኖሩ ህዝቦች በአብዛኛው በግብርና ሙያ የሚተዳደሩ ናቸው:: በንግድ የሚተዳደሩ ሰዎች ሁለተኛውን ደረጃ ይይዛሉ:: በሸክላ ሥራና በሌሎች የሥራ መስኮች

የሚተዳደሩት በጣም አነስተኛ ናቸው:: ከ 87.6% የሚሆነው ህዝብ የሚተዳደርበትን የግብርና መስክ ስንመለከት በወረዳው ውስጥ ለእርሻ የሚሆን መሬት 9723 ሄክታር ነው:: 9723 ሄክታር የሚሆነው የታረሰ መሬት ነው:: በደን የተያዘው መሬት ደግሞ 10239 ሄክታር እንደሆነ ከየኪ. ከወረዳ ግብርና ገጠር ልማት ቢሮ  የተገኘው መረጃ ያስረዳል::

የገጠር ልማት ይዞታን ስንመለከት አንድ አባወራ ገበሬ በአማካይ 1.5 ሄክታር መሬት ይኖረዋል:: በወረዳዋ ውስጥ ያለው አፈር ሎሞ (Loam) ነው:: በወረዳዋ ሁለት ዋና ዋና የአዝመራ ወቅቶች አሉ:: እነዚህም ከየካቲት እስከ ነሐሴ እና ከመስከረም እስከ ጥር ያሉ ወቅቶች ናቸው:: ከየካቲት እስከ ነሐሴ ባሉት ወራት የበቆሎ የቦሎቄና የዳጉሣ አዝማራ ይዘመራል:: ከመስከረም እስከ ጥር መጨረሻ የማሽላ አዝመራ ወቅት ነው:: ቡናም የሚለቀመው ከመስከረም እስከ ጥር ባሉ ወራቶች ነው:: በየኪ፣ በደፒና በሬዶ ቀበሌ የሚኖሩ አርሶ አደሮች በመስኖ በመጠቀም ሽንኩርት፣ ቲማቲም ጎመን፣ ቀይስር፣ ካሮት፣ ቃሪያ፣ ስኳር ድንች፣ ድንች፣ ወዘተ ... እያመረቱ ለአካባቢው ገበያ እንደሚያቀርቡ ከየኪ ወረዳ ገጠር ልማት ጽ/ቤት የተገኘው መረጃ ይገልፃል::

በየኪ ወረዳ በቆሎ፣ ማሽላ፣ ዳጉሣና ቦሎቄ በብዛት ይመረታሉ:: ባካ፣ ኮቺ፣ ኮሰባና ኮታሬ ባህላዊ ምግቦችም በመጠኑ ይመረታሉ:: ቴፒ የየኪ ወረዳ ዋና ከተማ ስትሆን በንግድ ግብይት በኩል ያላት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በጣም ከፍተኛ ነው:: በአካባቢው የሚመረቱ የቡና፣ የቆዳና ሌጦ ውጤቶች፣ ፍራፍሬዎችና ቅመማ ቅመሞች ለሽያጭ ወደ ማዕከላዊ ገበያ ይላካሉ::

በወረዳዋ የሚኖሩ ገበሬዎች ኋላ ቀር በሆኑ የእርሻ መሣሪያዎች ይገለገላሉ:: የእርሻ መሣሪያቹ ከብረትና ከእንጨት የተሠሩ ሞፈር፣ ቀንበር፣ ማረሻ፣ ወገል፣ ገሶ፣ ገጀራ፣ ማጭድ፣ ዶማ፣ ዘቢያ፣ ... ናቸው:: በአካባቢው በበሬ ማረስ የተለመደ ቢሆንም በሰው ኃይል እየተቆፈረ ጥኣ/ጎደሬ/፣ ኮቺ፣ ኮሰባና ኮታሬ የሸኮና የመዠንገር ባህላዊ ምግቦች ይተከላሉ:: በገጠር ቀበሌዎቹ የምስጥ ከይስና የእህል ትሎች፣ የብርቱካንና የቡና በሽታ ጉዳት እያደረሱ ነው:: በረግረጋማ አካባቢዎችም የጉበት ትል፣ አባሰንጋ፣ አባጎርባ ወዘተ የመሣሠሉት በሽታዎች የእንስሳትን ጤንነት የሚያውኩ እንደሆኑ ከወረዳው ግብርና ቢሮ የተገኘው መረጃ ያረጋግጣል::

### 2.2.2 ማህበራዊ መዋቅር

በየኪ ወረዳ ብዙ ብሔረሰቦች ይኖራሉ:: ከእነዚህም የሸኮ፣ የመዠንገር፣ የሸካቾ፣ የካፍቾ፣ የአማራ፣ የኦሮሞ፣ የዳውሮ፣ የጉራጌ፣ የቤንቺ ... ዋና ዋናዎቹ ናቸው:: የጥናቱ ዋና ትኩረት የሸኮ ብሔረሰብ ስለሆነ የብሔረሰቡን አመጣጥና አደረጃጀት እንመለከታለን::

የሸኮ ብሔረሰብ በቤንቺ ማጂ ዞን በጉራ ፈርዳ፣ በሸኮ፣ በበቃ፣ በቴጢ፣ በጠመንጃ ያኘር አካባቢ በሸካ ዞን ደግሞ በየኪ ወረዳ በ 13 ቀበሌዎች ውስጥ ይኖራሉ:: በሁሉም ቦታ የሚኖሩት ሸኮዎች መተዳደሪያቸው ግብርና ነው:: የተወሰኑት በከብት እርባታ ይተዳደራሉ:: በየኪ ወረዳ የሚኖሩት የሸኮ ብሔረሰቦች ቋንቋቸው ሸኮ ሲሆን ከወረዳዋ ስያሜ ጀምሮ የብዙዎቹ ቀበሌዎች ስሞች፣ በሸኮ ብሔረሰብ ስም ተሰይመው እያንዳንዱ ቀበሌ የጎሣ መሪዎች ተከፋፍለው እንደተሰጠ የመረጃ አቀባዮች ነግረውኛል (ከርክስ አፋ 15/4/99 ቴፒ ከተማ ቢሮ ውስጥ) :: የቀበሌዎቹም ስም ቆርጫ፣ ዛና፣ እንድሪስ፣ ሾሻ፣ ምቼ፣ በጨሊ፣ ዝንኪ፣ ዳረሙ፣ የኪ፣ኩኪ፣ ሹማ ሲሆኑ በመስክ ሥራዬ በመረጃ አቀባይነት የቆርጫ፣ የሾሻ፣ የምቼና የበጨሊ የጎሣ መሪዎች በአካል በማግኘት መረጃ ወስጃለሁ::


የሸኮ ብሔረሰብ አመጣጥና ታሪክን በተመለከተ በህትመት ደረጃ ተፅፎ የቀረበ አላገኘሁም:: ስለዚህ የዕድሜ ባለፀጋ ሽማግሌዎችን፣ የተማሩ የብሔረሰብ ተወላጆችን ከመንግስት መሥሪያ ቤት የወረዳ ባለስልጣኖችንና የብሔረሰቡን ባለባቶችና ቃልቾች በመጠየቅና በብሔረሰቡ ዙሪያ የተፃፉ መጣጥፎችን በማፈላለግ ማግኘት የተቻለውን በመያዝ ለመፃፍ ሞክሬያለሁ:: የሸኮ ብሔረሰብ ዓመተ-ምህረቱና ቀኑ በውል ባይታወቅም ከ 400 ዓመት በፊት በማጅ አካባቢ ጆባ የሚባል ቦታ ይኖር እንደነበረና በዚያም ሁለት ወንድማማቾች እንደነበሩ እነሱም ኮይናብና ሸነኪያዝ/ኢፋንዛብ/ ይባሉ እንደነበርና ከአባታቸው ከጆባ ቡርገፍ እንደተወለዱ አያት ቅድመ አያቶቻችንን ነግረውናል በማለት የመረጃ አቀባዮች ገልፀውልኛል (አባሽዋ ቆርጫ፣ 5/4/99 የኪ ወረዳ ቆርጫ ቀበሌ)::

ከጆባ ቡርገፍ ልጆች አንዱ የሆነው ኮይናብ ወይም ዘቱ ከነልጆቹ በጉራ ፈርዳ አድርጎ በበቃ፣ በቴጢ፣ በሸኮ ወረዳ፣ በየኪ ወረዳ ሰፍሮ ይገኛል:: በብሔረሰቡ ባህልና እምነት መሠረት ወንድ ልጅ ለአቅመ አዳም ከደረሰ ከአባቱ ተለይቶ ወንዝ ተሻግሮ ካልኖረና አካባቢውን ካልለቀቀ የአባቱ ሙት መንፈስ ወይም ሚያንጊ አባቱን ይገድለዋል ወይም ራሱ ይሞታል ተብሎ ስለሚታመን ብሔረሰቡ በአንድ ቦታ ተወስኖ እንዳይኖር ማድረጉን የመረጃ አቀባዮች ይናገራሉ:: ይህን እውነታ ለማረጋገጥ አክሊሉ ይልማ (1976:88) The phonology of sheko በሚል ርዕስ በፃፉት ላይ እንደገለጹት The territory in which the Sheko language speakers inhabit extends from north-west across the boundary of the Kefa administrative region to Illubabor around the vicinity of the Teppi town in the Yeki district of the Mocha Awraja በማለት ገልፀዋል::

የሸኮ ብሔረሰብ ራሱን የቻለ ንጉሥ አለው:: የንጉሡ ስም በሸኮ ቋንቋ «ወግባብ» ይባላል:: «ወግባብ» የሚሾመው በህዝብ ድምጽ ብልጫ አይደለም:: በትውልድ በዘር ሲወርድ ሲዋረድ

የሚገኝ ነው። የእንጋገሱ ሁኔታ ከይናብ ከአባቱ ከጀባ ቡርገፎ ተለይቶ ጉራፈርድ «ታብ» በተባለ ቦታ ከሰፈረ በኋላ ጉዞውን በመቀጠል «ዛዛ» ወደ ተባለ ቦታ ይሄዳል።

እዚያም አልቆየም «አፑታ» በተባለ ቦታ ሰፈረ። አፑታ በተባለ አካባቢ በሚኖርበት ወቅት የንግሥና ሥርዓቱ ተፈፀመ። በባህሉ የንግሥና ሥርዓት ሲፈፀም የእኛም ዛፍ ፍሬ፣ «የዘርጳቡይ/ንጭ ድንቢጥ ወፍ/ ጭራ፣ ማር፣ ካምዱ/ሥሪያ ያልጀመረ ጥቁር ወይፈን/፣ ወልዳ ያቢቃች ጥቁር አሮጊት ላም ያስፈልጋሉ። እነዚህ ከተዘጋጁ በኋላ የዘርጳቡይ ጭራ በማርና በደም ይታጠባል/ይነፃል/። ከዚያም ላባው በፀጉሩ ይሰካል። የእኛም ዛፍ ፍሬ በክር ተሰክቶ በአንገቱ ይጠልቅለታል። ወይፈንና አሮጊቷ ላም በቡርጃብ አማካይነት ይታረዳሉ። የተሰበሰበው ህዝብ ሥጋውን ይበላል። ይህ ሁሉ በአግባቡ ከተከናወነ በኋላ ዚቱ/ከይናብ/ ተብሎ ይነግሳል። ይህም የንግሥና ሥርዓት ከትውልድ ወደ ትውልድ ለከይናብ ዘሮች ብቻ ይተላለፋል። ሥርወ መንግስቱ ለማንም ጎሣ አይፈቀድም። አይሰጥም በማለት የመረጃ አቀባዮች ነግረውኛል። (ፍትሻ ሾሻ 10/4/99 የኪ. ወረዳ ሾሻ ቀበሌ)።



በመስክ ላይ ከመረጃ አቀባዮች መረጃ ሲሰበሰብ።
ከግራ ወደ ቀኝ ፍትሻ ሾሻና ካሣ ከርሺን



ከቀኝ ወደ ግራ ሻሻ ወሸካራና ከርከስ ኡፋ

የሸኮ ብሔረሰብ በተለያዩ ጎሳዎች የተከፋፈለ ቢሆንም ሁሉም ጎሣዎች ኮይናብ የበላይና ንግስናውን ከፈጣሪ ያገኘው እደሆነ አድርገው ስለሚረዱ ኮይናብን ያመልኩበታል:: ከፈጣሪ በታች ስልጣን የተሰጠውና የብሔረሰቡን ችግር ሊያቃልል የሚችል አጠቃላይ ለህይወት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች የሚገኙት በኮይናብ እንደሆነ ያምናሉ:: ኮይናብ ዝናብን የሚያወርድ ምህረትን የሚያመጣ ዘመንን የተባረከና ምቹ ማድረግ የሚችል ሲቆጣና ባህላዊ ሥርዓቱ ሲጣስ ደግሞ መዓትን የሚያወርድ፣ የሚገድልና የሚያጠፋ መሆኑን ይረዳሉ:: ኮይናብ በአሁኑ ጊዜ በሸኮ ወረዳ ፈጆቃ ቀበሌ ኮይኒካ አካባቢ ይኖራል:: ኮይናብ በአመት አንድ ጊዜ ጉብኝት በማካሄድ የብሔረሰቡ ባህላዊ ህግና ሥርዓቶች መከበራቸውን ያረጋግጣል:: ግብርም ከየጎሣ መሪዎች በየደረጃው ባህላዊ ህጉ በሚፈቅደው መሠረት ይቀበላል:: ከኮይናብ የተወለዱትና በተለያየ አካባቢ የሚኖሩት ግብር የሚያስገቡበት ጊዜ የተወሰነ ነው:: በሚታወቀው ዓመትና ወር ግብሩን የማያስገባ ካለ በሀገሪቱ በሽታ፣ ድርቅ፣ ጦርነትና ሁከት ይከተላል ተብሎ ስለሚታመን ባህላዊ ደንቡና ሥርዓቱ አይነኬና የማይቀር ጉዳይ ነው::

ኮይናብ ከ **5-10** ዓመት አንድ ጊዜ ወደ ጀባ ቡርገፍ ግብር ይወስዳል:: የሚወስደውም ግብር ድንግል ልጃገረድ፣ የዝሆን ጥርስ፣ ሙሉ ጥቁር ያልተጠቃች ጊደር፣ ወልዳ የጨረሰች ጥቁር ላም ነው:: ኮይናብ ግብሩን በሚወስድበት ጊዜ መጠንቀቅና ማረጋገጥ ያለበት ነገር አለ:: ይህም በሀገሩ ላይ «**ሸክን**» (የወር አበባ ሳታይ የወለደች ሴት) አለመኖሯን፣ «**ሹተማ**» (ከሥጋ ዘመዱ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ያደረገ ሰው) የሌለ መሆኑን፣ «**አንቾብ**» (በቤተሰብ ቁጥጥር ሥር እያለች ባል ሳታገባ ያረገዘች ሴት) የሌለች መሆኑንና በዚያ አካባቢ ከተወለዱ ህፃናት «ጋሞ» (የታችኛው ጥርስ ሳይወጣ የላይኛው ጥርስ ቀድሞ በቅሎ የተገኘ) የሌለ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል (ሻሻ ወሸካሬ 10/5/99 ዝንኪ ቀበሌ)::

ይህን በትክክል አጣርቶና ፈትሾ ነው ግብር ማስገባት ያለበት ይህን ሳያረጋግጥ ግብር የሚያስገባ ከሆነ ኮይናብ እዚያው ይሞታል ተብሎ ይታመናል::



ከግራ ወደ ቀኝ ቱቻ ሾሻና ካሳ ከርሽን




ከግራ ወደ ቀኝ ከርከስ ኡፋና ሻሻ ወሽካራ

በሸኮ ብሔረሰብ አንዲት ሴት የወር አበባ ሳታይ ልጅ ከወለደች በባህሉ የሚወገዝና ለሀገርም ጥፋት የሚያመጣ ነው ተብሎ ይታመናል። በብሔረሰቡ ከሥጋ ዘመዱ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ በጣም የተወገዘ ነው። ይህን የሚፈፅም ሰው ከማህበረሰቡ ተገልሎ በጫካ ውስጥ እስከ ሰባት ዓመት እንዲቀመጥ ይደረጋል። ከሰው ጋር አይገናኝም፣ ሰው በበላበትና በጠጣበት አይጠጣም አይበላም። በቅጠል ይበላል ይጠጣል። የሚበላው የሰዎችን ትራፊ የሚጠጣውም የሰዎችን ጭላጭ ነው። ማህበራዊ ደንቡን ስለጣሰ እንደሰው አይቆጠርም። ሌላው አንድ ህፃን ተወልዶ ጥርስ ሲያበቅል ቀድሞ መውጣት ያለበት የታችኛው ጥርስ ነው። የላይኛው ጥርስ ቀድሞ የሚወጣ ከሆን አገሩን ያረክሳል፣ ዘመኑ የረሃብና የችግር ይሆናል፣ ለሰው አይበጅም ተብሎ ይታመናል።

የሸኮ ብሔረሰብ የዘር ግንድ አራት ዋና ዋና ክፍል አለው። ይህም በጣም የሚከበረውና የንጉሥ ዘር የሚባለው የኮይናብ(የንጉሥ) ዘር ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከኮይናብ ዘሮች ቀጥለው የሚገኙት ኢያዙ(የጎሣ መሪዎች) ናቸው። በሦስተኛ ደረጃ የሚገኙት የቡርጃብ(የእስታራቂ) ዘር የሚባሉ

ናቸው:: አራተኛ ደግሞ ባንዱ የሚባሉትና ዝቅተኛ ጎሣዎች ናቸው የኮይናብን (የንጉሡን) ዘር ስንመለከት ጀባ ኮይናብንና ሽክኪያዝ/ኢፋንባብ/ ን ወለደ:: ኮይናብ ደግሞ ጎተበን፣ ፈንጀስን፣ ፈንኩምስን፣ ቱርቸንችን፣ ዘዝቴትን፣ ጆምደስን፣ ቱፋን፣ በጭንና ዘይኒን ወለደ:: ጎተብ የሚባለው ደግሞ በዱ የሚባል ልጅ ወለደ:: በዱም አይበራን፣ጆርኩብን፣ ኮራብን፣ አርሸን፣ ቱሬታን፣ ኮይንስንና ሽርሹን ወለደ እነዚህ በሽኮ ብሔረሰብ የበላይ ወይም ከፍተኛ የሚባሉት የኮይናብ ልጆችና የልጅ ልጆች ከማጅ እስከ የኪ ድረስ የየራሳቸው ግዛት አላቸው::

ቁጥር 1. የሽኮ ብሔረሰብ ንጉሥ/ወግባብ/ የዘር ግንድ ሚያሳይ ሰንጠረዥ





ምንጭ:: የመረጃ አቀባይ ከርንስ አዱ፣ ሻሻ ወሽካራ፣ ካሳ ከርሸን

በጣም ከሚከበሩት የኮይናብ ዘሮች ቀጥለው የሚገኙት ኪያዙ(የጎሣ መሪዎች) ተብለው የሚመደቡት ፈጆያብ፣ በሩያብ፣ ዘድያብ፣ አቡያብ፣ ካንያብ፣ዱዱያብ፣ ጎትያብ፣ጎፍያብ ወዘተ ናቸው:: በሸኮ ብሔረሰብ የቡርጃብ (የአስታራቂ ዘር) የሚባሉት ጎሣዎች ቡርጅያብ፣ አቡያብ፣ቶከያብ፣ከርቲያብ፣ሹርጤያብ፣ሹቴያብ፣ ቤርሲያብ ወዘተ. ናቸው:: በሦስተኛ ደረጃ የሚገኙትና ስልጣን የሌላቸውና ከተራው ህዝብ የሚመደቡ ጎሣዎች ኡርያብ፣ ቤንቲያብ፣ አርያብ፣ ቱድያብ፣ ሹጊያብ፣ አትኮያብ፣ አብትያብ ወዘተ. ናቸው:: ባንዱ የሚባሉት በአራተኛ ደረጃ የሚገኙት በብሔረሰቡ ባህልና እምነት ዝቅተኛ ጎሣዎች ተብለው ከማህበሩ የተገለሉ ናቸው::

እነዚህም ሸኮ ስራዎች ቆዳ ፋቂዎችና ቀጥቃጮች የሚሏቸው ናቸው፡፡ አክሊሉ ይልማ (1988:31) The phonology of Sheko በሚል ርዕስ ለ M.A ድግሪ ማሟያ ባቀረበው የጥናት ወረቀት ላይ የሚከተለውን ብሏል፡፡

"Among the Sheko, the blacksmiths, tanners and potters are despised and confined to separate classes. These groups are refered to as bándu by the rest of the society."

**ቁጥር 2. የሸኮ ብሔረሰብ የዘር ግንድ**




ምንጭ፡- የመረጃ አቀባዮች ሸሎ ፈይ፣ ኡርማ ዚቴ፣ ሀብታሙ ስጠኝ

## 2.3 ቋንቋና እምነት

### 2.3.1 ቋንቋ

የሸኮ ቋንቋ በቤንች ማጂ ዞን ጉራፈርዳ ወረዳ፣ በሸኮ ወረዳ በቲጤና በበቃ አካባቢ፤ በሸካ ዞን ደግሞ በየኪ ወረዳ ይነገራል:: በሁሉም አካባቢ ያሉ የሸኮ ቋንቋ ተናጋሪዎች ያለምንም ችግር ይግባባሉ:: የሸኮ ብሔረሰብ ቋንቋውንም ሆነ ብሔረሰቡን ሸኮ በማለት ይጠራዋል:: አክሊሉ ይልማ (1988:2) የሸኮ ቋንቋ በቦታ ርቀት ምክንያት አለመለያየቱን ሲያብራራ "The Sheko language spoken in both districts/ Sheko and Guraferda/is similar ብሏል::

የሸኮ ቋንቋ ከኦሞቲክ የቋንቋ ግንድ/ዝርያ/ እንደሚመድብ ቤንደር 1976:47/ Language in Ethiopia በሚለው መጽሐፍ ገልጿል:: የሸኮ ቋንቋ ምዕራባዊ ተብለው በሁለት ከተከፈሉት የማጅ ቋንቋዎችና ከፋ ጊሞጅያን መካከል በማጅ ቋንቋዎች ሥር ይገኛል:: እነሱም ማጂ፣ ሸኮና ናኦ ናቸው:: እነዚህ ቋንቋዎች ተቀራራቢ እንደሆኑም ቤንደር (1976:50) "To put it another way maji and Sheko are about as close as English and German. (about 60 percent)" በማለት ገልጿል:: ቤንዳር እዚህ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የቻለው በቋንቋዎች መካከል ያለውን የድምጽ፣ የቃላትና የምዕላድ ተመሣሣይነት በማየት ይመስላል::

የሸኮ ቋንቋ ተናጋሪዎች የሚገኙት በደቡብ፣ በሱዳን ጠረፍ አካባቢ፣ በምሥራቅ፣ ከዲዝ፣ ሜኒትና ቤንች ቋንቋ ተናጋሪዎች፣ በምዕራብ፤ ከአኙዋክና ኑየር ቋንቋ ተናጋዎች፣ በሰሜን ከቤንች፣ ከከፋ፤ ከሸኮና መዥንግር ቋንቋ ተናጋሪዎች ጋር ይዋሰናሉ:: የሸኮ ቋንቋ ተናጋሪዎች ቁጥር 23459 እንደሆነ በ 1987 ዓ.ም የተካሄደው የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ውጤት ያስረዳል:: ይህም ከጠቅላላ በቤንች ማጅና ሸካ ያሉትን ጨምሮ ነው:: ይህ ቆጠራ የተካሄደው ከ 12 ዓመት በፊት ስለሆነ አሁን ያለው ቁጥር ከዚህ የተለየ ሊሆን ይችላል::

### 2.3.2 እምነት

የሸኮ ብሔረሰቦች ክርስትና እምነት የሚከተሉ ናቸው:: ከእግዚአብሔር ቃል ቀጥሎ ቃልቻ በብሔረሰቡ ትልቅ ክብር ይሰጠዋል:: ቃልቻ የወግባብ/ንጉስ/ ዘርችም እንደሚገኙበት ተገልጿል:: በማህበረሰቡ ወግና ሥርዓት ቃልቻ ከወረርሽኝ፣ ከድርቅ፣ ከውጋ ማጥለቅለቅ፣ ከኃይለኛ ነፋስና በረዶ እንዲጠብቁ፣ ዘመኑ የፍስሃ እንዲሆን፣ ከብቶች እንዲረቡና በሽታ እንዳያጠቃባቸው፣ ጣርንትና ብጥብጥ እንዳይኖር፣ ስለት በማስገባትና ግብር በመስጠት ፀሎት ይደርጋል::

የአካባቢ ሰዎች ሲታመሙ፣ ልጅ መውለድ ሲፈልጉ፣ ሲጣሉ፣ ዕቃ ሲጠፋባቸው፣ አዝመራው ምርታማ እንዲሆን፣ ልጆች የተባረኩና ጤናማ እንዲሆኑ ቃልቾች ዘንድ እየመጡ ይፀልያሉ::

ይህም ቃልቾቹ ከፈጣሪ /ከእግዚአብሔር/ ጋር ግንኙነት ስለሚያደርጉ ልመናና ፀሎታችንን ያስሙልናል ብለው ስለሚያምኑ ነው፡፡ የፈለጉት ነገር ሲሳካ በምስጢር ለቃልቾች የሚያቀርቡትን ስለት ለመፈፀም ቃል የሚገባበትም ሁኔታም አለ፡፡

በአሁኑ ሰዓት ብዙው የሸኮ ብሔረሰብ ፕሮቴስታንትና የሃዋሪያት ቤተክርስቲያን እምነት የሚከተል ሲሆን የኦርቶዶክስ ኃይማኖት ተከታዮችም ቁጥር ቀላል አይደለም፡፡ በአባት መንፈስ/ሚያንጊ/ ና በቃልቻ የሚያምኑ ሰዎች አሁንም ጥቂት የሚባሉ አይደሉም፡፡

## 2.4 የሸኮ ብሔረሰብ ባህላዊ ተቋም አወቃቀር

የሸኮ ብሔረሰብ በውስጡ ከ 35 በላይ ጎሣዎች አሉት፡፡ እነዚህ ጎሣዎች ተቀራርበው የሚኖሩ በመሆናቸው በተለያዩ ምክንያቶች በመካከላቸው ግጭት ይፈጠራል፡፡ በግለሠብ፣ በቡድንና በጎሣዎች መካከል አለመግባባት ተፈጥሮ ግጭት ሲያስከትል ወደ ከፍተኛ ብጥብጥና ጥፋት ከመሄዱ በፊት ግጭቱ እንዲረግብና እንዲወገድ ይደረጋል፡፡ ይህን የተፈጠረን ግጭት የሚያቃልሉበትን ሥርዓት ነው የሸኮ ብሔረሰቦች በርቱሣ ብለው የሚጠሩት፡፡ በርቱሣ ማለት የተጣለን ማስታረቅ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ በብሔረሰብ ባህልና ልማድ ግጭት ሲፈጠር የማቃለልና የማስወገድ ሥራ የሚሠሩት 1ኛ የንጉሥ/ኪይናብ/ ዘሮች 2ኛ ኪያዞ (የጎ መሪዎች) 3ኛ ቡርጃብ 4ኛ ደግሞ ቃልቾች ናቸው፡፡ እነዚህ በማህበረሰቡ ዕውቅና ያላቸው የግጭት አስወጋጅ ሲሆኑ ቀላልና ዕለታዊ ግጭቶችን ደግሞ በአካባቢው ነዋሪ ዘንድ ተደማጭነት ያላቸውና በቁም ነገረኛነታቸውና በዕውቀታቸው የተሻሉ የሚባሉ ሰዎች ያቃልላሉ፡፡



አባ ሸዋ ቆርጫ ኪያዙ
(የጎሣ መሪ)



ከግራ ወደ ቀኝ ቦንጊ ጌሪ (የአገር ሽማግሌ)
ጎጊ ፋካ (የአገር ሽማግሌ)
ፍትሽ ሾሻ (ኪያዙ የጎሣ መሪ)
ተሰማ ዚማ (የቀበሌ አመራር)

## 2.4.1 ኮይናብ

ኮይናብ በሸኮ ብሔረሰብ የተከበረና ቁንጮ የንጉስ/ወግባብ/ ዘር ነው:: የብሔረሰቡ የበላይ ጠባቂና ማህበረሰቡ የሚተዳደርባቸው ሥርዓትና ልማዶችን የሚያስከብር ነው:: በሥሩ በተዋቀሩት የጎሣ መሪዎችና በርጀብ አቀንባባሪነት ሊፈቱ ያልቻሉ ከባድ ግጭቶችን የሚያስወግድና አልባት የሚሰጥ ነው:: በሸኮ ብሔረሰብ ኮይናብ የተናገረውን እምቢ የሚልና የሚጥስ የለም:: የኮይናብን ቃል የሚጥስ፣ ውሳኔውን የማይቀበል፣ ህይወቱ እንደሚጠፋ ተደርጎ ይታመናል:: የኮይናብን ቃል የጣሰ ማህበረሰቡ ከማህበራዊ ህይወት ነጥሎ ገለልተኛ ያደርገዋል:: ኮይናብ የሚታመን የሚከበርና የሚመለከበት እንዲሆን ያደረገው ሁሉ ነገር በስ ይሳካል ምክንያቱም ከፈጣሪ እገዛ ይደረግለታል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው:: ስለዚህ የግጭት መፍትሔ ማሳረጊያውና የመጨረሻ ይግባኝ የሚደመደምበት በኮይናብ ነው:: በበርቱማ ሥርዓት ከኮይናብ የሚያልፍ ነገር የለም:: በስው ይቋጫል::

### 2.4.2 ቡርጃብ

ቡርጃብ በሸኮ ብሔረሰብ ዋና የእርቅ አስፈፃሚ ነው:: ከንጉሡ ጀምሮ በየአካባቢ ያሉ የጎሣ መሪዎች ቡርጃብን በርቱማን/ እርቅን/ እንዲያከናውን ያዙታል:: ቡርጃብ ንጉሡን ከማንገስ ጀምሮ በተለያዩ ባህላዊ ክንዋኔዎች ላይ የሚበሉና የሚጠጡ ነገሮችን በቅድሚያ የሚቀመስ ነው:: የንጉሡና በየደረጃው ያሉ የጎሣ መሪዎች ባለሟልም ነው:: የጎሣ መሪዎች ሲሞቱ የቀብር ሥነ-ሥርዓት የሚያስፈጽመው ቡርጃብ ነው:: በሸኮ ብሄረሰብ የጎሣ መሪ ሲሞት አይቀበርም:: አልጋ ተሰርቶለት በደን ውስጥ ነው የሚቀመጠው:: ስለዚህ የሸኮ ብሔረሰብ ደን እንዳይመነጠር ይቆጣጠራሉ:: ደን ከሌለ የጎሣ መሪዎች ማረፊያ ስለሚያጡ በሁሉም አካባቢ ደን ጥበቃ ይደረግለታል:: በሸኮ ኮብም /ጫካ/ በተባለ ቦታ ዙሪያው ታጥሮ የጎሣ መሪዎች ሬሣ ይቀመጣል:: ቡርጃብ ሬሣውን ለሦስት ወር ያክል ይጠብቃል:: የመረጃ አቀባዮች (ካሳ ከርሸን 10/4/99 ሾሻ ቀበሌ፣ ደሳለኝ ምቼ 15/4/99 የኪ ወረዳ ምቼ ቀበሌ) እንደገለፁልኝ የጎሣ መሪው መሬት ውስጥ የማይቀበርበት ምክንያት ምድሪቱ በድርቅ ተቃጥላ ዝናብ አይጥልም፣ ንብ አይታነብም፤ የረሃብና የበሽታ ዘመን ይሆናል፤ ሞት ይበዛል ተብሎ ስለሚታመን ነው:: በመጨረሻ ሬሣውን ነብር ከበላው ዘመኑ የጥጋብ ትውልዱም የተባረከና ረጅም እድሜም ይኖረዋል:: ሬሣውን ጉንዳን ከበላው ደግሞ ዘመኑ የቸነፈር ትውልዱም የተረገመና ዕድሜው አጭር ይሆናል ብለው ያምናሉ:: ስለዚህ ቡርጃብ በማህበረሰቡ ዘንድ የሚከበርበት ምክንያት ብዙ ማህበራዊ ጉዳዮችን በማከናወኑ ነው:: ቡርጃብ በማስታረቅ ስራ የተሠማራ በመሆኑ በዚህ ዘርፍ የካበተ ልምድ አለው:: በግጭት አፈታት ዙሪያ ያለው ዕውቀት ከፍተኛ ነው:: ምክንያቱም አዘውትሮ የማስታረቅ ሥራ ስለሚያከናውን ነው:: ይህም ከህይወታቸው ጋር የቀጥታ ግንኙነትና ከፍ ያለ ዋጋ ይኖረዋል ማለት ነው::

### 2.4.3 ኪያዙ (የጎሣ መሪዎች)

የሸኮ የጎሣ መሪዎች የሚኖሩት በተለያዩ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ነው:: የጎሣ መሪዎች በሥራቸው ያሉ ህዝቦችን ይጠብቃሉ፣ ይንከባከባሉ:: ህዝቡ ካልኖረና ሰላም ከጠፋ እኛም መኖር አንችልም በማለት ከበታቻቸው ያለው ህዝብ ማህበሩ የሚተዳደርበትን ባህላዊ ህግ እንዲያከብር እንዲንከባከብና ጠብቆ ለትውልድ እንዲያስተላልፍ ጠንክረው ይሠራሉ:: ግጭት ተፈጥሮ ወደ ብጥብጥና ሁከት እንዳይሸጋገር ግጭቱን የማርገብ፣ የማቃለልና፣ የማስወገድ ሥራ ይሠራሉ::

በሸኮ ብሔረሰብ ውስጥ ሰው የገደለ፣ የሰው ሚስት የደፈረ ወይም ያገባ፣ ጠለፋ ያካሄደ፣ ከዘመዱ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈፀመ፣ ወይም በማህበረሰቡ ህግና ሥርዓት የተከለከለና ነውር የሆነ ሥራ የፈፀመ ሰው ጥፋት በፈፀመበት አካባቢ መኖር አይችልም:: ባህላዊ ህግና ሥርዓቱ አይፈቅድም:: ጥፋት ፈጽሞ በዚያው አካባቢ ሲኖር በደል የተፈፀመባቸው ቤተሰቦች ቢገድሉት ተጠያቂ አይሆኑም:: ሌሎችም የማህበረሰቡ አባላት «ነግ በኔ» በማሰብ ከማህበራዊ

ግንኙነት እንዲቋረጥ ያደርጋሉ፡፡ ስለዚህ አካባቢውን ለቆ ወደ ሌላ ቦታ ይሰደዳል፡፡ ጥፋተኛው የተሰደደበት አካባቢ የሚኖረው የጎሣ መሪ /አባ ቀሮ/ ለምን እንደመጣ ያስጠይቀዋል ወይም ራሱ (ጥፋተኛው) ሄዶ ለጎሣ መሪው ይናገራል፡፡ የጎሣ መሪ ጉዳዩን መርምሮ ካረጋገጠ በኋላ በሥሩ ያለውን ቡርጃብ በማስጠራት ጥፋት የተፈፀመበት አካባቢ ላለው የጎሣ መሪ ሄዶ እንዲናገር ያዛል፡፡ መልዕክት የተላከበት የጎሣ መሪ የራሱን አካባቢ ቡርጀብ ጠርቶ ጥፋት የተፈፀመባቸውን ቤተሰቦች በባህሉ ህግ መሠረት አነጋግሮ እርቅ /በርቱሣ/ እንዲያከናውን ያዝዋል፡፡

በዚህ የአሠራር ሂደት መሠረት ሁለቱ የጎሣ መሪዎች የተፈጠረው ግጭት የሚቃለልበትን ሁኔታ ያመቻቻሉ፡፡ አፈፃፀሙንም ይከታተላሉ፡፡ በየትኛውም አካባቢ ያለ የጎሣ መሪ በሚያስተዳድረው አካባቢ አዲስ ሰው ከመጣ ዝም ብሎ አያየውም፤ በዚያ አካባቢ እንዲቀመጥ አይፈቀድም፡፡ ስለዚህ ወንጀል የፈፀመ ሰው ተደብቆ መኖር አይችልም፡፡ የጎሣ መሪዎች ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት የሚታረቁበትን ሁኔታ ማመቻቸት ብቻ ሳይሆን ወንጀለኛ በክልላቸው እንዳይኖር ይቆጣጠራሉ፡፡ እንዲህ በመሆኑ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት አላቸው፤ ይከበራሉ፤ ይደመጣሉ፡፡ የጎሣ መሪዎች ኃላፊነትን መወጣት ባህላዊ ሥርዓቱ የተጠናከረ ህዝቡም የዚህ ባህላዊ ህግ ተገዢ እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡

### 2.4.4 ቃልቻ

በሸኮ ብሔረሰብ የኮይናብ/ ንጉሥ/ ዘር የሆኑት ቃልቻም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ በበርቱሳ ሥርዓት ላይ በንጉሥ ዘርነታቸውም ይሁን በቃልቻነታቸው ይሣተፋሉ፡፡ ቃልቻ እንደ ማህበረሰቡ እምነት ሁሉን ነገር ማየት የሚችል ነው፡፡ ከቃልቻ ሊሰወር የሚችል ነገር የለም ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለዚህ ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት በበርቱሣ ሥርዓት ወቅት ምንም ነገር አይደብቁም፡፡ ቃልቻው አድርጉ ያላቸውን ይፈፅማሉ፡፡ ቃልቻ የተጣሉ ሰዎችን የማስታረቅ ብቃት አለው፡፡ የማህበረሰቡ አባላት ችግር ሲያጋጥማቸው ወደ ቃልቻ በመሄድ ስለት ይሳላሉ፡፡ ሰዎች ያጡት ነገር እንዲሰጣቸው ወደ ቃልቻ በመሄድ ይፀልያሉ፡፡ በቃልቻው አማካይነት የፈለጉትን እንደሚያገኙና ከጭንቀታቸው እንደሚላቀቁ አድርገው ያስባሉ፡፡ በዚህ ምክንያት ለቃልቻ የሚሰጠው ክበሬታ ከፍተኛ ነው፡፡ ቃልቻ በድብቅ የሚከናወኑ ነገሮችን ያጋልጣል፡፡ ምክንያቱም ለእግዚአብሔር ቅርብ ስለሆነ ይረዳዋል፡፡ ወይም ውቃቢው ይነግረዋል ተብሎ ይታመናል፡፡

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት በማህበረሰቡ የሚደመጡ የሚከበሩና የሚመሰከባቸውም ናቸው፡፡ ማህበረሰቡ በሚመራበት ባህላዊ ህግ መሠረት የተዋቀሩ በመሆናቸው ግጭትን ለማርገብና ለማስወገድ ድርሻቸው የላቀ ነው፡፡ ህብረተሰቡም ወደ ዘመናዊ የህግ ሥርዓት ሳይሄድ በዚያው

አካባቢ ባቋቋመው ባህላዊ እርቅ ስርዓት እየተገለገለ ሰላሙን በማረጋገጥ ልማቱን ያፋጥናል፡፡ ስለሆነም የበርቴሣ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት በአካባቢ ባህላዊ የህግ ሥርዓት መከናወኑ ጊዜንና ገንዘብን ይቆጥባል፡፡ ማህበራዊ ግንኙነትን ያጠነክራል፡፡ ባህላዊ ተቋሙን ያስከብራል፡፡ ቂም በቀልን አስወግደው ሁሉም በልማት ተሳታፊ እንዲሆን ይረዳል፡፡

# 3. ክለሳ ድርሳናት

## 3.1 የግጭት ብያኔ

የሰው ልጅ ከማህራዊ ኑሮ ተነጥሎ ሊኖር ስለማይችል በዚሁ ግንኙነቱ ምክንያት ግጭቶች በተለያዩ ምክንያቶች መፈጠራቸው አይቀርም:: ግጭት ገሃድና ስውር በሆነ መንገድ ጎጂና ጠቃሚ የሆኑ ነገሮች እንዲፈጠሩ ምክንያት ይሆናል ግጭትን በተመለከተ የተለያዩ ሰዎች የተለያዩ ሀሳቦች አሏቸው:: ሀብታሙ ወንድሙ(1998) ግጭት ባህላዊ አመለካከት ባላቸው ሰዎች ዘንድ አስቸጋሪና ለጥፋት የሚዳርግ ስለሆነ መወገድ እንዳለበት እና በግጭት የሚሳተፉ ሰዎችም ሁከት ፈጣሪ በጥባጭና እርኩስ መንፈስ የተጠናወታቸው እንደሆኑ ተደርገው ይቆጠራሉ ይላል:: በማለት ሲገልጹ በሌላ በኩል በርካታ የማህበራዊ ሳይንስ ምሁራን ግጭት ሁሌ የሚኖር፣ ጠቃሚና ወደ ዕድገት ጎዳና የሚያራምድ መሆኑን ይናገራሉ:: የግጭትን ምንነት፣መንሻ ምክንያት፣ ስለአይነቱና ስለሚያስከትለው ነገር... የፖለቲካ፣የስነ ሰብእ፣ የስነ-ልቦናና የስነ-ልሳን ምሁራን ብዙ ሃሳቦችን አቅርበዋል::

ደስታ ተክለወልድ ግጭትን «መግጨት፣መገጨት.ድንገተኛ ጥል፣ሰለተ ጠብ፣» (1962፣249) በማለት ይፈቱታል:: የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል መዝገበ ቃላት ደግሞ « 1.ጥል፣ 2. አንድ ተሽከርካሪ ሌላን ተሽከርካሪ ወይም ሰውን፣ እንስሳትን፣ ... በመግጨቱ የተነሳ የተፈጠረ አደጋ» (1993፣ 261) በማለት ይገልጻል:: ኢፍሬም እሰፋ አዲሱ የአማርኛ መዝገበ ቃላት በተሰኘው መጽሐፉ ግጭትን «ድንገተኛ ጥል፣መግጨት፣ (1992፣261) ብሎታል እክስፎርድ አድቫንስድ ድክሽነሪ በበኩሉ ግጭትን ካለመስማማት ጋር በማያያዝ አገሮች፣ህዝቦች፣ድርጅቶች የሚያሳዩት አለመጣጣም(239) እንደሆነ ይገልጻል::

## 3.2 የግጭት ትውራዊ ቅኝት

ግጭትን አስመልክቶ በርካታ ምሁራን ብዙ ሀሳቦችን ሰንዝረዋል Coser (1970:20) ግጭት ከዝቅተኛ የአስተሳሰብ ደረጃ ተላቀን ለተሻለ አስተሳሰብ እንድንዘጋጅ የልማት ተጠቃሚ እንድንሆንና መልካም ነገርን የመፍጠር ችሎታ እንዲኖረን የማድረግ ኃይል አለው ይላል:: ማንኛውም ህብረተሰብ ደግሞ በለውጥ ሂደት የሚሳተፈውና የተሻለ የአስተሳሰብ ባለቤት የሚሆነው በውስጡ ባለ ግጭቶች አነሳሽነት ነው:: Coser (1970፣25) እንደገለፀው ያለ ግጭት የሚኖር ወይም ግጭት አልባ ሆኖ የኖረ የማህበረሰብ አካል አለ ማለት አይቻልም:: የግጭት መኖር ደግሞ የማህበረሰቡ መገለጫና የዕድገት ምልክት ነው:: ስለዚህ ህብረተሰብ የሚያድገውና ለውጥም የሚያመጣው በውስጡ ባሉ ግጭቶች መንስኤ ሰበብ ነው::

Fisher(1982:567) ግጭት ሁለት ሊስማሙ የማይችሉ የተለያዩ ዓላማና ተግባር ባላቸው ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ግለሰቦች ቡድኖችና ድርጅቶች መካከል የሚፈጠር ማህበራዊ ክስተት ሆኖ አንዱ በሌላው ላይ የበላይ ለመሆን ጥረት የሚያደርግበት ሁኔታ መሆኑን ይገልፃል:: ይህም የሚያመለክተው አንዱ ቡድን ወይም ወገን የራሱን ሃሳብ በሌላው ላይ በኀይል ለመጫን ሲሞክር፣ ሌላው ወገን ደግሞ ጥቅምና መብቱን ለማስከበር ሲል ግጭትን እንደማሸነፊያ አማራጭ አድርጎ ይነሳል:: Bliss (2002) ግጭትን ከሰዋዊ ፍላጎት፣ግንኙነቶች፣ፖለቲካ፣ከለውጥ አስተሳሰብ ወይም ፍላጎቶች ወዘተ ባላቸው ክፍሎች መካከል በልዩ ልዩ ማህበራዊ ግንኙነቶች ላይ በተለያዩ መልዕክቶች ይከሰታል ሲል Deng (1991፣299) ደግሞ ግጭት በማህበራዊ ግንኙነቶች ውስጥ የማይቀር ክስተት እንደሆነ ይገልጻል:: ግጭት ሁለት የተለያየ ፍላጎት ባላቸው ቡድኖች መካከል ይፈጠራል:: ይህም በአካባቢ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችን በብቸኝነት ለመቆጣጠር የአካባቢውን ጥሬ ሀብት በበላይነት ወይም በብቸኝነት ለመጠቀም ከሚመነጭ ግላዊ ወይም ቡድናዊ አመለካከት የሚመጣ ነው:: ሌላው ስልጣንን የአንድ ወገን መጠቀሚያ አድርጎ ሌሎችን የማግለል ሁኔታ ሲከሰት ግጭት ይፈጠራል:: በተጨማሪም አንዱ ወገን የሌላውኝ ማንነት አለማክበር፣አመለካከቱን አለመቀበል፣ በእግባቡና ፍትሀዊ በሆነ መንገድ አለማየት ... ሰዎችን ወደ ግጭት እንዲገቡ የሚገፋፉ ናቸው::

### 3.3 የግጭት መንስኤዎች

ለግጭት መቀስቀስ መንስኤ ወይም ቀስቃሽ የሚሆኑ በርካታ ምክንያቶች አሉ:: እነዚህን ምክንያቶች በርካታ ምሁራን በጥናታዊ ጽሑፋቸው ገልጸዋቸዋል:: የሁሉም ሀሳብ በአጠቃላይ ሲታይ ስነ-ልቦናዊ፣ማህበራዊ፣ፖለቲካዊና ባህላዊ ገፅታዎች መሆናቸውን ያመለክታል:: የግጭት ዓይነቶች ዋና ዋናዎቹ በሦስት እንደሚከፈሉ Kreidler(1984) ገልጿል:: እነሱም:-

#### 3.3.1 የሀብት ክፍፍል

ይህ ግጭት ከተጠቃሚዎች ፍላጎት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ አቅርቦት በሌለበት ወቅት (የመሬት፣የውሃ፣የገንዘብ) ሁለት ወይም ከዚያ በኋላ የሆኑ ሰዎች የአቅርቦት እጥረት ያለባቸውን ነገሮች ለማግኘት የሚከሰት የግጭት አይነት ነው:: ሰዎች መሠረታዊ መብታቸው ጥቅማቸውና ፍላጎታቸው ሳይሟላ ሲቀር የጎደለውን ነገር ለማግኘት ሲፈልጉ የሚፈጠር ግጭት ነው:: የሰው ልጅ ለአካላዊ፣ ስነ-ልቦናዊና ማህበራዊ መሠረታዊ ፍላጎቶቹ ካልተሟሉና ትኩረት የማይሰጣቸው ከሆነ ግጭትን ሊቀሰቅሱና ወደ ብጥብጥ ሊያመሩ እንደሚችሉ የሚያመለክት ነው::

### 3.3.2 የፍላጎት አለመጣጣም

አንድ ነገር የማድረግ ወይም የማግኘት (ስልጣን፣ዕድገት፣ለውጥ ...) ጽኑ ፍላጎት ኖሮ የተፈለገው ነገር በሌላ አካል ሲያዝና ትኩረት ሲነፈግ የፍላጎት መጣረስ በሚኖርበት ወቅት የሚፈጠር ግጭት ነው፡፡ በሌላ በኩል ፍትሐዊነት የሌለው የፖለቲካ መዋቅር፣ህጋዊ ሰውነትና የህዝብ አመኔታ የሌለው አገዛዝ፣ ደካማ አስተዳደርና ሥርዓት አልበኝነት የሰፈነበት ወይም መልካም አስተዳደር የሌለው አሠራርን መከተል ግጭትን ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡

### 3.3.3 የእሴቶች ግጭት

በአንድ ማህበረሰብ እምነቶች ባህሎች እሴቶች አመለካከቶች በውስጥም ይሁን በባዕድ አካላት ሲጣስ የሚፈጠር ግጭት ነው በብሔርተኝነት፣በዘረኝነትና በጎሰኝነት ምክንያቶች አንደኛው ወገን ሌላውን ወገን ከማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊና ሌሎችም ነገሮች ዙሪያ የመብት መነፈግና የማግለል ሁኔታ ሲከሰት የሚመጣ ግጭት ነው፡፡ ይህም በበቀል፣ በጥላቻና በጦርነት ላይ ስለሚያተኩር በዓለማችን ላይ ለሚደርሱት የንብረትና የሰው ልጅ እልቂት ምክንያት የሚሆን ነው፡፡ ይህ የግጭት ዓይነት ውስብስብ በመሆኑ በቀላሉ እልባት ለመስጠትም ሆነ ለመቆጣጠር የሚያስቸግር ነው፡፡

ግጭትን ሁልጊዜ በአፍራሽ ገፅታው ከመፈረጅና የማህበረሰብን ወግ፣ ልማድና ደንብ የሚጥስ እንደሆን አድርጎ ከማየት ይልቅ ሊስተካከሉና ሊታረሙ የሚገባቸውን የማህበረሰብ ልማዳዊ ሥርዓቶች ለማስተካከልና በተሻለ መንገድ ሊመራ የሚችል መሣሪያ መሆኑን ማወቅ ተገቢ ነው፡፡ ማንኛውም ማህበረሰብ የሚመራበትና የሚተዳደርበት ልማዳዊ ደንብና ህግ ይሆነኝ ብሎ የፈጠረው በውስጡ ከያዛቸው ተቃርኖዎች አንጻር መሆን እንዳለበት David Riches(1986፣68)ገልጿል፡፡ግጭት ለለውጥ ፣ ለዕድገት ፣ ለአዳዲስ አስተሳሰቦችና አሠራሮች መፈጠር ምክንያት ሲሆን አዎንታዊ ጎኑ የጎላ ይሆናል፡፡ የማህበራዊ ሳይንስ ምሁራን ማህበረሰባዊ ግጭት የግለሰባዊ ግጭቶች ድምር ውጤት እንደሆነ ይስማማሉ፡፡ ስለዚህ ግጭት በተፈጥሮው ከቀላል ወደ ከባድና ውስብስብ ወደ ሆነ ደረጃ ማደግ እንደሚችል ያመለክታል፡፡ በመሆኑም በልዩ ልዩ ማህበራዊ ግንኙነቶች ላይ በልዩ ልዩ መልኩ የሚከሰቱ ግጭቶች እንደየባህሪያቸውና ደረጃቸው ለማቃለል የሚያስችሉ ተገቢነት ያላቸው የግጭት ማስወገጃ ዘዴዎችን ይፈልጋሉ፡፡ በሌላ መልኩ ሲታይ ግጭት ወደ ባሰ ደረጃ ተሸጋግሮ ከፍተኛ ብጥብጥ ሲያስከትል በህዝብና በሀብት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደርስና በዕድገትና በለውጥ ሂደት ላይ መሰናክል ይፈጥራል፡፡ ይህም የግጭት አሉታዊ ገጽታ የሚታይበት ነው፡፡

Deutch (1973፡17) ግጭትን ገንቢና አፍራሽ በማለት መድቦ ግጭት ገንቢ የሚሆነው የግጭቱ ተሳታፊዎች በውጤቱ ሲረኩና በግጭቱም ምክንያት ያጡት ነገር የሌለ መሆኑን ሲረዱ ነው፡፡

በተቃራኒው ደግሞ የግጭት አፍራሽ ጎን የሚታወቀው የግጭቱ ተሳታፊዎች በውጤቱ ሳይረኩ ቀርተው በተከሰተው ግጭት ያገኙት ነገር እንደሌላ በተሰማቸው ጊዜ እንደሆነ ይገልፃል:: ግጭት በአፍራሽ መልኩ ተከስቶ በጥፋት ሊጠናቀቅ እንደሚችል የሚገልጹ ምሁራን የመኖራቸውን ያህል በአንጻሩ በገንቢ መልኩ ተከስቶ በጥሩ ውጤት መጠናቀቅ እንደሚችል የሚገልጹ አሉ:: ( pelton1974፣katz and lawyer 1985)::

ከላይ የተገለጹትን ሀሳቦች መሠረት በማድረግ ግጭትን ጠቅለል አድርገን ስንመለከተው በየትኛው ም ማህበረሰብ ውስጥ የሚነሱ ግጭቶች በዋነኛነት መፍትሔ ሊያገኙ የሚችሉት በዚያው በማህበረሰቡ ነው:: ምክንያቱም ግጭት በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ ግለሰቦች፣ ቡድኖች፣ ተቋማት፣ አገራት .... በሚያደርጓቸው ግንኙነቶች ላይ በመካከላቸው በሚፈጠሩ ያልተጣጠሙ አመለካከቶች፣ ፍላጎቶች፣ ስሜቶች፣ፍትሀዊነት የጎደላቸው የሀብትና የስልጣን ክፍፍሎች ወዘተ ሲንፀባረቁ አንዱ በሌላው ላይ የሚፈጥረው ትራኔ ወይም አለመስማማት ስለሆነ ነው::

## 3.4 የግጭት አፈታት ዘዴዎች

### 3.4.1 በዓለም አቀፍ

የማህባራዊ ህይወት አንዱ ገጽታ የሆነው ግጭት በበርካታ አነሳሽ ምክንያቶች እንደመፈጠሩ የተለያዩ የአቀራረብ ስልት ባላቸው የግጭት መፍቻ ዘዴዎች ሲረጋጋ፣ ሲፈታና ሲወገድ ይታያል:: ግጭት የሚፈታባቸው ስልቶችም ስለ ስኬቱና ለአፍራሽነቱ የየራሳቸው አስተዋዕኦ አላቸው:: የግጭት መፍታት ዋና ዓላማ በግጭት ውስጥ በገቡ አካላት መካከል የተፈጠረውን አለማግባባት በማስወገድ ተቋርጦ የነበረውን ግንኙነት ወደ ሰላማዊ መንገድ መመለስ ነው:: ስለሆነም የግጭት አፈታት ሥርዓት ግጭትን በመከላከልና ሰለምን ፈጥሮ ልማትን ለማምጣት የሚያስችል ዘላቂነት ያለው ሂደት መሆኑን የመስኩ ባለሙያዎች ይናገራሉ:: በመሆኑም ግጭትን ለመፍታት በየደረጃ የተቋቋሙ የግጭት አስወጋጅ አካላት ህግና ሥርዓት አበጅተው እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ::

በአለም አቀፍ ደረጃ ግጭትን ለመፍታት ኃላፊነት ያለበት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሥር የተደራጀው የፀጥታው ምክር ቤት ነው:: ኃላፊነቱም በአለም ላይ የሚከሰቱ ግጭቶችን መቆጣጠርና ማስወገድ ነው:: ድርጅቱ በአባል ሀገራት መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶችን ለመፍታት አራት አይነት የአፈጻፀም ሥርዓቶች አሉት:: እነዚህን ሥርዓቶች የተባበሩት መንግሥታት በጃንዋሪ 14,2003 ባካሄደው ጉባኤ ማጠቃለያ ላይ በወጣው የ(2002) Round up በሚለው ሰነዱ የሰፈሩት የመፍትሔ አቅጣጫዎች:

ሀ. የተባበሩት መንግስታት መልዕክተኛ ቡድን ግጭት በተከሰተበት ሀገር ማቋቋም

ለ. ግጭት በተነሳበት ሀገር ውስጥ የተኩስ አቁም ስምምነትን የሚቆጣጠር ጦር ማሠማራት

ሐ. ግጭት በተፈጠረበት ሀገር ጊዜዊ ፍ/ቤት ማቋቋም

መ. በአለም አቀፍ ፍርድ ቤት ችሎት ፍትህ ለመስጠት መሞከር ለምሳሌ በኔዘርላንድ ያለው (ICC) የሚሉ ናቸው፡፡

የተባበሩት መንግሥታት መልዕክተኛ ቡድኖች በሀገራት መካከል የተከሰቱ ግጭቶችን ለመቆጣጠር በጆርጂያ፣በሲኒያ ሄርዚጎቪና፣ላይቤሪያ፣ ኮንጎ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ፣ ማዕከላዊ አፍሪካ ሪፐብሊክ፣ አንጎላ፣ሴራሊዮን፣አፍጋኒስታን፣ ኤርትራና ኢትዮጵያ ውስጥ ተሰማርቶ ለነበረው ግጭት መልዕክተኛ ቡድን ልኳል፡፡ እንዲሁም ግጭትን ለማስወገድ በማለት በፀጥታው ምክር ቤት ትዕዛዝ ግጭት በተከሰተበት ሀገር የጦር ሰራዊት ሲሰማራ ቢታይም እስካሁን እንደታየው ሠራዊቱ በቦታው የሚደርሰው ብዙ ህዝብ አልቆ አያሌ ንብረት ከወደመ በኋላ በመሆኑ ጠቀሜታው ዝቅተኛ መሆኑ ይነገራል፡፡ ሌላው የፀጥታው ምክር ቤት ግጭት በተከሰተበት ሀገር የጊዜያዊ ፍርድ ቤት በማቋቋም የሚከተለው የዳኝነት ሥርዓት የዳኞች አመራረጥና ምልመላ ከየሀገሮቹ ልማዳዊ ፍትህ አሠራር ጋር ስለማይጣጣም ውጤቱ አጥጋቢ ሲሆን አይታይም፡፡ አለም አቀፍ ፍርድ ቤት አቋቁሞ ግጭት በተፈጠረባቸው አገሮች ውስጥ ጥፋተኛ የሆኑ ድርጅቶችንና ግለሰቦችን ለመዳኘት የታየው አሠራርም አመርቂ አይደለም፡፡

(Simma 1995) እንደገለፀው በተባበሩት መንግሥታት የሚሰራባቸው የግጭት ማስወገጃ ዘዴዎች የተፈለገውን ሰላም ለማምጣትና በዘላቂነት ግጭትን ለመቆጣጠርና ለማስወገድ ያልቻሉበት ምክንያት የግጭትን ምንጮች በወጉ ካለመመርመር፣ በግጭቱ የሚሳተፍ ህዝቦች የሚያነሷቸውን ችግሮች ከባለ ጉዳዮቹ ከማረጋገጥ ይልቅ የመሪዎችንና የቡድኖችን ማዳመጥ፣ በተኛውም ቦታ የተነሱ ግጭቶች በዓለም አቀፍ መፍትሔ ያገኛሉ ብሎ ማሰብ በእያንዳንዱ ሀገር ያለውን ልማዳዊ ሥርዓት መርምሮ ዕውቅና ያለመስጠትና በማህበረሰብ ደረጃ እንዲፈቱ ያለማመቻቸት፣ ግጭት ሲፈጠር መፍትሔ ለማፈላለግ ከመሯሯጥ ይልቅ ግጭት እንዳይከሰት ትኩረት መከላከል ላይ ያለማተኮርና በሁሉም ሀገር የሚከሰቱ ግጭቶች የሚዳኙት በአንድ ዓይነት መሆናቸው በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

ግጭትን ለመፍታት የሚያስችሉ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች ባህላዊና ዘመናዊ በመባል የሚታወቁ የህግ ሥርዓቶች አሉ፡፡ በሁሉም ዘዴ ተጠቅሞ ግጭትን ለመፍታት ስለግጭቱ ምንነት፣ባህሪይና ደረጃ ማወቅ ተገቢ ነው፡፡ ግጭቱን በቅድሚያ መመርመርና ለይቶ ማወቅ የግጭት መፍቻ አንዱ ስልት ነው፡፡ በተለያዩ አካባቢዎች የሚነሱ ግጭቶች እንደየማህበረሰቡ አኗኗርና ልማድ

የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እነዚህን ግጭቶች ለመፍታት የሚያስችሉ ዘዴዎችም አለም አቀፋዊና አካባቢያዊ የሆኑ ግላዊና የጋራ ባህሪያት ይታይባቸዋል፡፡

### 3.4.2 በአፍሪካ

በዓለም ውስጥ ከሚገኙት አህጉራት መካከል በርካታ ግጭቶች የሚከሰቱት በአፍሪካ ነው፡፡ በአህጉሪቱ ውስጥ የጎሳዎች የእርስ በርስ ግጭት፣ የድንበር ውዝግብ፣ የስልጣን ሽኩቻ፣ በተፈጥሮ ሀብት ላይ በሚደረግ የሀብት አጠቃቀም እና በመሳሰሉት ግጭቶች በከፍተኛ ደረጃ ይከሰታሉ፡፡ እነዚህም ግጭቶች ለረዥም ጊዜ የነበሩና አሁንም በብዙ የአፍሪካ ሀገሮች የሚታዩ ናቸው፡፡ በመሆኑም የአህጉሪቱ ዕድገት ወደ ኋላ ቀርቷል፡፡ Guy Martinእ.ኤ.አ. በ 1988 የአፍሪካ የግጭት አፈታት በሚል ርዕስ በፃፈው ላይ እንደሚከተለው ገልጿል፡፡ አፍሪካ ብዙ ግጭቶች የተፈጠሩባት አህጉር እንደሆነችና ብዙ ህዝብ እንዳለቀባት አጅግ ዘግናኝና አሰቃቂ ገድያ መፈፀሙን ለአብነትም ከ 1955-1995 በአርባ ዓመታት ውስጥ ከ 7-8 ሚሊዮን ህዝብ እንደሞተባትና ከእነዚህም ውስጥ በ 1994 ዓ.ም የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ የተፈፀመባቸውን ወደ 850,000 የሚደርሱ ሩዋንዳውያንን በመጨመር ነው ይላል፡፡

በአፍሪካ የሚከሰቱ ግጭቶች በአካባቢያቸው ያለውን የተፈጥሮ ሀብት በማውደም የአየር መቀየትን እያባባሱ ህዝቦች ለችግር ለድርቅ እንዲጋለጡ አድርገዋል፡፡ የግጭቶች መባባስ የህዝቡን ማህበራዊ ህይወት በማናጋት ለሞት፣ ለስደትና ለምዕዋት ዳርገዋል፡፡ ይህንን እልቂትና ስቃይ አርግቦ የህዝቡን ሰላም ለማረጋገጥ የተቋቋመው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ነው፡፡ ድርጅቱ በሀገራት መካከል የሚከሰቱ ግጭቶችን ለመፍታት እ.ኤ.አ እስከ 1992 ዓ.ም የሚጠቀመው ስልት

ሀ. በየሀገሩ መሪዎች አማካይነት አህጉራዊ ስብሰባ ማካሄድ

ለ. የሰላም ጉባኤ ማካሄድ

ሐ. ጣልቃ ገብ ጦር ማሠማራት

መ. የግልግል ኮሚቴ ማቋቋም እንደሆነ የአፍሪካን ኢኮኖሚስት በሚለው መጣጥፍ Vol 4 No12 ላይ ተገልጿል፡፡

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በ 1993 ባካሄደው ጉባኤ ግጭቶችን እንዲቆጣጠር MCPMR(Mechanism for Confilict Preventing Management and Resoulution) የተባለ አህጉራዊ ድርጅት መሠረተ፡፡ ነገር ግን ግጭትን ለመፍታት ብዙ የፈየደው ነገር የለም፡፡ በአፍሪካ በተለያዩ ዞኖች የኢኮኖሚና ትብብር ውህደት ለመፍጠር በማለት የተቋቋሙት የአፍሪካ

ህብረት ኢጋዥ ድርጅቶች ECOWAS(Economic Community of West African States) SADC, (South African Development Community) IGAD (Inter Governmental Authority on Development) ን ግጭትን በማስወገድ በኩል እስካሁን አንቱ የሚባል ውጤት አላስገኙም፡፡ ለምሳሌ ECOWAS በላይቤሪያና በሴራሊዮን ለተከሰቱ ግጭቶች መፍትሔ ለመሻት ጦር አሰማርቷል፡፡ IGAD በደቡብ ሱዳን ለተፈጠረው ግጭት መፍትሔ ለማፈላለግ ጥሯል፡፡ SADC በደቡብ አፍሪካ ሰላምን ለማስፈን ተሳትፎ አድርጓል፡፡ እነዚህ የኢኮኖሚ ትብብርና ውህደት መፍጠር አላማ አድርገው የተቋቋሙት ድርጅቶችም ቢሆኑ ግጭቶች ከተከሰቱና ብዙ ህዝብ አልቆ ሀብትና ንብረት ከወደመ በኋላ ለመፍትሔ የሚሯሯጡ ስለሆነና ልክ እንደ አህጉራዊ ድርጅቱ ስብሰባ ጠርቶ ችግሩን ለመፍታት ግጭቱ እየተባባሰ ሲመጣ ሰላም ለማስከበር በሚል ጣልቃ ገብ ጦር ከማሰማራት ያለፈ ሥራ ባለመሥራታቸው ዘላቂ መፍትሔ አልተገኘም፡፡ (Cervenka 1977) በማለት ገልጿል፡፡

በሆነ ደረጃ የተቋቋሙት ድርጅቶችና የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ያቋቋመው MCPMR ለግጭት መቆጣጠርና ማስወገድ ያደረጉት ጥረት ውጤታማ ያልሆነበት ምክንያት የተከሰቱት ግጭቶች መንስኤያቸው ምን እንደሆነ አለማጥናት፣ የግጭቶችን መነሻ ምክያቶች ከየሀገሮቹ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አለማገናዘብ፣ ግጭቶች በሀገሮች ወግና ልማድ መሠረት እንዲፈቱ አለማድረግ፣ ግጭት በጦር ሠራዊት ኃይል ይወገዳል ብሎ ማመንና የግጭቶችን መነሻ ምክንያቶች ከህዝቡ ከመስማት ይልቅ ከሁለተኛ ወገን ወይም የመሪዎችንና የባለስልጣናትን መቀበል የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ይመስሉኛል፡፡

የአፍሪካ ህዝብ ልማዳዊ መርህ እጅግ አስገራሚና ጠቃሚነቱም የሚጎላበት ምክንያት የማህበረሰቡ አባላት በሚከሰቱ ግጭቶች ላይ ግለሰብ፣ ቤተሰብ፣ጎሣና ህብረተሰብ ሳይቀር የጋራ ተሳትፎ በማድረግ በነፃ ውይይትና ግልፅ ንግግር ግጭቶች የወዲያውኑት መፍትሔ እንዲያገኙ ጥረት ማድረጋቸው ነው፡፡ አፍሪካ ውስጥ ያሉ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች በአብዛኛው ከህብረተሰቡ የአኗኗር ሥርዓት፣ ከማህበረ ፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ እውነታዎች ጋር በጥብቅ የተቆራኙና ከህብረተሰቡ ባህልና ታሪክ ጋር ትስስር ያላቸው ናቸው፡፡ ስለሆነም እያንዳንዱ ማህበረሰብ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ የየራሱ የግጭት አፈታት ሥርዓት አለው፡፡ የአፍሪካ ህዝብ በውስጡ የሚከሰቱትን ግጭቶች በባህላዊ መንገድ የመፍታት ልማድ እንዳለውና ባህላዊ ተቋም ዘላቂ መፍትሔን ማምጣት መቻሉን በርካታ ምሁራን በጥናት አረጋግጠዋል፡፡ (Orijiako 2005)

ዐጋ እንዳለው(2002:521) International conference of Ethiopian studeies ላይ conflict resoluation through cultural tolerance. An analysis of the micu Institution in

matakkal በሚል ርዕስ ባቀረበው ጽሑፍ በደቡብ ሱዳን በድንካና በኑየር ህዝቦች መካከል የተፈጠረውን ግጭት ለማቃለል የተቻለው ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓትን በመጠቀም በሀገር ሽማግሌዎችና በሃይማኖት መሪዎች እንሳሆነ ጠቅሷል::

ባህላዊ የግጭት አፈታቱም በሁለቱም ወገኖች መካከል የተፈጠረውን አለመግባባት አስወግደው በሰላም ተግባብተውና ተባብረው እንዲኖሩ አስችሏል ብሏል በሁለተኛ ደረጃ ፀጋ በዚሁ ጽሑፉ በኡጋንዳ በ1970 በኢድአሚን ዘመን መንግሥት የ"Acholi" ጎሳዎች በ"west Nile" ህዝቦች መገፋታቸውንና መጨቆናቸውን ምክንያት በማድረግ ለተፈጠረው ግጭት መፍትሔ የተገኘውና ግጭቱ ተወግዶ በሰላም ተግባብተው እንዲኖሩ የተደረገው በባህላዊ መንገድ ባቋቋሙት "Mato oput" በሚለው ባህላዊ የግጭት መፍቻ ሥነ-ሥርዓት እንደሆነ ገልጿል:: ባህላዊ ተቋሙ ማህበረሰቡ ባህላዊ መቻቻልን ተጠቅሞ ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን እንዲችል ረድቶታል::

የአፍሪካ ህዝብ ባህሉን እጅግ ያከብራል:: ባህላዊ ተሳትፎው ከጥልቅ ስሜት ከከፍተኛ ፍቅርና ከልባዊ ቀረቤታ የሚመነጭ ነው ይህም ባህላዊ ተነሳሽነትና ውስጣዊ ስሜት ለሚፈጥሩ ግጭቶች መፍትሔ ለማፈላለግ ከፍተኛ ሚና አለው:: ህዝቡ ቤተሰባዊ ቀረቤታውና ማህበረሰባዊ ትስስሩ/ ግንኙነቱ/ በአስተማማኝነት የሚከበር በጥንካሬው ዘላቂ ሆኖ የሚቀጥል ነው በማለት Utne(2001፣8/ ይናገራል::

እስማኤል ኢማ (2001፣46-52) በሶማሌ ላንድ በመሬት ባለቤትነት፤ በስልጣን ጥማትና ስግብግብነት፣የግጦሽና የውሃ መሬቶችን ለመያዝ በመፍጨርጨር፤ ሴቶችን አስገድዶ በማግባት፣ በጐሣ ልዩነቶች፣ በስድብ፣ በጥላቻና በባህላዊ እምነቶች አለመከበርና በሌሎች ምክንያቶች ግጭት በመፈጠሩ ለንብረት መውደምና ለህዝብ እልቂት መባባስ ምክንያት ሆኗል:: ይህንን ጥፋት የሚያስከትልና ወደ ባሰ ብጥብጥ የሚያመራ ግጭት የሶማሌ ህዝብ ዝም ብሎ አልተመለከተም:: በማህበረሰቡ ወግና ልማድ መሠረት በተቋቋሙት ባህላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች በመጠቀም ግጭቶችን አስወግደዋል:: የግጭቶችን ባህሪይ በመመርመር በሦስተኛ ወገን እርቅ በማድረግ፣ በገላገል በሽምግልናና ምስክሮችን በማቅረብ ከሁለቱም ወገን በተወከሉ የአገር ሽማግሌዎችና ገለልተኛ በሆኑ ሰዎች አማካይነት ግጭቶች እንዲወገዱ አድርገዋል:: በ 1991 እ.ኤ.አ. የሶማሌ መንግሥት ሲወድቅ የሱማሌ ላንድ ባህላዊ መሪዎች፤ ሽማግሌዎችና የኃይማኖት መሪዎች ቢገፉ ሆነው በሀገሪቱ የተከሰተውን የማዕከላዊ መንግሥት ስልጣን ክፍተት በመሸፈን የማረጋጋት ሥራ መሥራታቸውን ይገልፃል::

Utne (2001፣3-5) ባቀረበው ጽሑፍ በኡጋንዳና በሱዳን ህዝቦች መካከል በ "Kidepo" ወንዝ ምክንያት ከፍተኛ ግጭት ተፈጥሮ ሀብትና ንብረት ወድሟል:: ብዙ ሰውም ሞቷል:: የግጭቱ

መንስኤ በ "kidepo" ወንዝ የግጦሽና የውሃ አጠቃቀም ላይ ነው:: በወንዙ አካባቢ የሚኖሩ ህዝቦች ኑሮአቸው የተመሰረተው በከብት እርባታ ላይ ነው:: ስለዚህ ማህበረሰቡ ከብቶችን ከማንኛውም ሀብትና ንብረት በተለየ መልኩ ይመለከታቸዋል:: ይመካባቸዋል:: ልዩ ጥበቃና እንክብካቤ ያደርግላቸዋል:: ከሀብትነት በተጨማሪ መለኮታዊ ስጦታዎች እንደሆኑም አድረገው ይቆጥራሉ ስለዚህ ከብት በጣም ውድና አስፈላጊ ስለሆነ በጎሳዎች መካከል የከብት ስርቆት የሚዘወተር ነው:: ይህ ዘወትር የሚከናወን ስርቆት በሁለቱ ጎሳዎች መካከል ግጭትን ያስከትላል:: በከብት ዝርፊያ ሳቢያ በተነሱ ግጭቶች ምክንያት የሞቱ ሰዎችን ደም ለመበቀል በሚደረግ ግድያ ግጭቱን አባብሶ የከፋ ያደርገዋል:: የሁኔታውን አሳሳቢነት የተገነዘቡት የአካባቢ ነዋሪዎች በባህላቸው ህግና ሥርዓት መሠረት ከሁለቱም ወገን ሽማግሌዎችን በመምረጥ የግጭቱን መሠረታዊ ምክንያት በማጣራት በወጉ ከለዩ በኋላ ከማህበረሰቡ በመለየት ወደ ጫካ በመሄድ ለተወሰኑ ቀናት ተሰባስበው ይመክራሉ:: ነገሩን በአንክሮ በመመልከት ለረዥም ጊዜ ሲሰሩበት ባህላዊ የሽምግልና ኃይማኖታዊና ፎክሎራዊ ክንዋኔዎችን በመጠቀም የማርገብ ወይም የማስወገድ ሥራ ያከናውናሉ:: በእርቅ ስነ-ስርዓቱ ላይ የተመረጡ ከብቶች ወይም ፍየሎች ይታረዳሉ የመታረዱ ፋይዳም ግጭት እንዲፈጠር የሚያደርጉት እርኩስ መናፍስትን ለማስወገድ እንደሆነ በማሰብ ነው::

ከላይ የተገለጹት በአፍሪካ አህጉር በተለያዩ አካባቢዎች የታዩት ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች በመንግሥት ጥረትና በዘመናዊ የጦር መሳሪያ ሊፈቱ ያልቻሉ ነገር ግን በባህላዊ የግጭት ማስወገጃ ተቋማት እልባት ያገኙ ናቸው:: ስለዚህ ባህላዊ ተቋሞች ግጭት ለመፍታት ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው ማለት ይቻላል:: በአፍሪካ ውስጥ በሀገር ሽማግሌዎች በጎሣ መሪዎችና በባህላዊ ዳኞች የእርቅ ስነ-ሥርዓቶች እንደሚከናወኑ በርካታ ምሁራን በጥናታቸው አረጋግጠዋል:: ደማለኝ (2005:5)

### 3.4.3 በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ ግጭትን ለማስወገድ የሚያገለግሉ ባህላዊና ዘመናዊ የህግ ሥርዓቶች አሉ:: ዘመናዊ የግጭት አፈታት የሚከናወነው በፍትህ አካላት አማካይነት ነው:: ይህም ህገ-መንግስቱን መሠረት ያደረገ ነው:: የሀገሪቱ የፍትህ አካላት የሚጠቀሙበት የወንጀለኛ መቅጫ ህግና የፍትሐብሔር ህጎች መሠረታቸው ይኸው ህገ-መንግሥቱ ነው:: ዘመናዊ የግጭት አፈታት በኢትዮጵያ ከ15ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እንደሚሠራበት የሚጠቁሙ መረጃዎች አሉ:: በ15ኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ ወደ ግዕዝ ቋንቋ ተተርጉሞ ወደ ሀገራችን የገባው የሮማ ህግ ነበር:: (አምሳሉ 1976:63-65) በ1923 የነበረውና በ1948 ተሻሽሎ የመጣው የኢትዮጵያ ህገ-መንግስት ዘመናዊነት ላይ የሚያተኩርና የንጉሱን የአገዛዝ ስርዓት ለማስጠበቅ የተደነገገ ነበር::

በደርግ ዘመን በ1980 የተቋቋመው የኢትጵያ ህገ-መንግሥት ዘመናዊና ከቀደምቶቹ በተሻለ ሁኔታ ቢዘጋጅም በድንጋጌው ባህላዊ እሴቶችን ያላካተተ ነበር:: እንዳውም ብዙ ባህላዊ እሴቶች እንዲዳከሙ አሊያም ጨርሰው እንዲጠፉ አድርጓል:: ቀጥሎ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግሥት በ 1987 የወጣውና አሁን በሥራ ላይ ውሎ የምንጠቀምበት ነው:: እነዚህ ከላይ የቀረቡትየዘመናዊ ሕግ ሥርዓት ሰነዶች ናቸው::

ኢትዮጵያ ነፃነቷን አስከብራ የቆየች ሀገር ናት በነጻነቷና በጥንታዊነቷ የእሷነቷን አሻራ የሚያረጋግጡ ጥሩ ጥሩ ባህላዊ እሴቶች አሏት:: ግጭቶች በግለሰብ በቡድን፣በጎሳና በህብረተሰብ ደረጃ ሲፈጠሩ በጎሳ መሪዎች፣ በሀገር ሽማግሌዎችና ማህበረሰቡ ባቋቋማቸው ባህላዊና ልማዳዊ ሥርዓቶች አማካይነት ይፈታሉ:: ይህ ማህበረሰባዊ ክንውን ከጥንት ጀምሮ እስካሁን እየተሰራበት ነው:: በሌላ በኩል ዘመናዊ የህግ ሠነዶች ለባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓቶች የሰጡትን አሊያም የነፈጉትን ትኩረት ለማየት በ 1987 ዓ.ም በፀደቀው ህገ-መንግሥት ውስጥ የሠፈሩትን ሃሳቦች እንመልከት

- አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀፅ 1 ህገ-መንግስቱ የሀገሪቱ የበላይ ህግ ነው:: ማንኛውም ህግ፣ልማዳዊ አሠራር፣እንዲሁም የመንግሥት አካል ወይም የባለ ስልጣን ውሳኔ ከዚህ ህገ መንግስት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት አይኖረውም::

- አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 5 ደግሞ ይህ ህገ መንግሥት የግልና የቤተሰብ ህግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሃይማኖት ወይም በባህሎች መሠረት መዳኘትን አይከለክልም::

- አንቀጽ 78 ንዑስ አንቀጽ 5 የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የክልል ምክር ቤቶች በአንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት ኃይማኖትና የባህል ፍርድ ቤቶችን ሊያቋቁሙ ወይም ዕውቅና ሊሰጡ ይችላሉ::

- አንቀጽ 79 ንዑስ አንቀጽ 1 በፌደራልም ሆነ በክልል የዳኝነት ስልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ ነው::

- አንቀጽ 91 ንዑስ አንቀጽ 1 መንግሥት መሠረታዊ መብቶችንና ሰብዓዊ ክብርን፣ዴሞክራሲንና ህገ-መንግሥቱን እንዲያድጉ የመርዳት ኃላፊነት አለበት የሚሉት በነጋሪት ጋዜጣ ቁር 1 1987 ላይ በተለያዩ ገጾች ተገልፀዋል:: በተጠቀሱት አንቀጾች ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ተቀባይነት አግኝቶ የሚሠራበት ሁኔታ በግልፅ አልሰፈረም:: እንዲያውም አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀፅ 1 ልማዳዊ አሰራሮች የመንግሥትን ህግ ካልተከተሉ ተቀባይነት የላቸውም ይላል:: ሌሎችም አንቀጾች ቢሆኑ ለባህላዊ ተቋማት ግልፅና ጥርት ያለ ሀሳብ የላቸውም::

በህዝብ መካከል የሚቀሰቀሱ ግጭቶችን በማርገብና በማስወገድከፍተኛ ሚና የሚጫወቱት ባህላዊ ህጎች በዘመናዊ የህግ ሰነዶች ውስጥ ትኩረት አልተሰጣቸውም:: በሌላ መልኩ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች በአፍሪካና በኢትጵያ ግጭትን የማቃለል ተግባራቸው ከፍተኛ እንደሆነ ምሁራን በጥናት የተደገፈ መረጃ አቅርበው ገልፀዋል ለአብነትም (Yacob 2001):: የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታና የህዝቡን ባህልና ስሜት የሚረዱ የሀገሪቱ የህግ ባለሙያዎችና ምሁራን ስለባህላዊ የህግ ሥርዓቶች አስፈላጊነትና ጥቅም የሚያቀርቡትን ሀሳብ መቀበልና በዘመናዊ የህግ ሥርዓት ሰነድ ውስጥ ማጠቃለሉ ጠቀሜታው የጎላ ነው::

ዘመናዊ ህጎች በሀገሪቱ ውስጥ ለሚከሰቱ ግጭቶች መፍትሔ ለመስጠት ጥረት ሲያደርጉ ይታያል:: ጥያቄው ግን ዘላቂ መሆኑ መፍትሔ የማምጣቱ ጉዳይ ምን ያል ስር የያዘ ነው የሚለው ነው:: ግጭቶች ዘላቂ መፍትሔ አግኝተው ህብረተሰቡ በሰላም እንዲኖር በልማት ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆን ከዘመናዊ የህግ ሰነዶች ጎን በባህላዊ መንገድ የሚከናወኑት የግጭት መፍቻ ዘዴዎች አወንታዊ አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል::

በኢትጵያ ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች ግጭቶች ቢከሰቱም ወደ ባሰ ብጥብጥና ጥፋት እንዳያመሩ በማህበረሰቡ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ሥርዓት ሲረግቡ፣ ሲቃለሉና ሲወገዱ ቆይተዋል:: አሁንም በተግባር እየተሠራባቸው ነው:: ባህላዊ የግጭት አፈታት በኢትጵያ በተለያዩ አካባቢዎች መከናወናቸውን የሚገልጹ ጥናታዊ ጽሑፎች አሉ:: ለአብነት የሚከተሉትን እንመለከታለን::

ያቆብ አርሲኖ(2001) በኦሮሚያ ክልል ቦረና አካባቢ በቢጋ ወራት በቻልቢ የግጦሽ መሬት ምክንያት በቦረናና በጉጂ፣ በቦረናና ሶማሌ፣ በቦረናና ሀመር፣ በቦረናና አርቦሬ ጎሳዎች መካከል ከፍተኛ ግጭት እየተፈጠረ ንብረት ይዘረፋል:: የሠው ሕይወትም ይጠፋል:: ይህን አልቂት የሚያስከትል ግጭት በየጎሳዎች ወኪሎች አማካይነት በባህላዊ የግጭት ማስወገጃ ሥርዓት ተጠቅመው ሰላም በመፍጠሩ የቻልቢን ወንዝ በጋራ እየተጠቀሙ ነው:: ይኸው ፀሐፊ እንደገለጹት በከረዩና በኢቱ ጎሳዎች መካከል በተፈጠረው የድንበር ግጭት በአርሲ ጃርሶታ /ሽማግሌዎች/ አማካይነት የእርቅ ሥነ-ሥርዓት ተፈፅሞ በጋራ እንዲጠቀሙና ሰላም እንዲፈጠር መደረጉን አመለከቷል::

ተስመወርቅ ታፈረ (2002:883) International Conference of Ethiopian Studiesላይ "Inter and Intra-Ethinic conflict and indigenous instituations of conflict resolution among the Abala Afar of North Eastern Ethiopia" በሚል ርዕስ ባቀረበው ጽሑፍ በአባላ አፋርና በትግሬዎች መካከል ወረራን አስመልክቶ የሚፈጠርን ግጭት ለመፍታት

ሁለቱም ወገኖች የሚያምኑበትና የሚጠቀሙበት "Gereb" የሚባል ባህላዊ ተቋም አላቸው፡፡ ባህላዊ ተቋሙ ሁለቱም ወገኖች የሚዳኙበት ስለሆነ ለሚከሰቱ ግጭቶች ፍቱን የሆነ ዘላቂ መፍትሔ እንደሚያመጣ ገልጿል፡፡

ስዩም እና ያቆብ (2003፣43) በአፋርና ኢሳ ጎሳዎች መካከል ግጭቶች ሲፈጠሩ ግጭቶችን ለማስወገድ የሚጠቀሙበት ሥርዓት አላቸው፡፡ ይህም ሄራ ነው፡፡ ሄራ በሁለቱም ጎሳዎች መካከል ለሚከሰቱ ግጭቶች መፍትሔ የሚያስጥ ነው፡፡ ነገር ግን ግጭቱ ተባብሶ ወደ ብጥብጥና ሁከት ሲያመራና "በሄራ" ለመፍታት ሳይችል ሲቀር የሁለቱም ጎሳ ሄራዎች የመንግስት ጣልቃ-ገብነት እንዲኖር ያደርጋሉ በማለት ገልጿል፡፡

ቢጋ (በ 2002፣533) በጥናታዊ ጽሑፉ እንዳሰፈረው የመተከል አውራጃ በጣም ለምለምና በተፈጥሮ የታደለች አካባቢ ናት፡፡ በዚህ አካባቢ የጉምዝ ብሔረሰቦች ቀደምት ነዋሪዎች ናቸው፡፡ በመተከል ልምላሜና የተፈጥሮ ሀብት የተሳቡት የኦሮሞ፣የአገውና የአማራ ብሔረሰቦች ወደዚህ አካባቢ መስፈር ይጀምራሉ፡፡በዚህም ምክንያት በነባሮችና በመጤዎች መካከል ግጭት ይፈጠራል፡፡ በተለይ ቀድመው ወደ ክልሉ በሄዱት ኦሮሞዎችና በጉምዞች መካከል ከፍተኛ ግጭት እየተከሰተ ንብረት ይወድማል፡፡ የሠው ህይወትም ይጠፋል፡፡ የግጭቱ መባባስ የሚያስከትለውን ጥፋት የሁለቱም ጎሳዎች ሽማግሌዎች በመገናኘት በጉዳዩ ላይ ተወያዩበት፡፡ በዚ ጊዜ ወስደው ከተመካከሩ በኋላ በሁለቱም ወገን ተቀባይነት ያለው ሊያግባባቸው የሚችል "Micu" የሚባል ባህላዊ የግጭት መፍቻ ሥርዓት አቋቋሙ፡፡ በ "Micu"ባህላዊ ሥርዓት መሠረት እርቅ ወረደ፡፡ የሁለቱም ጎሳዎች የጋራ ችግሮችን በጋራ ሆነው ለመፍታት ተስማምተው በፍቅር መኖር ጀመሩ፡፡ ከዚያም በተለያዩ ጊዜያት ወደ ክልሉ የሄዱት የአገውና የአማራ ብሔረሰቦች ከነባሩ ብሔረሰብ ጋር ግጭት ሲፈጠር በ"Micu"ሥርዓት መፍታት ተለመደ፡፡ ይህ ተቋም በሁሉም ማህበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት በማግኘቱ ቁልፍ የግጭት ማስወገጃ መገለያ ሆነ፡፡ በንብረት ዘረፋና በግድያ ሲታመሱ የኖሩት ህዝቦች በ "Micu"ሥርዓት በመዳኘት ተግባብተው በሰላም ለመኖር ቻሉ፡፡ የ"Micu"ሥርዓት በጎሳዎች መካከል ለሚከሰቱ ግጭቶች መፍቻ ብቻ ሣይሆን በሁሉም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች ሁሉ ለአካባቢው ህዝብ ባህላዊ መገለያ በመሆን ለትዳሮች ግንኙነት፣ሲጋብቻ ሥርዓት ማስፈፀሚያ፣ ለባህላዊ መቻቻልና የንግድ መረብን ዘርግቶ በጋራ ለመጠቀም የሚያስችል ሥረዓት እንደሆነ በጥናታዊ ጽሑፍ አመልክቷል፡፡

እነዚህ በተለያዩ አካባቢዎች የተከሰቱ ግጭቶች በባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ አማካይነት ዘላቂ መፍትሔ እንዳገኙ ከጥናታዊ ጽሑፎች የተገኘው መረጃ ማረጋገጫ ነው፡፡ባህላዊ ተቋማት በነዓ

ውይይት፣በግልጽ ንግግርና ውጤታማ በሆነ አፈጻፀም በመጠቀም የግጭቶችን መሠረታዊ ባህሪያት እየመረመሩ በድርድር፣ በሽምግልና፣ በእማላጅና በእርቅ ለይቶ በማየት ዘላቂ ሰላምን የማስፈን ብቃት አላቸው። ለስኬታማነቱ ዋናው ጉዳይ ማህበረሰቡ ከልብ የሚደግፈውና የሚቀበለው «ከማህበረሰቡ፤ በማህበረሰቡ፤ ለማህበረሰቡ፤» በመሆኑ ነው። በዚህም ምክንያት ከትርብ አመታት ወዲህ የአንዳንድ አጥኚዎችን ትኩረት ለመሳብ በቅተዋል ለማስረጃም «አበጋር ባህላዊ የግጭት አፈታት በተሁለደሬ ወረዳ» በሚል ርዕስ በሰኔ ወር 1998 ዓ.ም የቀረበውን የጥናት ጽሑፍ መጥቀስ ይቻላል። የንፃነት መኮንን የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ በአምስት ምዕራፎች ተከፍሏል። የጥናቱ ዓላማም በአማራ ብሔራዊ ክልል ደቡብ ወሎ መስተዳደር ዞን በተሁለደሬ ወረዳ በሚኖሩ ህዝቦች ውስጥ ያሉ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት አወቃቀር ምን መልክ እንዳላቸውና ባህላዊ ተቋማቱ ግጭቶችን ለመፍታት የሚጠቀሙበት ደንብና ሥርዓት ለይቶ በማውጣት ጠቀሜታቸውን ማሳየት የሚል ነው።

በእነዚህ ዓላማዎች መነሻነትም በብሔረሰቡ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች «የዘር አበጋር፤» እና የስያሜ /የመንደር/ አበጋር እንደሆኑ « የዘር አበጋሮች የከረሩ፤ አስቸጋሪና ውስብስብ ግጭቶችን የሚያስወግዱ ናቸው። እነዚህ ተቋማት በኀይማኖት መሪዎች፣ በዕድሜ የገፉ የአገር ሽማግሌዎች፣ በዕውቀታቸው የሚታመንባቸው አስታራቂዎች ሊያቃልሉት ያልቻሉትን ግድያንና ከባድ ግጭቶችን የሚያስታርቁ ሲሆኑ «የስያሜ/የመንደር/ አበጋሮች» ደግሞ በሚኖሩበት አካባቢ ወይም በአንድ ማህበራዊ ግንኙነት ላይ ተደማጭነት ያላቸው ሰዎች የዘር አበጋሮች በሌሉበት ቦታና ጊዜ የእነሱን ሚና የሚሸፍኑ ናቸው። በአካባቢያቸው ዕለታዊና ቀላል የሆኑ ግጭቶች ሲከሰቱ የሚያስታርቁ መሆናቸውን በጥናቷ አካታለች። በተሁለዳሬ አበጋር የግጭት አፈታት ሥርዓት ወሉትና ምርቃት፣ ቃላዊ ግጥሞች፣ ተረቶችና ምሳሌያዊ ንግግሮች ከፍተኛ አስተዋዕኦ እንዳላቸውና ተቋሙም ማህበረሰቡ የሚያምንበትና የሚጠቀምበት ስለሆነ ግጭትን የማስወገድ ሚናው ከፍተኛ መሆኑን በጥናታዊ ጽሑፏ አመላክታለች።

ሌላው « በአድአ ሊበን ወረዳ የኦሮሞ ሰረ ጪፌ ከግጭት አንፃር» (1998) በሚል ርዕስ የቀረበው የኤም፡ኤ. መሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ የሙሉጌታ ነጋሳ ነው። ጥንታዊ ጽሑፉ በስድስት ምዕራፎች የተከፋፈለ ነው። ዓላማ አድርጎ የተነሳውም የኦሮሞ ሰረ ጉማ ምን እንደሆነና በግጭት አፈታት ዙሪያ ያለውን ፋይዳ ማመልከት፣ የሰረ ጉማ ማህበራዊ ዐውድና ክዋኔን በርቶ ግራፍ፣ በቪዲዮ ካሜራዎችና በቴፕ ሪከርድ ቀርፆ በመረጃ ምንጭነት እንዲያገለግሉ ማዘጋጀት ሲሆን የሰረ ጉማ የግጭት አፈታት ሂደት ውስጥ የአገር ሽማግሌዎች የኀይማኖት መሪዎችና ሌሎችንም የሚያበረክቱትን አስተዋጽኦ ማስተዋወቅ የሚሉ ናቸው።

ገዳያና የአካል መጉደል ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች በሰረ ጉማ ደንብና ሥርዓት መሠረት ለአካባቢው ማህበረሰብ የጋራ በሆኑ የዕምነት ስፍራዎች የሚፈጽሙ ድርጊቶችን ማመልከት

ነው፡፡ በእርቅ ስነ-ሥርዓቱ ከንውን ውስጥ መሃላ፣ ምርቃት፣ እርግማንና እግዚአታ ይፈፀማል፡፡ ይህም ግጭትን ለማስወገድ በሚደረገው ሂደት የላቀ ድርሻ ያበረክታል፡፡ በእድሜ የገፋና የተሻለ ግንዛቤ ያላቸው አባቶችና የሀገር ሽማግሌዎች ግጭትን ከማስወገድ አንጻርና በእርቅ ሥርዓቱ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች ተቀባይነት እንዲኖራቸው በማድረጉ በኩል ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ስለሆነም በሁለት ወገኖች መካከል የተፈጠረን ግጭት በማቃለል ቂም በቀልን አስወግዶ ተቀባይነት ያለው ሰላም በመፍጠር መረጋጋትን እንደሚያመጣ በጥናቱ አካቶ አቅረቧል፡፡

በ 1998 ዓ.ም የካቲት ወር ለኤም. ኤ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበው ሌላው ጥናታዊ ጽሑፍ «ሽምግልናና የእርቅ ሥርዓት በወላይታ» በሚል ርዕስ የተሰራ የይልማ ተፈሪ ጥናት ነው፡፡ በስድስት ምዕራፍ ተከፋፍሎ የቀረበው ጽሑፍ ዓላማ አድርጎ የተነሳው በወላይታ ማህበረሰብ ውስጥ እየተሰራባቸው ያሉት ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት እንዴት እንደተዋቀሩና ግጭትን ለመፍታት የሚጠቀሙበት ልማዳዊ ህግ እንዴት እንደሆነ ከለየ በኋላ ጠቀሜታውን ለማሳየት እንደሆነ በጥናቱ አመልክቷል፡፡

በወላይታ ብሔረሰብ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች«ጩሜታ» «ጫቆና» «ጩጫ ጬቻ መሆናቸውን አብራርቶ«ጩሜታ የሚባለው በዕርቅ ሥርዓት በጣም ከባድ ያልሆኑ ግጭቶች እንደ ባልና ሚስት፣ የቤተሰብ አባላት፣ የጎረቤት፣ የጓደኛና ጠለፋን የመሳሰሉትን መነሻ አድርገው የሚፈጠሩ ግጭቶችን ለመፍታት ያገለግላል፡፡«ጫቆ» ደግሞ በጎሳና በጎሳ መካከል የሚፈጠሩ ከባድ ግጭቶችን ለመፍታት ይጠቅማል፡፡ «ጩጫ ጬቻ» የተሰኘው የግጭት መፍቻ ዘዴ በገዳይ ምክንያት ግጭት ውስጥ የገቡ አካላትን ለማስታረቅ የሚገለገሉበት እንደሆነ ጥናቱ አሳይቷል፡፡ ቃላዊ ግጥሞች ምሳሌያዊ ንግግሮችና ተረቶች በወላይታ የሽምግልናና የእርቅ ሥርዓት ውስጥ ቁልፍና በጣም ጠቃሚ መሆናቸውን ጥናቱ ይጠቁማል፡፡

"Conflict and conflict Resoluation Among the people of chihera" (1998) በሚል ርዕስ የቀረበው የዮሐንስ ብርሃኑ ጥናት ስምንት ምዕራፎች አሉት፡፡ ጥናቱ በተካሄደበት አካባቢ የሚኖሩ ህዝቦች ባህላዊ የሽምግልና ሥርዓት ግጭትን ለመፍታት ቅድሚያ የሚሰጡትና ወሳኝ እንደሆነ፣ ህዝቡ ከመደበኛ የህግ ሥርዓት በበለጠ ባህላዊ ሽምግልናን እንደሚጠቀምና የሚመርጥበትን ምክንያት በመመርመር፣ የሽምግልና ባህላዊ የእርቅ ተቋም አወቃቀሩ በጥበብ፣ በእድሜ፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃዎች፣ በኃይማኖት የስልጣን ደረጃ ... የመምረጫ መስፈርት መሆኑን የጥናቱ ዓላማ ላይ አመልክቷል፡፡

የሽምግልና እርቅ ሥርዓት እርቅ እና «ይቅር ለእግዚአብሔር» በማለት ሁለት ስልቶችን እንደሚከተል በማሳየት ግጭቶች ቀላል ወይም ከባድ ሊሆኑ ቢችሉም ከሁለቱ ዘዴዎች በአንዱ መፍትሔ ሊገኝ ይችላል፡፡ በሽምግልና የእርቅ ሥርዓት ላይ ተረቶች ምሳሌያዊ ንግግሮችና

ፈሊጣዊ አነጋገሮች እርቁን የማፋጠንና መፍትሔ የማምጣት ሚናቸው ጉልህ ነው፡፡ እነዚህ አባባሎችና ንግግሮች ግጭትን የማብረድ፤ ቁጣን የማለዘብ፣ የሀገር ሽማግሌዎች ለዛ ያለው ቋንቋ ተጠቅመው ውሳኔያቸው ተቀባይነት እንዲያገኝ የማድረግ ኃይል አላቸው የሚለትን በጥናቱ አካቷል፡፡


# 4. በርቱማ፣ ባህላዊ የግጭት አፈታት በሸኮ ብሔረሰብ

## 4.1 የሸኮ ብሔረሰብ የአስተዳደርና የፍትህ ሥርዓት

የሸኮ ብሔረሰብ በግንኙነቱ የሚፈጠሩ ግጭቶች ሰላምን እናግተው ወደ ብጥብጥ እንዳያመሩ የሚቆጣጠሩበት ደንብ አላቸው:: ማህበረሰቡ በማህበራዊ ግንኙነቱ መረዳዳትን፣ መግባባትን፣ ስነ-ልቦናዊ ብርታትን ተላብሶ እንዲኖር የሚያስችል ከአያት ቅድመ አያት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ አስተዳደራዊ ሥርዓት አላቸው:: የዚህ ስርዓት አስፈፃሚ የሆነውና የማይናወጥ ሥርወ-መንግሥት ተከትሎ የሚሄደው ኮይናብ ነው:: ኮይናብ ማህበረሰቡን በበላይነት የሚያስተዳድር የባህላዊ ህጎች ሁሉ የበላይ አስፈፃሚ እንደሆነ በምዕራፍ ሁለት ተገልፇል::

ይህ ንጉሥ የሸኮ ብሔረሰብ አኮኖሚያዊ ማህበራዊ፣ አስተዳደራዊና ባሕላዊ ጉዳዮችን በበላይነት የሚመራ የሚቆጣጠርና ከፍተኛ ኃላፊነት የተሰጠው ነው:: ይህን ከፍተኛ ስልጣን ማህበረሰቡ የተቀበለውና ያፀደቀው ነው:: በመሆኑም ህጋዊ መሠረት ያለው ኮይናብ ሥርዓት እንዲከበር የሚያደርጉ በሥሩ የተዋቀሩ የፍትህ ሥርዓትን የሚያስፈፅሙ አካላት አሉት::

ተጠሪነታቸው ለኮይናብ የሆነ የህግአስፈፃሚ አካላት የሚባሉት በተለያየ አካባቢ የሚኖሩ የጎሣ መሪዎች ናቸው:: እነዚህ የጎሣ መሪዎች በሚያስተዳድሯቸው አካባቢዎች ለሚፈጠሩ ግጭቶች እንደየጉዳዮቹ ክብደትና ቅለት መፍትሔ እንዲያገኙ የሚያደርጉ ናቸው:: በብሄረሰቡ ህግና ደንብ መሠረት በርጃብ የሚባለው ግጭቶች ሲፈጠሩ ለማቃለልና ለማስወገድ ኃላፊነት ያለበት ነው:: በርጃብ የማስታረቅ ሥራውን የሚሠራው በጎሣ መሪዎች እየታዘዘ ነው:: ሁሉም የጎሣ መሪዎች የየራሳቸው በርጃብ አላቸው:: ከበርጃብ ቀጥሎ ያለው የዳኝነት እርከን በየአካባቢው የሚገኙ ታዋቂና በማህበረሰቡ ዘንድ ተሰሚነት ያላቸው ባቡ/ሽማግሌዎች/ ናቸው:: ስለዚህ የስልጣን እርከኑን ስንመለከት




ከላይ ወደ ታች የተዘረጋ የአስተዳደር መዋቅር ነው::

አንድ ሰው ወይም ቡድን ፍትሕ ለማግኘት ሲፈልግ ጉዳዩ በጣም ከባድ ከሆነ ለኮይናብ ያመለክታል። ኮይናብም ለአካባቢ የጎሣ መሪዎች ይመራል። የጎሣ መሪውም ወደ ቡርጃብ ይመራል። ቡርጃብ የተሰጠውን ትዕዛዝ ተቀብሎ ጉዳዩ መፍትሔ እንዲያገኝ በአካባቢው ካሉ ታዋቂ፣ታታሪ፣ቁምነገረኛና ዕውቀት ያላቸውን ሽማግሌዎች በማሰባሰብ እርቁን ያስፈፅማል። ውጤቱንም ለላከው የጎሳ መሪ ያቀርባል። የጎሣ መሪውም በደረጃው ለኮይናብ ያሳውቃል። ነገሩ በጣም ውስብስብና አስቸጋሪ ሆኖ በቡርጃብና በጎሣ መሪዎች የማይፈታ ከሆነ ለኮይናብ ያተላለፋል። በዚያ በኩል መፍትሔ ያገኛል (ኩርማ ዚቲ 20/4/99 ሾሻ ቀበሌ) በማለት ገልፀውልኛል። በቤሔረሰቡ ግጭትን ለማስወገድ የተዋቀሩ የፍትህ አካላት ከላይ የተጠቀሱት ናቸው። እነዚህ የፍትህ አካላት ግጭትን የሚያስወግዱት በበርቱሳ ሥርዓት ነው። በሸኮ ቤሔረሰብ በርቱሳ ተቀባይነት ያለው ሥርዓት ነው፡

በርቱሳ በህዝባዊ ዕውቁ ሰላምን፣ ፍቅርን፣ ዝምድናን ከማጠናከር አንፃር የሚታይ ነው። ሰዎች በግጭት ምክንያት ሁከት፣ብጥብጥ፣ ስደትና የስነ-ልቦና ቀውስ ውስጥ ገብተው እንዳይቀሩ የበርቱሣ ሥርዓት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል። ስለሆነም የበርቱሣን ምንነት መገንዘብ የሚያስገኘው ማህበራዊ ጠቀሜታ አንፃር ነው።

በርቱሳ እንደመደበኛ የህግ አንቀጽ እየተጠቀሰ በዘመናዊና መደበኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚሰጥበት ሳይሆን ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል የሚተላለፍ ነው። በርቱሳ ባህላዊ እሴቶችን መሠረት በማድረግ በመሃላ፣ በምርቃት ፣በእርግማን፣ በውግዘት፣ በማህበራዊ መገለል ... እየተተናበረ የሚከናወን ነው። ይህም የራሱ ተሳታፊዎች መቼቶች፣ ዕውዶች ያሉት ባህላዊ ሥርዓት ነው። ስለዚህ በርቱሣ በማህበራዊና ባህላዊ ዐውድ ይወሰናል። በተሳታፊዎች ጉልህ ሚና ለውጤት ያበቃል። እርቀ ሰላም ይወርድበታል። ተቃረኖ ውስጥ በገቡ ወገኖች መካከል የሚከሰቱ ግጭቶች ተወግደው ወደ ሰላማዊና የተረጋጋ ህይወት ውስጥ ይገቡበታል።

የሸኮ ማህበረሰብ ከቀድሞ ጀምሮ ከነበረው የፍትህ ሥርዓት ጎን ለጎን ይጠቀምባቸው የነበሩትን ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት የአሰራር ደንብና ሥርዓት ይዞ በመቀጠል እስካሁን ድረስ በአካባቢው ለሚከሰቱ ግጭቶች በቤሔረሰቡ ልማድና ደንብ መሠረት መፍትሔ እየሰጠ ይገኛል። በሸኮ ማህበረሰብ ከቀላል ዕለታዊ ጠቦች አንስቶ እስከ ከባድ የነብስ ግድያ ድረስ የሚከሰቱ በርካታ ግጭቶች ይኖራሉ። የግጭቶቹ መነሻዎችም በአብዛኛው በማህበረሰቡ መካከል ካሉ ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ አስተዳደራዊና ባህላዊ እውነታዎች ጋር በእጅጉ የተቆራኙ ናቸው። በአካባቢው በተለያዩ ሁኔታዎች የሚፈጠሩ ግጭቶችን እንደየባህሪያቸውና ደረጃቸው ለመፍታት ባህላዊ የበርቱሣ የግጭት አፈታት ሥርዓት ይጠቀማሉ።

በሸኮ ቤተሰብ ግጭት በሦስት ተከፍሎ ይታያል፡፡ የመጀመሪያው በጫ፣ይባላል፡፡ «በጫ» ቀላል ጠብ የሚባል ሲሆን በተለያዩ መነሻ ምክንያቶች በቤተሰብ በባልና ሚስትና በጎረቤት መካከል ዘለፋና ስድብ፣ ዛቻና ማስፈራራት የሚፈፀምበት ነው፡፡ ሁለተኛው «ደብም» ነው፡፡ ይህ ደግሞ መካከለኛ ጠብ ይባላል፡፡ በድንበር ጭቅጭቅ፣ በሀብት በስርቆት፣ በባህላዊ እሴቶች አለመግባባት የተነሳ በድብደባ ምክንያት በአካል ላይ ጉዳት ማድረስ የሚፈፀምበት ነው፡፡ ሦስተኛው «ሽቡደብም» የሚባለው ሲሆን በጣም የከረረ ጠብ የሚባለው ነው፡፡ በዚህ ጠብ የነብስ ግድያ የሚፈፀምበት ነው፡፡

በበርቱግ ከሚፈቱ ግጭቶች መካከል ግድያ፣ የባልና ሚስት ጠብ፣ ጠለፋ፣ በጎሣና በጎሣ መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶች፣ ስርቆትና የሀብት ክህደት እንደሆኑ ከባህሉ ባለቤቶች የተሰበሰበው መረጃ ያስረዳል፡፡ አንዱ ግጭት ለሌላው ግጭት ምክንያት የሚሆንበት አጋጣሚ ያለ በመሆኑ የበዳዮቹ የእርቅ ሥርዓት ላይ ተመሳሳይነት አለ፡፡ ስለሆነም ከግጭቶቹ ዋና ዋናዎቹን ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

## 4.2 የግጭት አይነቶችና የአፈታት ሥርዓታቸው

### 4.2.1 የነፍስ ግድያ

በሸኮ ቤተሰብ የግድያ ወንጀል የሚፈፀመው በጠለፋ፣ባል ሚስቱን ሌላ ሰው ሲያገባበት፣በጎሣና በጎሣ መካከል በሚፈጠሩ የለቅሶ፣የዓመታዊ በዓላትና የሰርግ ጭፈራ፣ አንዱ ወገን የሌላውን ንብረት ሲሰርቅ፣ በድንበርና በግጦሽ ቦታ በሚፈፀሙ የወሰን መተላለፍና በመሳሰሉት ምክንያቶች በሚፈጠሩ ግጭቶች ነው፡፡ የዚህ አይነት ድርጊት በአብዛኛው የሚፈፀመው በጎረምሶችና በጎልማሶች ሲሆን ይህም በሸኮ ቋንቋ (ሽቡደብም) /የከረረ ጠብ/ የሚባለው ነው፡፡

በቤተሰቡ የነፍስ ግድያን የሚያስታርቁት ቡርጃብ የሚባሉ ናቸው ቡርጃቦች በሰብሳቢነት ተሰይመው በአካባቢው ያሉ ሽማግሌዎች ተመርጠው ይጨመራሉ፡፡ ቡርጃቡ በአካባቢው ያለውን ባህል ጠንቅቆ የሚያውቅ ነው፡፡ ሽማግሌዎችም የገዳይና የሟች ዘመድ ያልሆኑ፣ ጥሩ ስነ-ምግባር ያላቸው፣ ተሰሚ የሆኑና በአካባቢው ህዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውና በማስታረቅ ልምድ የተካኑ የዕድሜ ባለፀጎች ናቸው፡፡

በቤተሰቡ የነብስ ግድያ ጉዳይ መጀመሪያ የሚታየው በባላባት ዘንድ ነው፡፡ የነብስ ግድያ ሲፈፀም በባላባቱ ቤት አካባቢ በሚገኝ ትልቅ ዛፍ ስር በመሆን ባላባቱ ገዳዩንና የገዳዩ ወገኖች የሚናገሩትን በትዕግስት ያዳምጣል፡፡ የገዳይ ቤተሰብም«በእጃችን የሰው ህይወት አልፏል፡፡» ስለዚህ አስከፊ ወንጀል ሠርቷል፡፡ የደረሰበትን በደል ለጎሣ መሪና ለሽማግሌ መክሰስና

ማኅበሩ ሲገባ ባህላዊ ህጉን በመጣስ ጥፋት ስለሰራ እኛም እንድንሰደድ አድርጎናል:: ስለዚህ ከሟች ቤተሰብ ጋር እንድንታረቅ እርዱን በማለት» ይናገራል::

ግድያ የተፈፀመበትን ምክንያትና የተፈፀመበትን አካባቢ ጠይቆ ይረዳል:: ሁሉንም መረጃ አሟልቶ ከጨረሰ በኋላ ፀሎት ያደርጋል:: የተፈጠረው ችግር እንዲቃለል አምላኩን ይለምናል በአካባቢያችን የተፈጠረው ግጭት የሰው ህይወት እንዲጠፋ አድርጓልና ፈጣሪዬ ሆይ የዚህ ግድያን አስቀድሞ ጥፋት እንዳይደርስበት የአንተ እገዛ አይለየን ደግሞ በክልላችን ግድያ አይምጣብን ይህንን የተፈጠረን ግጭት እንዲቃለል እርዳን፣ የሟችን ወገን አራራልን እርቀ ሰላምን አውርድልን በማለት ይማፀናል::

የሰሩት ወንጀል ቢሆንም የባህሉን ህግ ጠብቀው በመምጣታቸው ጉዳዩን ሟቹ ካለበት አካባቢ ካሉት ጋር ተነጋግረው እስከሚያመቻቹ መታገስ እንዳለባቸው ይነግራቸዋል:: በመጨረሻም ግድያ በተፈፀመበት አካባቢ እንዳይሄድ ያስጠነቅቃል:: የሚገኙበትን አድራሻ ጠይቆ መልዕክት ሲላክላቸው እንዲመጡ በመናገር ያሰናብታቸዋል::

በባህሉ ህግና ሥርዓት መሠረት የነብስ ግድያ በርቱሚ የሚከናወነው የጎሣ መሪና የጎሣ መሪ፣ በወረዳውና የአካባቢ ታዋቂ ሽማግሌዎች አማካይነት ተላልከው ሁኔታዎች ባህላዊ ሥርዓቱ በሚፈቅደው መሠረት ከተመቻቹ በኋላ ነው:: ሰው የገደለ ሰው ግድያ በተፈፀመበት አካባቢ ሌላው የጎሣ መሪ መግደሉን አይነገረውም:: ከአካባቢው ርቆ መሄድ አለበት:: ይህም የሟች ወገኖች እንዳያገኙት ነው:: በሌላ በኩል በበርቱሳው ሥርዓት ወቅት ነገሩን ለማርገብ ይጠቅማል መፀፀቱን ስለሚጠቁምም የሟች ወገኖች ክብራቸውን እንደመጠበቅ ተደርጎ ይታያል

በገዳዩ ቤተሰብ ማመልከቻ የቀረበለት የጎሣ መሪ ነገሩን ከሰማበት ሰዓት ጀምሮ ለጉዳዩ ክብደት ሰጥቶ ይንቀሳቀሳል:: በሥሩ ያለውን ቡርጃብና ሁለት ታዋቂ ሽማግሌዎችን ያስጠራል:: የጎሣ መሪው መልዕክት የደረሳቸው ሽማግሌዎችና ቡርጃብ በጎሣ መሪው ከይብሲንታ/ደጅ/ ይመጣሉ:: የጎሣ መሪውም በተለመደው የመሰብሰቢያ ትልቅ ዛፍ ስር ከተጠሩት ሰዎች ጋር ይቀመጣሉ:: የተፈጠረውን ችግር ያስረዳቸዋል:: በቡርጃብ ሰብሳቢነት ወደሟች ቤተሰብ አካባቢ የጎሣ መሪ ሄደው የሆነውን ለባላቱ እንዲናገሩ ትዕዛዝ ይሰጣል:: ጉዳዩ የተሳካ እንዲሆን ፀሎት አድርጎ በሰላም ተመለሱ በማለት ይልካቸዋል::

የነፍስ ግድያ መፈፀሙ የተነገረው የጎሣ መሪ የላካቸው ቡርጃብና ሽማግሌዎች በተሰጣቸው ትዕዛዝ መሠረት ይሄዳሉ:: በባህሉ እንደዚህ አይነት ጉዳይ ሲያጋጥም በጎሣ መሪ ቤት የሚሄደው ጧት ነው:: አካባቢው ሩቅ ከሆነ ጠጋ ብለው ከዘመድ ቤት በማደር ጧት ተነስተው

ይሄዳሉ፡፡ በጎግመሪው ቤት እንደደረሱ የላካቸውን የጎሣ መሪ ስምና የመጡበትን ምክንያት ያስረዳሉ፡፡ የመጡበት ጉዳይ የንብስ ግድያ መሆኑ ሲታወቅ ነገሩ ክብደት ስላለው ከሰው እይታ ራቅ በማለት ወደ ባላባቱ የመሰብሰቢያ ትልቅ ዛፍ ስር ይሄዳሉ፡፡ ውይይት ይጀመራል፡፡ መልዕክተኞቹ ገዳዩ ባህላዊ ሥርዓቱን ጠብቆ ለጎሣ መሪው መናገሩን፣ መፀፀቱንና ማመልከቱን ይገልፃሉ፡፡ ስለዚህ አፋጣኝ መፍትሄ እንዲሰጥ ያስፈልጋል፡፡ የገዳይ ቤተሰብ አካባቢያቸውን ለቀዋል፤ ህፃናት፣አዛውንቶችና ሴቶች እየተንገላቱ ነው፡፡ የበርቄሳው ስርዓት እስከሚከናወን ባህላዊ ህጉ በሚፈቅደው መሠረት ይፈጸም በሚሉት ጉዳዮች ዙሪያ በጋራ ይወያያሉ፡፡ የጎሣ መሪው ኃላፊነቱን ይቀበላል፡፡ ከእንግዶች ጋር ፀሎት ያደርጋሉ፡፡ ነገሩ እንዲቃለል አምላክ እንዲረዳቸው ይማፀናሉ፡፡ የጎሣ መሪው ባህላዊ ሥርዓቱ በሚፈቅደው መሠረት የሚከናወነውን ሰሐኤርስ መልዕክት እንደሚልክ ተነጋግረው ይለያያሉ፡፡

በሟች ቤተሰብ አካባቢ ያለው የጎሣ መሪ የተፈጠረን ግጭት የማርገብና የማቃለል ኃላፊነት አለበት፡፡ መልዕክት ከደረሰው ቀን ጀምሮ የተፈጠረው ግጭት መፍትሔ እንድያገኝ ጥረት ያደርጋል፡፡ በአንድ አካባቢ ሰውና ሰው ከተገዳደለ የበርቄሳ ሥርዓት የሚከናወነው በዚያው አካባቢ ባለው በርጃብና ቃዊቱ ሽማግሌዎች ነው፡፡ የበርቄሳ ሥርዓት እንዲከናወን የሚያዘው የጉም የጎሣ መሪው ነው፡፡ ስለዚህ በርጃብ ካለበት ኃላፊነት አንፃር የአስታራቂነት ሚናውን ለመወጣት ያለመታከት ይሠራል፡፡ በንብስ ግድያ በርቄሳ የቡርጃብ የመጀመሪያ ሥራው በሁለቱ ባላንጣዎች ድንበር ላይ እርጥብ ግራዋ ቆርጦ መጣል ነው፡፡

በርጃብ የሟች ወገኖች የሚኖሩበት አካባቢ እርጥብ ግራዋ የሚጥለው ለሁለት ነገር ነው፡፡ የመጀመሪያው የሟች ቤተሰቦች በገዳይ ቤተሰቦች ላይ የበቀል እርምጃ በመውሰድ አደጋ እንዳያደርሱ ነው፡፡ ገዳዩና ቤተሰቦቹ ባህላዊ ህጋችን በሚፈቅደው መሠረት ድርጊቱን ለባላባት አሳውቀዋል፡፡ ቤተሰቡ በሙሉ አካባቢውን ለቀዋል፡፡ ስለዚህ የተፈጠረውን ግጭት በጎሣ መሪ በበርጃብና ሽማግሌዎች አማካይነት እስከሚታይ ታገሱ የሚል ማሳሰቢያ ነው ሁለተኛው ጥፋት የፈፀመው ሰው ቤተሰቦች በወንዝ፣ በግጦሽ ቦታ፣ በለቅሶና በገበያ ... ሁሉ ላለመገናኘት ሸሽተዋል፡፡ አገር ጥለው ተሰደዋል፡፡ ስለዚህ እስካሁን የተሰቃዩት ይበቃል ወደ መኖሪያ አካባቢያቸው ይመለሱ፡፡ የበርቄማው ሥርዓት እስከሚከናወን እናንተም በቡርጃብ አማካይነት የተጣለውን ግራዋ አትለፉ፡፡ በራሳችሁ አካባቢ በሚገኝ ውኃ፣ ግጦሽ ገበያና ሌሎች ማህበራዊ ግንኙነቶችን አድርጉ የሚል ነው፡፡ በብሔረሰቡ እምነት ባህላዊ ህጉን የጣሰ መጥፎ ነገር እንደሚደርስበት ስለሚታወቅ የቡርጃቡ ግራዋ ቅጠል መጣል ዋጋ አለው፡፡ ቅጠሉ ከተጣለበት ቦታ አልፈው አይሄዱም የጎሣ መሪውንና የቡርጃቡን እርግማን ይፈራሉ፡፡

በአካባቢው ባሉ የበርቄሳ ሥነ-ሥርዓት እስከሚከናወን የገዳይና የሟች ቤተሰብ ከአንድ ወንዝ ውኃ ቀድተው አይጠጡም፡፡ በአንድ ገበያ አብረው አይውሉም ከብቶቻቸው አንድ ላይ

አያሠማሩም። ልጆች አንድ ላይ አይጫወቱም። በለቅሶና በሰርግ ቦታ አይገናኙም። ማህበራዊ ግንኙነቱ የሚከለከለው ለገዳይ ቤተሰብ ነው። የሟች ቤተሰብ ከሁሉም ቦታ እንዲቀሩ አያከለክሉም።

በብሔረሰቡ እምነት የሰው ህይወት ያጠፋ ወንጀሉ ከተፈፀመበት አካባቢ ተሰውሮ መኖር አለበት። የሟች ቤተሰብ በደም ፍላት ተነሳስተው አደጋ ሊያደርሱበት ይችላሉ። የገዳይና የሟች ቤተሰብ ተቀራርበው የሚኖሩ ከሆነ የገዳዩ የቅርብ ዘመዶች አካባቢውን መልቀቅ አለባቸው። በተለይም ገድያው በተፈፀመበት ሰሞን መሰወር የግድ ነው። ይህ ካልሆነ የሟች ወገን የአፀፋ እርምጃ ይወስዳል።

በሟች ቤተሰብ አካባቢ የሚገኘው ቡረጃብ ከአካባቢው የጎሣ መሪ ትዕዛዝ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በእርጥብ ግራዋ መጣል የጀመረውን ባህላዊ የእርቅ ጅማሮ ይቀጥልበታል። የበቀል እርምጃ እንዳይፈፀም ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል። ቀጣዩ እርምጃ ከሟች ቤተሰብ ጋር ተገናኝቶ እርቅ እንዲፈፀም ማድረግ ነው። የሟች ወገን ሀዘኑን እየረሱ መምጣታቸውን ማረጋገጥ የመጀመሪያ ሥራ ነው። ቡረጃብ በማስታረቅ ሥራ የተካነ ነው። ለረዥም ጊዜ ያካበተው የማስታረቅ ጥበብ አለው። ለእርቁ ስኬት የሚረዱትን የአካባቢ ሽማግሌዎች ይመርጣል። እነዚህም በአካባቢው ህዝብ ተቀባይነት ያላቸው፣ ፈግመው የሚያደርሱ፣ መርቀው የሚያስደስቱ ማህበራዊ ከበሬታ ያላቸው የዕድሜ ባለፀጎች ናቸው።

የተመረጡት የአካባቢ ሽማግሌዎች በቡረጃብ ሰብሳቢነት ወደሟች ቤተሰብ ቤት በጧት ተነስተው ይሄዳሉ። እዚያም እንደደረሱ ከሟቹ የቅርብ ዘመድ በር ላይ ቆመው በሩን ያንኳኳሉ በሩ ሲከፈት በቡረጃብ መሪነት ወደ ቤት ውስጥ ይገባሉ። በቤት ውስጥ እንደገቡ የተፈጠረው ነገር ሁሉም መጥፎ መሆኑንና እነሱም ጉዳት እንደደረሰባቸው በማንሳት ያፅናናሉ። ገዳዩም ሰይጣን እንዳሳሳተውና መጥፎ አጋጣሚ መሆኑን አውስተው የዚህ ዓይነት ክስተት የማያጋጥም መሆኑን ይገልፃሉ። የሟች ወገኖችም ቡረጃብ የተከበረ በመሆኑ የሚናገረውን በጥሞና ያዳምጣሉ። በመጨረሻ የመጡበት ጉዳይ ለእርቅ መሆኑ ይነገራቸዋል። በባህሉ በመጀመሪያ ቀን እሺ ማለት ያልተለመደ ስለሆነ መታረቅ የማይፈልጉ መሆናቸውን ይገልፃሉ። ቡረጃቡ ደጋግሞ በለምንም እሺ አይሉም ሽማግሌዎችና ቡረጃብ ወደመጡበት ይመለሳሉ።

ቡረጃብና መጀመሪያ አብረውት የሄዱት ሽማግሌዎች ለሁለተኛ ጊዜ በሟች ዘመዶች ቤት ይሄዳሉ። አሁንም እርቅ መውረድ አለበት ብለው ይጠይቃሉ (ይማፀናሉ)። ለእርቅ የጠየቁበት ምክንያት በጎሣ መሪዎች ትዕዛዝ መሆኑን ያሳውቃሉ። አሁንም የሟች ቤተሰብ ፈቃደኛ አይሆኑም። ቡረጃብ የሚከበርና ታዋቂ ቢሆንም የሟች ወገን ማንገራገራቸው የሚጠበቅ ነገር ነው። በመጨረሻም ቡረጃቡ ጥንቃቄ በተሞላበት አቀራረብ ገዳዩ ባህላዊ ሥራዓቱን ጠብቆ አገር ለቆ ጠፍቷል። ዘመዶቹም ተሰደው ብዙ ጊዜ ሆኗቸዋል። ገዳዩ በድርጊቱ መፀፀቱን አሳውቋል።

ስለዚህ እሽ ብትሉን መልካም ነው ለናንተም ጥሩ አይሆንም በማለት ነገ በኔን እንድያስታውሱ ያሳስባል። ለምቢ ብለው የሚያስቸግሩ ከሆኑ ለጎሣ መሪው ተነግሮ ከዚያም ለከይናብ ይተላለፋል። ይህ ደግሞ ለነሱ ጥሩ አይደለም መረገም ነው። እረግማኑን ፈርተው ፈቃደኛ እንዲሆኑ ደጋግመው ይጠይቃሉ ጥያቄው እየበረታ ሲመጣ እኛ ብቻችን መወሰን አንችልም ከዘመድ ጋር እንምከርበት ይላሉ። በባህሉ የዚህ አይነት ደረጃ ከተደረሰ ጥሩ ፍንጭ ነው ሽማግሎች ለሦስተኛ ጊዜ የምንመለሰው ጥሩ ነገር ለመስማት ነው በደንብ አስቡበት ወቀቢን ፍሩ ከይናብን ፍሩ የጎሣ መሪንና ሽማግሌን ፍሩ በማለት ጠንከር ያለ ንግግር ተናግረው ይወጣሉ።

በርጃቡ ከተጣለበት ኃላፊነት አንዱ ሰዎችን ማግባባትና የበርቴሣው ሥርዓት መከናወን እንዳለበት ስለሚያምን ለሦስተኛ ጊዜ ከመሄዳቸው በፊት የሟችን ወገን የሚያግባባ ሰው ያመቻቻል። የሟች ወገን የቅርብ ዘመድ ወይም ጎረቤት ፈልጎ የማግባባትና የማሳመን ሥራ እንዲሠራ ያደርጋል። የሟችን ወገን ለማግባባት የተመረጡት ሰዎች ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ እየተጠቀሙ የማግባባት ሥራ ይሠራሉ። የሟች ወገንም የጎሣ መሪውንና የቡርጃብን ስልጣን ስለሚያውቁና ሽማግሎች መመላለሳቸውን በማሰብ ፈቃደኛ የመሆን አዝማሚያ ያሳያሉ። የማግባባት ሥራውን የሚያከናውኑት ሰዎች የሟች ቤተሰብ ለእርቅ መዘጋጀታቸውን ለቡረጃብ በማስጥር ይናገራሉ።

ለሦስተኛ ጊዜ ሽማግሎችና በርጃቡ በተለመደው ሰዓት ወደ ሟች ቤተሰብ ቤት ይሄዳሉ። በዕለቱ የሟችን ወገን እንዲያግባቡ ኃላፊነት የተሰጣቸው ሰዎችም ይኖራሉ። ውስጥ ውስጡን ያለቀ ጉዳይ ስለሆነ ሽማግሎች ወገን ለመጠበቅ ሲሉ ያለፈውን ጉዳይ እምን አደረሳችሁት ብለው ይጠይቃሉ ከብዙ ዝምታ ቡኋላ የሟች ወገን ፈቃደኝነታቸውን ይገልፃሉ። ቡርጃቡም በመደሰት ምርቃት ያቀርባል። ከምርቃቱ ቡኋላ ጨሞ እንዲጠጡ ይደረጋል። የሽማግሎቹ ጥረት ስለተሳካ ጨሞው ሲጠጣ በፈገግታና በደስታ ነው። ጨሞ የሸኮ ብሔረሰብ ባህላዊ መጠጥ ነው። ከቡና ቅጠል የሚዘጋጅ ሲሆን ነጭ ሽንኩርት፣ ጨው፣ ሚጥሚጣና በሶቢላ ተጨምሮ በማሰሮ የሚፈላ ነው በሸኮ ብሔረሰብ ጨሞ መጠጣት የተለመደ ነው። አንድ ሰው ወደ መኖሪያ አካባቢ ሲሄድ ጨሞ ጠጡ ነው የሚባለው። ጨሞ ለማንም ሰው አይነፈግም።

በርጃቡና ሽማግሌዎች ሳይታክቱ የሟችን ወገን ለዕርቅ ፈቃደኛ እንደሆኑ ጥረት አድርገው ተሳክቶላቸዋል። ውጤቱም ለጎሣ መሪው ይነገራል። ነገሩ መሳካቱን የሰማው የጎሣ መሪ ይደሰታል። በርጃቡና ሽማግሌዎቹ ኃላፊነታቸውን ስለተወጡ ምስጋና ያቀርባል። የምስጋናው ምስጢር ትዕዛዙ ስለተከበረ ብቻ ሳይሆን በሚያስተዳድረው አካባቢ ሰላም መስፈኑን በመገንዘብና ከእቻ የጎሣ መሪ የመጣው መልዕክት ባግባቡ ስለተከናወነ ባህላዊ ህጉን የማስከበር ብቃት እንዳለው የሚያሳውቅ ስለሆነም ነው። ስለዚህ ለእቻ የጎሣ መሪ ጉዳዩ መሳካቱን ያሳውቃል።

በገዳይ ቤተሰብ በኩል ባህላዊ ህጉ የሚያዘውን እንዲፈፅሙና በነሱ በኩል የሚቀመጡ ሽማግሌዎችን እንዲያዘጋጁ አስታውሶ የቀጠሮውንም ቀን ወስኖ ይልካል::

የበርቱግው ሥርዓት እንዲከናወን በተያዘው ቀጠሮ ሽማግሌዎች ይሰበሰባሉ:: አስታራቂ ሽማግሌዎች የሚሆኑት ከሟችና ከገዳይ ወገን ዝምድና የሌላቸው መሆን እንዳለበት ተገልጿል:: ከሁለቱም በኩል የሚቀርቡት ቡርጃዎች የበርቱግው ሥርዓት ዋና ተዋንያን ናቸው:: ከቡርጃብ በተጨማሪ ከገዳዩ ወገን አራት ከሟች ወገን አራት ሽማግሌዎች ይመረጣሉ:: ዕርቅ ከመጀመሩ በፊት የተመረጡት ሽማግሌዎች አድሉ እንዳይፈፅሙ በባላባቱ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል:: በዚህ እርቅ ላይ አድሉ የሰራ የገድያ ወንጀል ከዘሩ አይጥፋ! የወለደው አይደግ! የዘራው አያፍራ! ታማሪ ከስ ያፊቅ... የመሳሰሉትን መጥፎ መጥፎ ነገሮች እያነሳ ያስፈራራል:: በመቀጠል በረጃዎቹና ሽማግሌዎች በነገ መሪው አቀነባባሪነት የጋራ ፀሎት ያደርሳሉ:: የፀሎቱ ፋይዳ ነገሩ ለዓማቸ በሆነ መንገድ እንዲያልቅ አምላካቸውን መለመን ነው:: ሽማግሌዎችም ለጉዳዩ ትኩረት እንዲሰጡ ነው::



አስታራቂ ሽማግሌዎች

በሸኮ ብሔረሰብ የበርቄማ ሥርዓት የሚከናወነው ዕሁድና ሐሙስ ነው:: ሐሙስ ቀን በብሔረሰቡ ይከበራል:: በዚህ ቀን ሥራ አይሠራም በምትኩ ንፋስ ጉዳት እንዳያመጣ፣ መብረቅ እንዳይወርድ፣ የውኃ ማጥለቅለቅ እንዳይከሰት፣ በሽታ እንዳይስፋፋ... የሚፀለይበት ቀን ነው:: በአካባቢው የሚኖሩ ቃልቾች ሐሙስና ዕሁድ ቀን መከበር እንዳለባቸውና የውቃቢ ቀን እንደሆኑ ያስተምራሉ:: በመሆኑም ሐሙስና ዕሁድ የሚከበሩ ቀኖቹ ስለሆኑ የማሥታረቅ ሥራ የሚሠራው በነዚህ ቀኖች ነው:: ቀኖች ፀሎት የሚደረግባቸው በመሆኑ የተከሰተ ግጭት እልባት ያገኛል የሚል ሀሳብ መኖሩን የመረጃ አቀባዮች ገልፀውልኛል::


ገዳዩና ቤተሰቦቹ ወደ ባላባት ቤት ሄደው እርቅ እንድፈፀም ከጠየቁበት ጊዜ ጀምሮ ለካሣ የሚሰጠውንና ለእርቅ ማስፈፀሚያ የሚያገለግሉ ነገሮችን ያዘጋጃሉ:: በብሔረሰቡ ህግ ሰው የገደለ ሰው አንድ ልጃገረድ ወይም ወንድ ልጅ እንዲከስ በባህላዊ ደንቡ የተደነገገ ነው:: የሰው ካሣ የሚሰጥበት ምክንያት የሞተውን ሰው የሚተካ እንዲወለድ ነው:: በሞተው ሰው ምትክ ሌላ ሲወለድ የወላጆችን ሀዘን ያስረሳል ተብሉም ነው:: ሌሎች የገዳይ ቤተሰብ ማቅረብ የሚገባቸው በግ፣ ወይፈን፣ ዶሮ፣ የሚጠጣ፣ ጠጅ፣አረቂ፣ ቦርዴ/ከጤፍና ከጌሾ የሚዘጋጅ ጠላ/፣ የሚበላ ባካ፣ ከቺ፣ እንጀራ፣ ወትቱ የአዝመራ ከሆነ ኪጆ/ከበቆሎ እሸት የሚዘጋጅ ባህላዊ ምግብ/ ነው:: ገዳዩ ሀብትና ንብረት ከሌለው አባትና እናት እህትና ወንድም አጎትና አክስት እንዲሁም የቅርብ ዘመድና ጎረቤት ይረዱታል::

ገዳዩ ለካሣ የሚከፈል ልጃገረድ ወይም ወንድ ልጅ እንደሌለውና በቤተሰቡ በኩልም ሊያቀርብለት የሚችል የሌለ መሆኑን ለአስታራቂ ሽማግሌች ቀድሞ ያሳውቃል:: ሽማግሌችም አለመኖሩን በትክክል ያጣራሉ:: በአካባቢው ባህል የሰው ካሣ ማቅረብ የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ የእንስሳ ካሳ እንዲቀርብ ይደረጋል:: የሟች ቤተሰቦችም ገዳዩ የሰው ካሣ መስጠት እንደማይችል የገለፁቸዋል:: እነሱም ሽማግሌች በትክክል ማጣራታቸውን ጠይቀው ይረዳሉ:: ገዳዩ የሠው ካሣ አለማቅረቡን ሲያረጋግጡ የከብት ካሣ ለመቀበል ፈቃደኛ ይሆናሉ:: ባህላዊ ህጉ በሚፈቅደው መሠረት ከ 10-12 የሚደርሱ ከብቶች ለካሳ ይሰጣሉ::

በብሔረሰቡ ባህል የበርቄማ/እርቅ/ ስነ-ስርዓት የሚከናወነው በትልቅ ወራጅ ወንዝ ዳር ነው:: በቤት አካባቢና እህልና አትክልት በሚያበቅል መሬት ውስጥ የነብስ ግድያ ግጭት እርቅ አይከናወንም:: በቤት አካባቢ የማይከናወነው በቀያቸው የዚህ አይነት መገዳደል እንዳይኖር በመፍራት ነው:: ወንዝ ዳር የተመረጠበት ምክንያት ሰው እንዲጣላና እንዲጠፋፋ የሚያደርገውን የግጭት መንፈስ ውኃ ጠራርጎ ይወስደዋል በሚል ነው:: በእህልና አትክልት ቦታ የማይከናወነው ማሳው እህል አያበቅልም አትክልት ተተክሎ አይፀድቅም ተብሎ ስለሚታሰብ ነው::ወንዝ ወራጅና ተጓዥ ስለሆነ ሰውና ሰው እንዳይስማማና እንዲገዳደል የሚያደርገው እርኩስ መንፈስ በወራጅ ውኃ ተጠራርጎ ይሄድ:: በመካከላችን ሰላም ይፈጠር::

እንደወትሮው እንሁን። እንስማማ። በክፉ እንተሳሰብ። ተደጋግፈንና ተባብረን በፍቅር እንኑር በሚል አስተሳሰብ ነው።

ለእርቅ ቀጠሮ የሚያዘው በወንዝ ዳር ቢሆንም የገዳይና የሟች ቤተሰብ በአንድ አካባቢ አይቀመጡም። ከወንዝ ማዶ ለማዶ ሆነው ለየብቻ ይቀመጣሉ። እርቅ ስላልወረደ ገዳዩ በሟች ዘመዶች ጥቃት እንዳይደርስበት በማሰብ ነው። በብሔረሰቡ ባህል ጦር አዘውትሮ መያዝ የተለመደ ነው። ለእርቅ የሚመጡት የሟች ቤሰተቦች ድንገት ተነሳስተው ነገር እንዳይፈልጉ ሽማግሌዎች ያስጠነቅቃሉ ያስፈራራሉ። የገዳይ ቤተሰቦችን ደግሞ ደበቅ ብለው በስውር ቦታ እንዲቀመጡ ያደርጋሉ።



በእርቅ ሥነ ሥርዓት ወቅት የሟች ቤተሰብ ለብቻ ተቀምጠው



በእርቅ ሥነ ሥርዓት ወቅት የገዳይ ቤተሰብ ለብቻ ተቀምጠው

አስታራቂ ሽማግሌዎች ወንዝዳር የሚገኝ ዛፍ ስር ተቀምጠው በእርቅ አፈፃፀሙ ዙሪያ ይመክራሉ። መደረግ የሚገባው ነገር ሁሉ እንዳይቀር የገዳይ ቤተሰብን እየጠሩ ይጠይቃሉ ለእርቅ ማስፈፀሚያ የሚያስፈልጉ ቀርድ፣በግ፣አፁ/ስርጢ/፣ የእህል ዘር፣ ዶሮ... መዘጋጀቱን ያረጋግጣሉ። ለካሣ የሚቀርበው ሰው ከሆነ መቅረቡን ያያሉ። እንስሳት ከሆኑም ባህላዊ ህጉ በሚፈቅደው መሠረት ቁጥራቸውና የከብቶች ሁኔታ/ጥራታቸው/ በሽማግሌዎች ይረጋገጣል። አስፈላጊው ሁሉ መሟላቱን ሳያረጋግጡ እርቅ ቢጀምር የሟች ቤተሰብ ሰበብ ፈልገው የእርቁን ሥነ-ሥርዓት ሊያፈርሱ ይችላሉ። ስለሆነም የካሳና የእርቅ ማስፈፀሚያ ነገሮች በሚፈልገው መጠን መቅረባቸው በሽማግሌዎች ይረጋገጣል። እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ከቀረቡ በኋላ በቀጥታ ወደ እርቅ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም ይገባል።

በእርቅ ወቅት ለደም ማድረቂያ በግ ይታረዳል በጉ የሚታረደው በወንዙ ዳር ነው ይህም ሁለት አይነት ጠቀሜታ አለው። የመጀመሪው በጉ በወንዝ ዳር ሲታረድ ደሙን ጎርፍ ይዞት ይሄዳል። በገዳይና በሟች መካከል ጥል እንዲፈጠር ያደረገው ሰይጣን ነው ተብሎ ስለሚታሰብ የበጉን ደም ጠራርጎ ጎርፍ ሲወስደው በሁለቱ ወገኖች መካከል መራራት፣ተንኮል፣በክፉ መተያየትና ቅራኔ በጎርፍ እንደተወሰደ ተደርጎ ይቆጠራል። ሁለተኛው ጠቀሜታ ይኑ /የበግ እንጀት/ በሸኮ ብሔረሰብ ትልቅ መሃላ የሚፈፀምበት ነው። በወንዙ ዳር አካባቢ ሁለት ረገርኘርም እንጨቶች ተፈርቀው ይተከላሉ የበጉ አንጀት በሥርዓት ከወጣ በኋላ በሁለቱ እንጨቶች ላይና ታች ላይ አንጀቱ ይታሰራል። መካከሉም ክፍት ይሆናል በዚህ ክፍት ቦታ የገዳይ ቤተሰብ አራት የሟች ቤተሰብ አራት ሆነው እጅ ለእጅ በመያያዝ በቡርጃቡ መሪነት በአንጀቱ መካከል አራት ጊዜ ያልፋሉ። እጅ ለእጅ አይላቀቁም። ይህም በክፉ ላለመተያየት ቃል የሚገቡበትና አንድነታቸውን የሚገልፁበት ነው።

በአንጀት መካከል የመሹለኩ ሥራ ከተከናወነ በኋላ ሁለቱ እንጨቶች በቡርጃቡ ጋደም ይደረጋሉ። ይኑ/አንጀቱም/ ይረግባል። ትርጉሙም በመካከላችን የተፈጠረው አለመግባባት እንደዚህ አንጀት ይርገብ ማለት ነው። ከዚህ በኋላ አንጀቱ በወራጁ ወንዝ ውስጥ ይጣላል። ምክንያቱም ጥሉ እንደውኃ ይቀዝቅዝ ከመካከላችን ይጥፋ ማለት ነው። በሸኮ ብሔረሰብ አንጀት ለሰዎች የጥል ማምለጫ እንደሆን ይታመናል። በተጨማሪም እርግማንና ጥላቻን መሸሎኪያና መሸሸጊያ እንደሆን ምሳሌ ነው። የታረደው በግ የሟችና የገዳይ ቤተሰብ አይበሉም። ቡርጃብ ነው ወደ ቤቱ ወስዶ የሚበላው።



በእርቅ ሶኅ ሥርዓት ወቅት ይኑ (በበግ እንጀት መሀል እየሾለኩ መሃላ ሲፈፅሙ

ሌላው በበርቱላ/በእርቅ/ ሥርዓት የሚያስፈልገው ቀርድ ነው። ቀርድ በብሔረሰቡ እምነት የቂም ማድረቂያ ነው። በቀርድ የሚፈፀም እርቅ በግጭት ውስጥ የገቡት አካላት የበሉትና የጠጡት እንዲስማማቸው የማድረግ ኃይል አለው ተብሎ ይታመናል። ነገር ግን በቀርድ ያልተከናወነ እርቅ በግጭት ውስጥ የገቡ አካላት የመበሉትና የሚጠጡት አይስማማቸውም የሚል አስተሳሰብ መኖሩን የመረጃ አቀባዮቼ ገልፀውልኛል። ቀርድ የሚገኘው ከትልልቅ ዛፎች ሥር ጥቅጥቅ ካለ ጫካ ውስጥ ነው። የቀርድ ተክል እንዶድ መሰል ሲሆን ቅጠሉ ሰፊና ደንዳና ነው። ቀርድ በጣም ቀዝቃዛ ተክል ነው። ለቅዝቃዜው መንስኤ በዛፍ ስር መገኘቱና በጣም የተጠቀጠቀ ደን ውስጥ መብቀሉ ነው።



ቡርጃብ ለእርቅ የሚሆን ቀርዲ ሲያዘጋጅና መጀመሪያ ራሱን ሲቀባ

በአርቅ ሥነ-ሥርዓት ወቅት ቀርድ ተቆርጦ ከተዘጋጀ በኋላ በአፈርና በበጠጥ ይታሻል፡፡ የቀርድ ዝግጅት የሚከናወነው በቡርጃብ ነው፡፡ ቡርጃቡ ቀርድውን በአፈርና በበጠጥ አሽቶ መጀመሪያ የራሱን እንብርትና እንጨን ይቀባል፡፡ በመቀጠል የሟችና የገዳይ ቤተሰቦችን አቀራርቦ ተራ በተራ በማስለፍ በቀርዱው እንብርትና እንጫቸው አካባቢ ይቀባቸዋል፡፡ ቀርድው የተመረጠበትና እንብርት ላይ የሚቀባበት ምክንያት በሰዎች መካከል በተፈጠረው ግጭት ሰበብ አንጀታቸው አሩል ተናደዋል፡፡ ስለሆነም ቀርድ ቀዝቃዛ ተክል በመሆኑ ንዴታቸውን ለማብረድ ነው፡፡ ጥሉም እንደቀርዲው እንዲቀዘቅዝ ነው፡፡ ቀርድ ከተቀባ በኋላ ቂም የሚይዝና ነገር የሚፈልግ ሰው በክሉ ህግ የተወገዘ ስለሆነ የተባሉ ሰዎች ከልባቸው ይታረቃሉ፡፡ ዳግሞ ጥል አያነሱም፡፡



በእርቅ ስነ ስርዓት ወቅት ሁለቱን ባላንጣዎች በርጃብ በቀርዲ እየቀባ ሲያስታርቅ

በእርቅ ስነ-ስርዓት ከሚያገለግሉት መካከል አፀ አንዱ ነው። አፀ በአማርኛ ሰርጤ ይሉታል። አፀ በምግብ መስል ተክል ነው። በበርቴማ ሥርዓት በወንዙ ዳር ቡርጃብ አፀውን ይተክላል። ከወንዙ ማዶ ያሉት የሟች ቤተሰቦች ወደ ወንዙ ሲመጡ የገዳዩ ቤተሰቦች አፀውን በጦር ወግተው ይጥሉታል። በዚህን ጊዜ የሟች ቤተሰብ ወደ ኋላ ይመለሳል። ሲመለሱም አሁንም አልተዋችሁንም፤ ልትወጉን ነው፤ አሁንስ በዛ እኛም ወንዶች ነን ከእንግዲህ ይለይልናል በማለት ይናገራሉ። ባህላዊ ህግ ስለሆነ የሰውዬውን መወጋትና መሞት ለማስታወስ ነው። በዚህን ጊዜ ቡርጃቡ ለህግና ሥነ ሥርዓቱ እንጂ እናንተን ለመውጋት አይደለም በማለት ይናገራል። ለሁለተኛ ጊዜ አፀው ይተከልና የገዳይና የሟች ቤተሰብ በጋራ ጦራቸውን ይሰኩበታል። በተለይም ገዳዩና የሟቹ ወንድም ፊት ለፊት ቆመው ጦራቸውን ይሰካሉ። በመጨረሻ አፀው ይወድቅና ውኃ ውስጥ ይጣላል። የጦሩ በአፀ ላይ መሰካት ሟቹ በጦር ተወግቶ መሞቱን ለማስታወስ ነው። ከዚህ ሥነ-ሥርዓት በኋላ ጠብ አቆመ። በጦር እንወጋጋም በሁላም እንንተር ብለው ጦር ላያነሱና ሬብሻ ላይፈጥሩ ቃል የሚገቡበት ነው።



ለእርቅ ማፈፀሚያ የሚሆነውን እፁ ሲተክሉና ገዳዩ በጦር ሲወጋው

በእርቅ ስነ-ሥርዓት ላይ ከሚከናወኑት መካከል ዶሮ ታርዶና ተገንዞ የሚቀርብበት አንዱ ነው። ዶሮው በዑርጃው አማካይነት ታርዶ ከተገነዘ በኋላ ሟቹ በሞተበት አካባቢ ይቀበራል። በሁለቱ ባላንጣዎች መካከል የተፈጠረው አለመግባባት ለመጨረሻ ጊዜ ይቀበር ከዚህ በኋላ ላለፈ ጥል ወደ ኋላ አንመለስም። በዚሁ ይብቃ የሀከትና የግጭት መንፈስ ከኛ ይራቅ ማለት ነው።

ለካሣ የቀረበውን ሰው ዑርጃው አይቶ ካረጋገጠ በኋላ ለሟች ቤተሰብ ያስረክባል። የተሰጠውም ሰው ከሟች ቤተሰብ ጋር ይቀላቀላል። ሴት ከሆነች ለሟች ወንድም ትሰጣለች ወንድም ከሆነ ሟቹ እህት ካለው እህቱን ያገባል። የሞተው እህትና ወንድም ከሌለው በዝምድና ቀረቤታ ያለው ተመርጦ እንዲጋቡ ይደረጋል። የበጉ አንጀት/ደነ/፣ የቀርድ፣ የእፁ፣ የዶሮ መታረድ ሥነ-ሥርዓት ከተከናወነና ለካሣ የቀረበው ሰው ወይም እንስሳት እርክክብ ከተፈፀመ በኋላ የሚፈፀመው ሥነ-ሥርዓት የእህል ዘር ቀመሣ ነው። የእህል ዘር የሚባለው ባካ፣ከቲ፣አማ፣እና ሌሎችም ናቸው። የገዳይና የሟች ቤተሰብ በሰልፍ እንዲቆሙ ይደረጋል ከሁለቱም መሀል ዑርጃብ ይቆማል። ከየእህል ዘሮች ዑርጃብ እየቀመሰ የተሰለፉት ሰዎች ተራ በተራ እየተቀባበሉ እንዲቀምሱ ይደረጋል። ሁሉም ቀምሰው ከጨረሱ በኋላ አስታራቂ ሽማግሌዎች ይቆማሉ። መጀመሪያ ዑርጃብ ይመርቃል። በመቀጠል ሽማግሌዎች ተራ በተራ የምርቃት ሥነ-ሥርዓት


ያካሂዳሉ። ሁሉም በስነ ስርዓት ምርቃቱን ተቀብለው የእርቅ ስነ-ሥርዓቱ ገዳዩና የሟች ቤተሰብን በማሳሳም ይጠናቀቃል።



በነብስ ገድያ ግጭት ለካሳ የቀረበችውን ልጃገረድ በ·ርጃብ ተቀብሉ ለሟች ቤተሰብ ሲያስረክብ

ከወንዝ ዳር የተከናወነው የእርቅ ሥነ-ሥርዓት ከተጠናቀቀ በኋላ ወደ ገዳይ ቤተሰብ ቤት ያሔዳል። በገዳይ ቤተሰብ ቤት ሁለት ወይፈን ይታረዳል። የተለያዩ ባህላዊ መጠጦች ይዘጋጃሉ። የሟች ቤተሰብና አስታራቂ ሽማግሌዎች ወደ ድግስ ቤት ሔደው ይበላሉ። ይጠጣሉ። የገበዛው ሥነ-ሥርዓት የሚጀምረው በበ·ርጃቡ አማካይነት አንድ ብርጭቆ ጠጅ ተሞልቶ ገዳዩና የሟቹ ወንድም በጋራ እንዲጠጡ በማድረግ ነው። ይህም እርቅ መውረዱን ለማመልከት ነው። ቂም በቀል አበቃ። በዘሁ መተያየት ቀረ። እንደቀድሞው ተግባብቶ በሰላም መኖር ተጀመረ። የሚለውን ያመለክታል። በድግሱ ቤት ይዘፈናል ይጨፈራል። መብላት መጠጣትና መደሰት በሁሉም ተሳታፊዎች ይታያል። ከዚህ ስነ-ስርዓት በኋላ እርቅ ወርዷል። ሁሉም ወደልማት ሥራ ይሠማራሉ።





እርቅ ከተፈፀመ በኋላ የሟችና የገዳይ ቤተሰብ በአንድ ላይ ሆነው ሲበሉና ሲጠጡ

ከእርቅ ሥነ ሥርዓት በኋላ ገዳይና የሟች ወንድም በአንድ ብርጭቆ ሲጠጡ

### 4.2.2 የጎሣዎች ግጭትና አፈታቱ

በምዕራፍ ሁለት እንደተገለፀው የሸኮ ብሔረሰብ በብዙ ጎሣዎች የተከፋፈለ ነው፡፡ እነዚህ ጎሳዎች ተቀራርበው የሚኖሩ ስለሆነ በግንኙነታቸው ግጭቶች ይፈጠራሉ፡፡ በጎሣዎች መካከል ከሚፈጠሩ ግጭቶች ዋና ዋናዎቹ በለቅሶ፣ዘፈንና ዓመታዊ በዓላት ጭፈራ ላይ፣ አንዱ ጎሣ የሌለውን ጎሣ የመናቅና የበታች አድርጎ ከመመልከት የሚመነጭ፣ በወሰን፣ በግጦሽና ከብቶች ውኃ በሚጠጡበት ቦታና በሌሎችም ምክንያቶች ጎራ ለይተው በቡድን ይጋጫሉ፡፡

ከመረጃ አቀባዮች ከተገኘው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው በጎሣዎች መካከል ጎልቶ የሚታየው ግጭት በለቅሶ፣ በሰርግና በዘፈን ላይ በሚከናወኑ ጭፈራዎች ላይ ነው፡፡ በሸኮ ብሔረሰብ ሰው ሲሞት ለቅሶ የሚሄዱ ሰዎች ጋሻ፣ ጦር፣የነብር ቆዳ፣የጎሽ ቀንድ እና ሌሎችንም ጌጣጌጦች ይዞ መሄድ የተለመደ ነው፡፡ በለቅሶውም ሥነ-ሥርዓት ጭፈራ ሲጀመር ጎሣዎች ጎራ ለይተው ይፋጨፍራሉ፡፡

አንዳንድ ምግባረ ብልሹ የሆኑ ወጣቶችና ጎልማሶች ከጎሣቸው ውጭ በሌላው ጎሣ መካከል ገብተው ይጨፍራሉ። የሰው ጋሻም ይወጋሉ። ጋሻቸው የተወጋባቸው የጎሳ አባላትና በጭፈራቸው ጣልቃ የተገባባቸው ቡድኖች ለምን ያባታችን ጋሻ ይወጋል? ለምንስ ከኛ ጎሣ ተቀላቅሉ ይጨፈራል በማለት ረብሻ ያነሳሉ። ሌላው ግጭት የሚነሳበት ጉዳይ የአንዱ ጎሣ አባል ከሌላው የጎሣ አባል ሚስት፣የወንድም ሚስትና የዘመድ ሚስት ጋር ሲጨፍር ከታየ እንደ ድፍረት ስለሚቆጠር ጥል ይፈጠራል። ድብድብ ሊነሳ ይችላል። በዘፈን ላይ በሚደረጉ ጭፈራዎች አንደኛው የጎሣ አባል ከሌላው የጎሣ አባል መካከል ገብቶ ሲጨፍር የመጋፋትና የሌሎችን ቡድኖች የጭፈራ ጊዜና ቦታ የሚሻማ ሲሆንና ልታይ ልታይ ማለቱን ካበዛው የዚህኛው የጎሣ አባላት እልህ ውስጥ ስለሚገቡ ረብሻ ይቀሰቀሳል።

በጎሣዎች መካከል ከሚፈጠሩ ግጭቶች አንዱ በድንበር፣ በግጦሽ ቦታና ከብቶች ውኃ በሚጠጡበት ወንዝ አካባቢ ነው። ጎሣዎች ተቀራርበው የሚኖሩ ስለሆነ በእርሻ ማሳ፣ በቡና አትክልትና በከብት ግጦሽ ቦታ አንዱ የሌላውን ድንበር ሲገፋ ረብሻ ይፈጠራል። ከብቶች ወደ ግጦሽ ቦታ ሲሄዱ የአንዱ ጎሣ አባል ከብቶች ወደ ሌላው የጎሣ አባል የግጦሽ ቦታ ከገቡ ከብቶችን የመደብደብ፣ ባለቤቱንም የመዘለፍ ሁኔታ ይከሰታል። ከብቶቹ የተደበደቡበትና የተዘለፈው ሰው ዝም ብሎ አይመለከትም። የአፀፋ እርምጃ ይወስዳል። በዚህ ጊዜ ረብሻ ይቀሰቀሳል።

ሌላው ከብቶች ውኃ የሚጠጡበት ወንዝ የጋራ ከሆነ፣ወደ ጠብ ሊያመሩ የሚችሉ የተለያዩ ሁኔታዎች ወይም ሰበቦች ይፈጠራሉ። የአንዱ ጎሣ በሬ ከሌላው ጋር ውጊያ ይገጥማል። አውራ በሬዎች ሥሪያ ያነሳሉ። በዚህ ጊዜ ትርምስ ይፈጠራል። ከብቶች ገደል የመግባት ዕድል ሊገጥማቸው ይችላል። ወንዙ ትልቅ ከሆነም በውኃ የሚወሰዱ ከብቶች ይኖራሉ። በተጨማሪም የኔ ከብቶች ቀድመው ይጠጡ የናንተ ይቆዩ የሚል ሀሳብ ይመጣል። ከብቶችንም ቀላቅሎ የመውሰድ አጋጣሚ ይኖራል። በነዚህ ምክንያቶች አለመግባባት ይፈጠራል።

በጎሣዎች መካከል ጎልቶ የሚታየው ሌላው ጥል መጥፎ ስድብ ነው። በተለይ ጎሣን የማናናቅ፣ የማንቋሸሽና የቤታች አድርጎ ከማየት የሚሰነዘር ስድብ ግጭቱን የሚያባብስና ማቆሚያ የሌለው እንዲሆን የሚያደርግ ነው።

በጎሣና በጎሣ መካከል የሚከሰት ግጭት በጣም አደገኛና በህዝቦች መካከል የከፋ እልቂት ሊያስከትል የሚችል መሆኑ ይታወቃል። ስለዚህ እያንዳንዱ የጎሣ መሪ ግጭት ሲቀሰቀስ የጠርቱግ ስነሥርዓት እንዲከናወን ጥረት ያደርጋል። ጥሉ የቡድን ስለሆነ ጉዳት ከመድረሱ በፊት የጎሣ መሪዎች ቁጥጥርና ክትትል ያደርጋሉ። በአንድ አካባቢ የጎሣ ግጭት ከተነሳ ወይም ሊነሳ ይችላል ተብሎ ሲጠረጠር የጎሣ መሪዎች በጋራ በመሆን ተከታትለው የማርገብና

የሚቃለል ሥራ ይሠራሉ። በጎሣና በጎሣ መካከል ማህበራዊ ግንኙነቱ ተቋርጦ ወደ መቃቃርና ግድያ ከመሄዱ በፊት አፋጣኝ መፍትሔ ይፈለጋል። ጉዳቱ የከፋ ሊሆን ስለሚችል ጊዜ አይሰጠውም። እንደ ሌሎች የግጭት ዓይነቶች በመላላክና ሽማግሌ በመምረጥ አይጓተትም። ረጅም ቀጠሮ አይያዝለትም። ሁሉም የጎሣ መሪዎች በፍጥነትና በትጋት አቋም ይወስዳሉ። አፋጣኝ መፍትሔም ያስገኛል።

ግጭት መከሰቱ ሲረጋገጥ ባላባቶች የጎሣ መሪዎች ተገናኝተው ይወያያሉ። ግንኙነት ሊቋረጥ አይችልም ሰርግ፣ ለቅሶ፣ ገበያ፣ ዓመታዊ በዓላትና ሌሎችም ማህበራዊ ግንኙነቶች የማይቀሩ ናቸው። ስለዚህ የጎሣ መሪዎች ልጆቻችን ተጋጭተዋል አንዱ ሌላውን ለማጥቃት እያደባ ነው። መፍትሔ መፈለግ አለብን በማለት ይነጋገራሉ። ሁከትና ብጥብጥ ሳይፈጠር ግጭቱ መርገብ አለበት። የጉዳዩ አሳሳቢነት በሁሉም የጎሣ መሪዎች ዘንድ ትኩረት ይደረግበታል። በብሔረሰቡ የጎሣ ግጭት ሲፈጠር የእርቅ ሥነ-ሥርዓቱን ለማከናወን ካሉት የጎሣ መሪዎች መካከል አንዱ ይመረጣል አመራረጡ ባለው የተሻለ ዕውቀት፣ በማህበራዊ ተቀባይነትና የጎሣ መሪው የክብር ደረጃ ከሌሎች የተሻለ መሆኑ ታምኖበት ነው። የምርጫው ሥነ-ሥርዓት ከተከናወነ በኋላ በርቱማው የሚካሄደው በተመረጠው የጎሣ መሪ ደጅ ነው።

የተመረጠው የጎሣ መሪ ሌሎችን የጎሣ መሪዎች በሰብሳቢነት ይመራል። የሚሰበሰቡበትን ቀንና ሰዓት ቢጋራ ያስወስናል። በያዙት ቀጠሮ ቀንም የተከሰተው ግጭት የሚቃለልበትን መንገድ ለመፈለግ ዕቅድ ያወጣሉ። በግጭት ውስጥ የገቡ አካላት ለእርቅ ከመምጣታቸው በፊት እያንዳንዱ የጎሣ መሪ በሥሩ ያሉት የጎሣ አባላት ለእርቅ እንዲዘጋጁ የማድረግ ኃላፊነት ይወስዳል። ጥፋት ፈፀሙ ወይም ለግጭት መንስኤ የሆኑ ግለሰቦችና ቡድኖችን የማጣራትና የመለየት ሥራ ይከናወናል። ይህንንም በአግባቡ ማከናወኑን ለተመረጠው የጎሣ መሪ ያሳውቃል። የጎሣ መሪዎች በየአካባቢያቸው ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት እንዲታገሱ ያስጠነቅቃሉ። ምክንያቱም የተጀመረው እርቅ ከመፈፀሙ በፊት ችግር እንዳይፈጠር ነው።

በግጭቱ ውስጥ የገቡት ቡድኖች ወይም ግለሰቦች ተለይተው ከታወቁ በኋላ በጎሣ መሪዎችና ባላባቶች አማካይነት በተመረጠው ባላባት ደጅ ይመጣሉ። በእርቅ ስነ-ስርዓቱ በማስታረቅ ሥራ የሚሳተፉት የጎሣ መሪዎች ቢሆኑም ጉዳዩ ትኩረት መስጠቱን ለማመልከት ቃልቾች፣ ቡርጃዎችና ታዋቂ የአገር ሽማግሌዎች ይጨመራሉ። በግጭት ውስጥ የገቡ አካላት እርቅ የሚከናወንበት ቦታ ሲመጡ በአንድ ላይ አይቀመጡም። በየጎሣቸውና ቡድናቸው ፈንጠር ብለው ለየብቻ ነው። ከዚያም አስታራቂዎች ተራ በተራ እየጠሩ ስለጠቡ መንስኤ ያጣራሉ። የተጣሉ ሰዎች ለሚጠየቁት ጥያቄ ውሸት ቢናገሩ የቃልቾች የጎሣ መሪዎች የከይናብ አምላክ አደጋ እንደሚያደርስባቸውና በእውነት የማይናገረውን በራ/እርግማን/ እንደሚፈፀም ያስጠነቅቃሉ።

የጠበ ምክንያት ከተመረመረ በኋላ ቀድሞ ጠብ ያነሳው ማን እንደሆነ ይጣራል፡፡ በጥል ውስጥ የገቡ አካላት የተጣሉበትን ምክንያትና የጠቡን ቀስቃሽ በትክክል የማይናገሩና መተማመን ከሌለ ምስክር ይቀጠራል፡፡ የሚጠሩ ምስክሮችም በጎሣ መሪ፣በቃልቻና በታዋቂ የአገር ሽማግሌ ፊት መዋሸት ስለሚፈሩ የተደረገውን ሁሉ በትክክል ነው የሚናገሩት፡፡ ስለዚህ ጠቡን የጫረውም ሆነ የአፀፋ እርምጃ የወሰደው አካል እንደሚመሰክርባቸው ስለሚያውቁ የፈፀሙትን አይደብቁም፡፡ ያባቴን ጋሻ ስለወጋ ወጋሁት ከወንድሜ ሚስት ጋር ስለጨፈረ ተናድጄ መታሁት፡፡ በኔ የግጦሽ ቦታ ከብቶችን ስላስግራበትና የኔ ከብቶች ውኃ እየጠጡ ሳለ የሱን ከብቶች አቀላቅሎ ሁከት ስለፈጠረ ሰደብኩት ድንበሬን ስለገፋ ደበደብኩት በማለት እውነቱን ለማረጋገጥ የአይን ምስክሮችን እየጠሩ ለአስታራቂዎች ይናገራሉ፡፡

አስታራቂ ሽማግሌዎች የሁለቱንም ወገን ሀሳብ ከሰሙ በኋላ የማግባባት ሥራ ይሠራሉ፡፡ ያባትህ ጋሻ እንዳይወጋ ከፈለክ ለምን ለቅሶ ቤት አመጣህ? የተወጋው በጭፈራ ላይ ነው፡፡ የሚጨፍር ሰው ስሜት ውስጥ ይገባል፡፡ ስለዚህ ሆን ብሎ ለመውጋት ሳይሆን በጭፈራው የጠለቀ /ኃይለኛ ስሜት ውስጥ ገብቶ ነው፡፡ መታገስ ነበረብህ ይባላል፡፡ በባህላችን መጫወትና መጨፈር ከአባቶቻችን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ነው፡፡ ቢሆንም ከሰው ሚስት ጋር መጨፈር ጥሩ ስለማይሆን ከዛሬ ጀምሮ የዚህ አይነት ድርጊት አትፈፅሙ፡፡ ያለፈው አለፈ በማለት በሰሩት ሥራ እንዲፀፀቱ ተደርጎ ይነገራል፡፡ በከብት ውኃ መጠጫ ቦታ ለሚነሳ ጥል አማራጭ ቦታ ካለ የየግል ከብት ማጠጫ ቦታ ይደለደላል፡፡ አማራጭ ቦታ ከሌለ ግን ተራ በተራ ተመካክረው እንዲጠቀሙ ይደረጋል፡፡ የግጦሽ ቦታው የጋራ ከሆነ በምክክርና በመግባባት እንዲጠቀሙ ይሆናል፡ የየግላቸው ከሆነም አንዱ የሌላውን የግጦሽ ቦታ እንዳይጠቀም ማስጠንቀቂያና ምክር ይሰጣል፡ እያንዳንዱ የየራሱን በመጠቀም የሌሎችን አለመንካት ተከባብሮ ለመኖር እንደሚያስችል ይነገራል፡፡

የጎሣ መሪው ከአስታራቂ ሽማግሎች ጋር የማጣራቱን ሥራ እንደጨረሰ በመጨረሻም በባህላዊ ህግና ሥርዓቱ መሠረት ዳግም ጠብ እንዳይነሳ ቃል የሚገቡበት መሃላ ይከናወናል፡፡ በባላባቱና በጎሣ መሪዎች አስተባባሪነት እንቁላል፣ አመድ፣ጭራ፣ ጦር፣ዞማ፣ ጠገራ፣በአንድ እቃ ላይ ይቀመጣሉ፡፡ እነዚህ ሁሉ በአንድ ከተቀመጡ በኋላ በሽማግሌዎች ፊት ለፊት እንዲቀመጡ ይደረጋል፡፡ በግጭት ውስጥ የገቡ አካላት አንድ በአንድ እየተጠሩ በየተራ እንዲራመዱ ይደረጋል፡፡ በሸኮ ብሔረሰብ ይህ ትልቅ መሃላ ነው፡፡ እንደዚህ አይነት መሃላ የሚፈፅም ትክክለኛ ና እውነተኛ ሰው ብቻ ነው፡፡ የመሃላው ምስጢር ዳግም ጠብ አናነሳም ክህደት አንፈፅምም በክፉ አንተያይም ብለው ቃል የሚገቡበት ሥነ-ሥርዓት ነው፡ ከዚህ የመሃላ ስነ-ሥርዓት በኋላ ተግባብተው በመፈቃቀር ኑሮአቸውን ይመራሉ፡፡ ለሌሎችም አባላት ጥሩ አርአያ ይሆናሉ፡፡

በመጨረሻ የሚከናወነው የሚበላና የሚጠጣ ነገር ነው። ግጭቱ የቡድን በመሆኑ የበርቱማ ሥነ-ሥርዓት ሲቋጭ ክብት ይታረዳል። የመጠጥ አይነት ይዘጋጃል። ለእርድና ለሚጠጣ ነገር የሚዘጋጀው በጎሣ መሪዎች አስተባባሪነት ከእያንዳንዱ የጎሣ አባል መዋጮ በመጠየቅ ነው። በተጨማሪ በእርቁ ስነ-ሥርዓት ላይ ጥፋተኛ የሆኑት አካላት እንደጥፋታቸው ክብደትና ቅለት እየታየ ከከፍተኛ የከብትና የገንዘብ ቅጣት እስከ ዝቅተኛ የገንዘብ ቅጣት የሚጣል ስለሆነ ለእርቁ ለሚዘጋጀው እርድና መጠጥ እንዲውል ይደረጋል። የአካባቢው ህዝብ በጋራ ሆኖ ይበላል ይጠጣል። የተጣሉ አካላት በጋራ በአንድ ማዕድ ይበላሉ ይጠጣሉ። ይዘፍናሉ። ይጨፍራሉ። ባላባቶችና አስታራቂዎችም የምርቃት ሥነ-ሥርዓት ያካሂዳሉ። ሁሉም በመደሰት በልቶ ጠጥቶ ወደ የአካባቢው ይሄዳል። ከዚህ በኋላ ሁሉም ተከባብረው በፍቅርና በመግባባት ይኖራሉ።

በሸኮ ብሔረሰብ በድንበር ጉዳይ ድርድር አይደረግም። አንተ ከዚህ ተመለስ። አንተም ከዚህ ወዲያ ያለው ይበቃህ የሚለው ተቀባይነት የለውም በትክክለኛውና እውነተኛው ወሰን ላይ ካልሆነ በድንበር የሚዋሰኑት ሰዎች በድርድር በሚደረግ መግባባት አይረኩም። ከልብም አይታረቁም። ድንበሩ በጥንቱና በእውነተኛው ቦታ መፅናት አለበት ብለው ያምናሉ። በባህላቸው ድንበር መግፋት በጣም ነውር ነው። ድንበር የሚገፋ ሰው እንደሰይጣን ነው የሚቆጠረው። የሰው ድንበር የሚገፋ ሰው ማህበራዊ መገለል ይገጥመዋል። ፈጣሪ መጥፎ ነገር ያደርስበታል የሚል እምነት ስላላቸው እንዲህ አይነቱን ሰው ጓደኛና ዘመድ ይርቀዋል።

በሸኮ ባህል ድንበር የሚገፋበት አካል በትክክለኛው ወሰን ላይ ግራዋ በመትከል ወደ አካባቢው የጎሣ መሪ በመሄድ ክስ ይመሰርታል። ክስ የቀረበለት የጎሣ መሪ ድንበር ገፋ ተብሎ የተከሰሰው ሰው ተጠርቶ እንዲመጣ ያዛል። የጥሪ መልዕክት የደረሰው ሰው የጎሣ መሪው ፊት ቀርቦ ይጠየቃል። ጉዳዩ ወደ የጎሣ መሪው መድረሱ ክብደት አለው። ድንበር የገፋው ሰው በቀላሉ አለመስተቱን ይገነዘባል። ድርጊቱን መፈፀሙን የሚያምን ከሆነ በባህሉ የሚከናወን የእርቅ ሥነ-ሥርዓት አለ። ይህም በቡርጃብ ድንበሩ ተገፋ በተባለው ቦታ በመሄድ የተተከለውን ግራዋ ያመጣል። ቀርድ እንዲዘጋጅ ያደርጋል። የበግ ጆሮ ተቆርጦ ሲደማ ደሙ ከቀርድ ጋር ይጨቃጨቃል። ሁለቱ በድንበር የተጣሉ ሰዎች በቡርጃብ አማካይነት እንብርትና አገጫቸውን ይቀባሉ። ከዚህ በኋላ እርቅ ወረደ ቂም መያያዝ ቀመ በሰላም ኑሩ ድንበሩም በተተከለው ግራዋ የሙ፣ ይሁን ማለት ነው። ቡርጃቡ ግራዋውን ነቅሎ ቀርድ አዘጋጅቶ ከበግ ደም ጋር በመጨቃጨቅ የሚያስታርቀው ድንበር የገፋው ሰው የፈፀመውን ስህተት ስላመነ እንዳይሞት ነው። ነገር ግን ድንበር የገፋው የማያምን ከሆነ በባህላዊ ህጉ በጎሣ መሪው፣በቡርጃብና ያገር ሽማግሌዎች አስተባባሪነት በራ/እርግማን/ ይደረጋል። ተደጋግሞ እንደተነገረው በብሔረሰቡ እርግማን መጥፎ ነገር እንደሚያመጣ ስለሚታወቅ ክህደት መፈፀም አይዘወተርም።

### 4.2.3 ግሽ/ጠለፋ/

ግሽ/ጠለፋ/ በሸኮ ብሔረሰብ መካከል የሚከናወንና የሚታወቅ የጋብቻ ዓይነት ነው፡፡ ጠለፋ በፍላጎት ወይም በጉልበት በኃይል ልጃገረድን አስገድዶ በመውሰድ የትዳር ጓደኛ ማድረግ ነው፡፡

በሸኮ ብሔረሰብ ዘንድ ግሽ/ጠለፋ/ ከጥንት ጀምሮ የሚከናወን ነው፡፡ ድርጊቱ የሚከናወነው በሁለት መንገድ ነው፡፡ የመጀመሪያው በመፈቃቀድ በፍላጎት ላይ የተመሠረተ ጠለፋ ነው፡፡ ይህም ጠላፊው ከምትጠለፈው ልጅ ጋር ተግባብቶ በመወያየት የሚፈፀም ነው፡፡ ሁለቱ መግባባትና መፈቃቀራቸው እየጠነከረ ሲመጣና ከሁለቱ ቤተሰቦች የአንደኛው መጋባታቸውን የማይፈልጉት መሆኑን ሲያረጋግጡ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ልጁ ጠልፎ እንዲወስዳት ተስማምተው የሚፈፅሙት ነው፡፡

ሌላው የጠለፋ አፈፃፀም በወንዱ ውሳኔ በጉልበት የሚደረግ ነው፡፡ ይህን ድርጊት የሚፈፅመው አካል ከልጅቱም ሆነ ከቤተሰብ ፈቃደኝነት ሳይኖር ሲቀር ነው፡፡

ግሾ በሸኮ ብሔረሰብ የሚወገዝ ነው፡፡ በተለይ ከፍላጎት ውጭ የሚከናወን ጠለፋ በብሔረሰቡ የማይፈለግና ከፍተኛ ችግር የሚፈጥር ነው፡፡ ምክንያቱም የሴቷን ፍላጎት አይጠብቅም፡፡ በዚህም ምክንያት በተጠላፊዋ ልጅ ላይ አካላዊና አእምሮአዊ ጉዳት ያደርሳል፡፡ ይህን ጉዳት የተጠላፊዋ ቤተሰቦች ስለሚረዱ የመጠለፍ ዕድል የገጠማት ልጅ ቤተሰቦች ጦር ሰብቀው በመውጣት ከጠላፊው ጋር ውጊያ ይገጥማሉ፡፡ መገዳደል ደረጃ ሊደርሱ ይችላሉ፡፡

በመሆኑም ከፍላጎት ውጭ የሚፈፀም ጠለፋ ብዙ ችግሮች አሉበት፡፡ በሸኮ ብሔረሰብ ለግሽ/ጠለፋ/ መከናወን ምክንያት የሚሆኑት ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1ኛ/ በጎሣና በጎሣ መካከል የዘር ልዩነት ኖሮ የልጅቷ ቤተሰቦች ልጃቸውን ለጋብቻ ሲጠየቁ በዘሩ እኛ አለመሆን ምክንያት ለመስጠት ፈቃደኛ ሳይሆኑ ሲቀሩ

2ኛ/ የልጁ ስንፍና፣ መጥፎ ባህሪይ፣ እንዲሁም ኑሮውን በአግባቡ ለመምራት አይችልም የሚለው በልጅቱና በቤተሰብ ዘንድ የሚታወቅ ከሆነ ለትዳር ቢጠይቅ ፈቃደኛ ካለመሆን የሚመነጭ

3ኛ/ በልጅቱ ውበት በመማረክ ድንገተኛ ፍቅር ይዞት ግብታዊ በሆነ መንገድ ተነሳስቶ የሚፈፀም

4ኛ/ በገንዘብ እጦት ምክንያት ለጥሎሽ የሚከፈል ሀብት ሳይኖረው ሲቀር በድርድር ማግኘት እንደማይችል ሲረዳ ጠለፋን እንደ አማራጭ መጠቀም የሚሉ ናቸው፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ግሸ ሲፈፀም ጠላፊው የጠለፋትን ልጅ በስውር ቦታ ያስቀምጣታል። ጠላፊው ልጅ ከወላጆቹ ሳይመካከር የፈፀመው ከሆነ የቅርብ ዘመድ ጋር ሂዶ መጥለፉን ለወላጆች እንዲነግሩ ያሳውቃል። ይህም ስሁለት ነገር ይጠቅማል የመጀመሪያው የጠለፈው እሱ መሆኑ ከታወቀ የልጅቷ ቤተሰቦች በቤተሰቦቹና በቅርብ ዘመዶቹ ላይ አደጋ እንዳያደርሱ ቤት እንዳያቃጥሉ፣ ተጠንቅቀው እንዲጠብቁ ነው። ሁለተኛው ማግባት መፈለጉንና በራሱ ፈቃድ ጋብቻ መመሥረቱን በማሳወቅ ዕውቅና ለማግኘት ነው።

የልጁ ቤተሰብ የዚህ ዓይነት ዱብዕዳ ሲመጣ ይረበሻሉ። ሀሳብ ውስጥ ይገባሉ። እኛ በአግባቡ መዳር ስንችል ሳንዘጋጅ የዚህ ዓይነት ነገር ማድረግ አልነበረበትም ብለው ይቆጣሉ። ከሰው ጋር ሊያጋድለን ነው ብለው ይበሳጫሉ። ቤተዘመድ ተሰብስቦ የሆነው ሆኗል የሚያዋጣው መፍትሔ መፈለግ ነው በማለት ያግባባል። ቤተሰብም ዕውቅና ይሰጣል። የአካባቢውን ሰው በመጥራት የተወሰነ ዝግጅት ያደርጋል። ባልና ሚስት መሆናቸውን የልጁ ቤተሰብና ዘመድ እንዲያውቁ ያደረጋል።

ያለፍላጎቷ ልጃቸው የተጠለፈችባቸው ቤተሰቦች የጠለፈውን ልጅ የሚያውቁ ወይም ጥቆማ ከደረሳቸው በሱም በቤተሰቦቹ ላይ አደጋ ሊያደርሱ ይችላሉ። በተፈፀመው የጠለፋ ድርጊት ያናደዳሉ። ከፍተኛ ድፍረትና ጥቃት እንደተፈፀመባቸው በመቁጠር በቡድን ተደራጅተው ጠላፊው ሊኖር ይችላል ተብሎ በሚታሰብበት አካባቢ ያንገርብባሉ። ቤት ሊያቃጥሉ ይችላሉ። ድብድብ ሊፈጠር ይችላል። ስለዚህ የጠላፊው ቤተሰብ በጥንቃቄ ነው የሚቀመጡት። ልጃቸው ከተጠለፈችባቸው ቤተሰቦች ዓይን ይሰወራሉ። ጥቃት እንዳይፈፀምባቸው በጥንቃቄ ይከታተላሉ።

የጠላፊው ልጅ ቤተሰብ ልጃቸው መጥለፉን ካረጋገጡበትና ለጋብቻው ዕውቅና ከሰጡበት ሰዓት የምር ቀጣዩ ሥራቸው ለእርቅና ለጥሎሽ የሚሆን ከብት ማፈላለግና አስታራቂ ሽማግሌዎችን ማዘጋጀት ነው። ወደ ልጅቷ ቤተሰብ ሽማግሌ የሚላከው ብዙ ጊዜ ሳይቆይ ወድያውኑ ነው። ምክንያቱም የልጅቷ ቤተሰቦች ተንቀናል በሚል ሀሳብ የከፋ አደጋ ሊያዳርሱ ይችላሉ። ሽማግሌ በወቅቱ ከተላከ በእርቅ ስነ-ሥርዓቱ ወቅት መካረር እንዳይኖር ያግዛል።

ለእርቅ የሚላኩት ሽማግሌዎች ከተመረጡ በኋላ በጠላፊው አባት ቤት ተሰብስበው ይመካከራሉ። ዕቅድ ያወጣሉ። በልጁ ቤተሰብ ቤት የሚበላና የሚጠጣ ከቀመሱ በኋላ ፀሎት በማድረግ ፈጣሪያቸውን ይለምናሉ። የሚሄዱበት ጉዳይ የተሳካ እንዲሆን አምላካቸው እንዲረዳቸው ይማፀናሉ። የልጁ አባትና እናት መንገዱን ቀኝ ያድርግላችሁ። ሰዎችን ያራራላችሁ ብለው ይሸኟቸዋል፤፤

እርቅ ለማውረድ የተላኩት ሽማግሌዎች ወደ ልጅቱ ቤተሰብ ቤት በቀጥታ አይገቡም። በቤተሰቦቿ መኖሪያ ቤት አካባቢ ከሚገኙት ጎረቤቶች መካከል ለልጅቷ ቤተሰቦች የሚቀርቡትንና

የሚገቡበትን በማረጋገጥ ወደተመረጠው ጎረቤት ቤት ይገባሉ:: በልጅቷ ቤት ሰተት ብለው ቢገቡ የልጅቷ ቤተሰቦች ስለተናደዱ ድብድብ ሊነሳ ይችላል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው:: ሽማግሌዎች ያነጋገሩት ጎረቤት የመጡበትን ጉዳይ ካረጋገጡና ከሽማግሎች ጋር ከተነጋገሩ በኋላ ወደልጅቷ ቤተሰብ ቤት ይሄዳል ቀስበቀስ እያዋዛ ካግባባ በኋላ «ሰዎች መጥተዋል:: እርቅም ጠይቀዋል» በማለት ይናገራል:: ጎረቤት በመሆኑና የሰዎችንም ባህሪይ ስለሚረዳ አነጋገሩ በጥንቃቄ ነው:: በባህሉ በጠለፋ እርቅ በመጀመሪያ ቀን እሺ አይባልም:: ጠላፊውና ቤተሰቦቹ መጨነቅ አለባቸው በሚል ሃሳብ ነው:: ስለዚህ ሳምንት እንዲመጡ ይባላል:: መልዕክቱን ያደረሰው ጎረቤት ወደ ሽማግሎች ተመልሶ የተባለውን ያስረዳል:: ሽማግሎችም ቀጠሮውን ተቀብለው ይሄዳሉ::

ሽማግሎች ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ልጅቷ ቤተሰብ ቤት ሲሄዱ በሬ፣ ወይፈን፣ላምና ጊደር በመያዝ ነው ይህም ባህላዊ ህጉ የሚፈቅደው ነው:: የልጅቷ ቤተሰብም የሚበላ ባካ፣ከቴ፣አማ፣ ... የሚጠጣ በረዴ፣አረቂ፣ ጠላ፣ ጨሞ... አዘጋጅተው ይጠብቃሉ:: ሽማግሎች ወደ ልጅቷ ቤተሰብ ቤት ሲደርሱ ከብቶችን በወላጆቿ በር ላይ አስረው ወደ ቤት ይገባሉ:: ቤት ውስጥ ገብተው እየተመጠጡ በስልፍ ቆመው ሦስት ጊዜ ጎንበስ ቀና በማለት ሰላምታ ይሰጣሉ በሸኮ ቋንቋ «ጃሽ» ሰላም ማለት ነው:: ስለዚህ ሦስት ጊዜ «ጃሽ» «ጃሽ»«ጃሽ» ይላሉ::

የሰላምታ ልውውጡ ካለቀ በኋላ ከሽማግሌዎች መካከል አንዱ የመጣነው ልንክስ ነው:: «ጥፋት ፈፅመናል» «ስህተት ሰርተናል» «አጥርዎን ሰብረናል» «ቤቱን ደፍረናል» «ከበርጩማዎ አውርደናል»:: «ፀሐይ አስመትተነዎታል»:: «ስርቆት ፈፅመናል»:: ይህንንም «ጥፋት አምነን እንክሳለን»:: ይላል:: በመቀጠል ቤትዎን በደፈረርንበት አንድ ጊደር፣ አጥርዎን ስለሰበርን አንድ በሬ፣ ከበርጩማዎ በማውረዳችን አንድ ወይፈን፣ በፀሐይ በመመታትዎ አንድ እናት ላም ከስናል ብሎ ያቀርባል:: የተባሉት እንስሳትም በትክክል መጥተው በር ላይ መታሰራቸውን ያስረዳል:: እነዚህ ከብቶች በካሣ መልክ ቢሰጡም በእርቁ ስነ-ስርዓት ወቅት ከሚቀርቡት የከብት ጥሎሽ ጋር አብረው ይታሰባሉ::የልጅቷ ቤተሰብም እንግዶች እንዲቀመጡ ይፈቅዳሉ::

የካሳ ስጦታ ከተከናወነ በኋላ ግጭቱ እየቀዘቀዘ/እየረገበ/ በቤተሰብ ደረጃ የመተያየቱ አዝማሚያ ይታመራል:: ለሦስተኛ ጊዜ አስታራቂ ሽማግሎች ከ 3-7 የሚደርሱ ከብቶች በመያዝ ወደልጅቷ ቤተሰቦች ቤት ይሄዳሉ:: ይህም ጥሎሽ ለመስጠት ነው:: በዚህን ወቅት ጠላፊው አብሮ ይመጣል:: የልጅቷ ቤተሰቦች ቤት ድግስ ይደገሳል:: የጥሎሽ ሥነ-ሥርዓቱ ከተከናወነ በኋላ ጉባኤው ይፋ ይሆናል:: ልጁም የልጅቷን ቤተሰብ ይቅርታ ይጠይቃል:: ሽማግሎች ሁለቱን የተጋቡ አካላት ያስታርቃሉ:: የተዘጋጀው ድግስ ይበላል ይጠጣል ሽማግሎች የምርቃት ስነ-ስርዓት ያካሂዳሉ:: ከዚህ በኋላ አባትና ልጅ ሆነው በሰላም ይኖራሉ::

በብሔረሰቡ ባህል የካሳና የጥሉሽ ስጦታ ተከናውኖ እርቅ ከወረደ በኋላ የልጅቷ እናት ለልጆች ማቋቋሚያ የሚሆን የእህል ዘር ታዘጋጃለች:: አትክልትና ፍራፍሬ ትተክላለች:: የአዝመራውን ወቅት በማረጋገጥ ለእህል፣ለአትክትልትና ፍራፍሬ ማዘጋጃ ቦታ እንዲመቻች ወደ ልጁ ቤተሰብ ቤት መልዕክት ይላካል:: የልጁ ቤተሰብም እንግዶች የሚመጡበትን ቀን ሲያረጋግጡ ቦታውን ያዘጋጃሉ:: ለሚመጡ እንግዶች ማረፊያ ቦታ ይመቻቻል:: ምግብና መጠጥ ይሰናዳል::

የልጅቷ እናት የሚዘራውንና የሚተከለውን ይዛ ስትሄድ ብዙ ወጣቶችን አስከትላ ነው:: ምክንያቱም ብቻዋን ጥካ፣ካቺ፣ቡና፣ብርቱካን፣ሙዝ፣የእህል ዘርና ሌሎችንም መዘራትም ሆነ መትከል አትችልም:: በልጁ ቤተሰብና በልጅቷ ቤት የድግስ ዝግጅት ቢኖርም የልጅቷ እናት የቦርዴ ድፍድፍ በብዛት አዘጋጅታ ይዛ ትሄዳለች:: የሚበላ ምግብም አዘጋጅታ ትይዛለች:: እንግዶች በልጁ ቤት ሲደርሱ አቀባበል ከተደረገላቸው በኋላ ሲበሉና፣ሲጠጡ ሲዘፍኑና ሲጨፍሩ ያድራሉ:: በሚቀጥለው ቀን ዘሩ ይዘራል አትክልትና ፍራፍሬው ይተከላል:: ማታ ማታ ድግሱ እየተበላ እየተጠጣ ይዘፈናል:: ይጨፈራል:: ይህም እርቅ መውረዱንና የልጅቷ ቤተሰቦች ከልብ መታረቃቸውን የሚያረጋግጥ ነው:: ጋብቻውን ወደናል ብለው ማረጋገጣቸውም ነው:: የልጁና የልጅቱ ቤተሰቦችም ስለሚቀላቀሉ ዝምድናው እየተጠናከረ መምጣቱን አመላካች ነው:: ከዚህ በኋላ ልጁና ቤተሰቦቹ ከልጅቷ ቤተሰብ ጋር ይግባባሉ:: በደስታና በመከራ አብረው ይሳተፋሉ:: ልጁም ከልጅቷ ቤተሰብ ጋር በመተጋገዝና በመደጋገፍ በሰላም ይኖራሉ:: ልጆችም ቤተሰብን በሥራ ይረዳሉ::

በልጁና በልጅቱ ስምምነት የሚፈፀም ጠለፋ ከልጁም ሆነ ከልጅቱ ሁኔታ የሚታይ ፍንጭ አለ:: ይህም ለቤተሰቦቻቸውና ለአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ እንዲታወቅ ወይም ጥርጣሬው ጎልቶ እንዲወጣ የሚያደርግ ምልክት ስለሚታይ ነው:: ልጁና ልጅቱ የተግባቡ ስለሆነ ሲወያዩ ሲጫወቱ ይታያሉ:: በተለይ የልጁ ጓደኞች እህትና ወንድሞች እንዲሁም የቅርብ ዘመዶች ሁለቱ ልጆች መፈቃቀራቸውን ሊያውቁ የሚችሉበት አጋጣሚ ሰፊ ይሆናል:: በአካባቢው ወሬው ይናፈሳል:: ይህም በልጁና በልጅቷ ቤተሰቦች ጆሮ ይደርሳል:: ምክንያቱም የልጁና የልጅቱ መቀራረብ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተሰማ ስለሆነ ነው:: በመሆኑም ጠለፋው እንደተከናወነ በቀጣዮቹ ቀናት ወደልጅቷ ቤተሰቦች ሽማግሌ እንዲላክ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ::

በአካባቢው ባህል ግጭት ተፈጥሮ በዝምታ አይታለፍም:: ለተከሰተው ግጭት መፍትሔ ይፈለግለታል:: ስለሆነም የጠላፊው አባትና እናት ወደ ልጅቷ ቤተሰብ ቤት ሽማግሌ በመላክ እርቅ እንዲከናወን ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ:: ታዋቂ የአገር ሽማግሌዎችን በማነጋገር እርቅ እንዲያስፈፅሙላቸው ይጠይቃሉ:: ሽማግሌዎችም እምቢ አይሉም::ምክንያቱም በሽኮ ባህል በማስታረቅ ሥራ መሳተፍ ሞራላዊ ግዴታ ቢኖር በትም ማህበራዊ ከበሬታም ያስገኛልና::

የእርቅ ሥርዓት ለማስፈፀም የተመረጡት ሽማግሌዎች ከልጁ አባት ቤት በመገኘት በጉዳዩ ዙሪያ ይወያያሉ። ጉዳዩ የተሳካ እንዲሆን በጋራ ከፀለዩ በኋላ ወደልጅቷ ቤተሰብ ቤት ይሄዳሉ። በልጅቷ መኖሪያ አካባቢ ሲደርሱ ቀጥታ ቤተሰብ ቤት አይገቡም። ከወላጆቿ ጎረቤት በአንደኛው ቤት ይገባሉ። የመጡበትን ጉዳይ በጥሞና ያስረዳሉ። ጉዳዩ የተነገረው ጎረቤትም ጠለፋው በልጅቷ ፍላጎት ነው ወይስ በጉልበት አስገድዶ ነው የሚለውን ያጣራል። የሚያጣራበት ምክንያት የልጅቷ ወላጆች ሲጠይቁት በአግባቡ መልስ ለመስጠት ነው። በብሔረሰቡ ባህል መዋሸት ነውር ስለሆነ የጠለፋውን ሁኔታ በትክክል ይናገራል።ልጅቷ በራሷ ፍላጎት መሆኑ ይታወቃል።

በሸኮ ባህል ልጃገረድ ክብረ ንጽህና ከሌላት ጋለሞታ ተብላ ክብሯ ይቀንሳል። ስለዚህ የተጠለፈች ልጃገረድ ተመልሳ ወደ ቤተሰብ መምጣቷ በማህበራዊ ግንኙነቷ ላይ ችግር ይፈጥርባታል። ወላጆችም የልጃቸው ሞራል እንዳይነካና በአካባቢው ነዋሪዎች ዘንድ መዘባበቻ እንዳትሆን በማሰብ ለእርቅ ሲጠየቁ እምቢ አይሉም። ወግና ባህሉን ለመጠበቅ ይግደረደራሉ። ልጅቷ ጋለሞታ እየተባለች የትዳር ጓደኛ እንደማታገኝ ስለሚታወቅ እርቁን ይፈልጉታል። ጠላፊውም ይህን ስለሚያውቅ ልጅቷን ከጠለፈ በኋላ የመጀመሪ ርምጃው ክብረ ንፅህናዋን መግሰስ ነው።

በሸኮ ባህል መሠረት በፍላጎት ላይ ተመስርቶ የተፈፀመ ግሽና በኃይል የተፈፀመ ግሽ የግጭት አፈታቱ ይለያያል። በመፈቃቀር ላይ ተመስርቶ የተፈጸመ ከሆነ ሽማግሌዎች ብዙ አያጨናንቁም። ልጆቹ ወደው የፈፀሙት ነው በሸኮ ተረት «ከሞትና ከጋብቻ የሚቀር የለም።» የላሉ። ስለዚህ የልጆ ነገር ሆኖ ራሳቸው ፈፅመውታል ይባላል። የልጅቷ ቤተሰቦችም ንዴታቸው ይቀንሳል። ከጠላፊው ይልቅ በልጃቸው ይናደዳሉ። ልጃቸው ወዳ ሄዳች የሚለው ክብራቸውን የሚያቀርድ እንደሆን አድርገው ይገምታሉ። ወግ ማዕረጉም ከሌሎች የጋብቻ አይነቶች ያነሰ ነው። ይህም ያናድዳቸዋል።

በብሔረሰቡ ባህል አንድ ልጃገረድ ከጓደኛዋ ጋር ተግባብታ በግሽ የምትሄድ መሆናን የምታስታውቅበት መንገድ አለ። እንጨት እየለቀመች በቤቱ ጥግ ዙሪያ ትከምራለች። የወላጆቿን ቤት ታሳምራለች ውስጡንና ውጩን ትመርጋለች። ትለስናለች በአመድ፣ በከብት እበትና ከወንዝ ዳር ነጭ ኖራ እያመጣች ታስጌጠዋለች። ግድግዳውን የተዋበ ታደርገዋለች። የተለያዩ ስዕሎች ትስልበታለች። ልጅቱ ከወትሮው በተለየ ሁኔታ ከቤት ውስጥ ሥራ ይልቅ የውጭ ሥራ ታዘወትራለች። ቡና መልቀም፣ ባካ መኮትኮት፣ ውኃ በተደጋጋሚ መቅዳት፣ ከብት መጠበቅ፣ እንጨት መልቀም ... ታዘወትራለች። እነዚህ ሥራዎች ከልጁ ጋር ለመገናኘት ምቹ ናቸው። እነዚህ አዳዲስ የሚታዩ ባህሪዎቿ ለቤተሰቦቿ የሚጠቁሙት ነገር አለ። በመጨረሻም እንድትጠለፍ ካመቻቸች በኋላ እንጨት ለቀማ ሄድኩ ብላ ነው በዚያው

የምትቀረው። ይህን ድርጊት የልጅቷ ቤተሰቦች ስለሚረዱ በእርቅ ሥርዓት ወቅት ብዙም አያስቸግሩም በተጠለፈችበት ወቅትም ለግድያና ለጥል አይነሳሱም።

እርቅ እንዲፈፀም የተመረጡት ሽማግሌዎችም የካሳ ከብቶችን ከሰጡ በኋላ የእርቅ ስነ-ስርዓት የሚፈፀምበትን ቀን ቀጠሮ ጠብቀው የተዘጋጁትን የጥሎሽ ከብቶችና ጠላፊውን ልጅ በመያዝ ወደ ልጅቷ ቤተሰቦች ቤት ይሄዳሉ። ባህላዊ ደንቡ በሚያዘው መሠረት የሚደረገው ሁሉ ይከናወናል እርቅ ይወርዳል። ልጁና የልጅቱ ቤተሰብ በሽማግሌዎች አደራዳሪነት ከታረቁ በኋላ ምርቃት ይካሄዳል። ልጁና ልጅቱም ቤታቸውን ሰርተው ሰላማዊ በሆነ መንገድ ይኖራሉ። ልጅ ከልጅቷ ቤተሰብ ጋር ተቀራርቦ በመከራና በደስታ ጊዜ አብሮ ይሳተፋል። ልጁና ልጅቱም ቤተሰቦቻቸውን በሥራ ይረዳሉ።

### 4.2.4 የባልና ሚስት ግጭት አፈታት

ባልና ሚስት የጋራ ህይወታቸውን አጣምረው ሲመሩ በኑሮ ሂደት አልፎ አልፎ ችግር መፍጠሩ አይቀሬ ነው። በመካከላቸው ለሚፈጠረው አለመግባባት ምክንያት የሚሆነው የወንዱ ወይም የሴቷ ሊሆን ይችላል።

ባልና ሚስት ኑሮአቸውን ለማሸነፍና የተሳካ ለማድረግ የበኩላቸውን ጥረት ያደርጋሉ። በዚህ የኑሮ ውጣ ውረድ እንቅስቃሴ የጋራ ጥረታቸው ተሳክቶ የተቃናና ሰላማዊ ህይወት እንዳይኖሩ የሚያደናቅፉ መሰናክሎች ይፈጥራሉ። እነዚህም ከባልና ሚስት ከራሳቸው የሚፈጠሩና ሌላ አካል በእነሱ መካከል ጣልቃ ሲገባ በሚያጋጥሙአቸው ውስጣዊና ውጫዊ ችግሮች የተነሳ ሰላማዊ ኑሮአቸው ቀስ በቀስ ተናግቶ መለያየት የሚከሰትበት አጋጣሚ አለ። ሀብታሙ ወንድ (1998፡19) ለባልና ሚስት ግጭት ዋና መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉትን እንደሚከተለው ገልፀዋል "Sexual incompatibility and financial Problems are the main causes for conflicts between husbands and wives."

ግጭቱ እንዲፈጠር የባልየው ወይም የሚስቲቱ ሊሆን ቢችልም በሸኮ ብሔረሰብ ዘንድ በባልና ሚስት መካከል ለሚፈጠሩ ትራኔዎች ዋና ዋና ናቸው ተብለው የሚታወቁት ቀጥሎ የተመለከቱት ናቸው።

ሀ. ሚስት ወይም ባል በስውር ከሌላ ሰው ጋር ዝሙት/ዚቲ/ የሚፈፅሙ ከሆነ በመካከላቸው ያለው ፍቅር እየቀነሰ ይመጣል። ዝሙት የፈፀመው አካል በአካባቢው ነዋሪዎች ተደርሶበት ወሬው ሲናፈስ ከአንደኛው ጆሮ ሲደርስ ከሚመጣ ቅናት፣ ዘለፋ፣ ጥልና ከሚፈጠር ሁከት

ለ. ሴትየዋ በተለያዩ ምክንያቶች ልጅ መውለድ ካልቻለች

ሐ. ሚስት በባሏ ዘመዶች ጭቅጭቅ፣ ሐሜት፣ እንዲሁም መገለል ሲደርስባት ባሏ ከዘመዶቹ ጋር አብሮ እሷን የሚያገል/የሚጠላ/ መስሎ ስለሚታያት ከሚፈጠር ጥርጣሬ የሚመነጭ አለመግባባት

መ. ሴትዬዋ በባህላዊ ህግና ሥርዓቱ መሠረት ማከናወን ያለባትን ሥራ ሳትሰራ መንደር ለመንደር እየዞረች ወሬ የምታናፍስ ሰውና ሰውን የምታጣላ መሆኗ ሲረጋገጥ

ሠ. ባልየው ሥራ ማይሠራ መጠጥ የሚያበዛና ስካራም ሆኖ በቤት ውስጥ ረብሻ እየፈጠረ ሲያስቸግር።

ረ. ባልና ሚስት ተመካክረውና ተግባብተው ለመኖር ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ቤተሰቡ ለችግር ሲጋለጥና በቤት ውስጥ የሚላስ የሚቀመስ ሲጠፋ ጥፋቱን ወደ አንደኛው የማላከክ ሁኔታ ሲፈጠር የሚከሰት

ሰ. ሚስትየዋ በቤት አያያዝ፣በንብረት አጠቃቀም በምግብ ዝግጅት ደካማ ከሆነች ለምሳሌ ጨሞ በአግባቡ የማታፈላ፣ ኪጃ በሥርዓት የማታዘጋጅ፣ ወተት፣ አይብና ቅቤ በንጽህና የማትጠቀም ከሆነ

ሸ. ሴትየዋ ጠጭ ሆና ከቤት ውጭ መንገድ ለመንገድ እየተወላገደች ስትሄድ የአካባቢ ነዋሪዎች መሳቂያና መሳለቂያ ማድረጋቸውን ባልየው ሲያረጋግጥና በእንስሳት አያያዝና በልጆች እንክብካቤ ላይ ድክመት ሲታይባት

ቀ. ባል ወይም ሚስት የጋራ ገንዘባቸውን ያለ አግባብ ሲያጠፉና ሲያባክኑ በኑሮአቸው ላይ መቃወስ ሲመጣ የሚፈጠር።

በእነዚህና በሌሎችም ምክንያቶች በባልና ሚስት መካከል ግጭት ይፈጠራል። በሸኮ ብሔረሰብ በባልና ሚስት ግጭት አፈታት እርቅ ጎረቤት የአካባቢ ሽማግሌዎች፣ የልጅቱና የልጁ አባትና እናት፣ በርጃብ፣ ባላባቶችና ቃልቾች እንደግጭቱ ክብደትና ቅለት ይታያል።

በሦስተኛ ወገን የሚከናወን እርቅ ግጭትን ለማስወገድ ጠቃሚ እንደሆነ ሀብታሙ ወንድሙ (1998፣19) እንደሚከተለው ይገልፃል፤ "Mediation and arbitration by athird party and accommodating the disagreements and conflicts are some of the main techniques of conflict resoulation in most families".

በባልና ሚስት መካከል አለመግባባት ሲፈጠር የማግባባት ሥራ የሚከናወነው በጎረቤቶቻቸው አማካይነት ነው። ጎረቤት ጉዳዩን ተከታትሎ እንዲግባቡ ያደርጋል። አለመግባባቱ እየተባባሰ

ከመጣና ከጎረቤት አቅም በላይ ከሆነ በልጅቱና በልጁ ቤተሰቦች አማካይነት ይታያል:: የሁለቱ ወላጆች በመገናኘት የግጭቱን ምንጭ ያጣራሉ:: ጥፋተኛውን የመለየት ሥራ ይሠራሉ:: ጥፋት የፈፀመው አካል ከመጥፎ ድርጊቱ እንዲቆጠብ መክረውና ተቆጥተው ግጭቱ እንዲረግብ ያደርጋሉ:: በዚህ ደረጃ የሚፈፀመው የመግባባት ሥራ ውጤታማ የሚሆንበት አጋጣሚ ቢኖርም አልፎ አልፎ የማይሳካበት ሁኔታ ይኖራል::

ባልና ሚስት ግጭት ውስጥ ገብተው በጎረቤቶቻቸውና በወላጆች አስታራቂነት የማይሳካ ከሆነ በሦስተኛ ደረጃ የሚታየው በአካባቢ ሽማግሌዎች ነው:: ሽማግሌዎቹ በአካባቢው ነዋሪዎች ዘንድ የተከበሩና ተሰሚነት ያላቸው ናቸው::ሽማግሌዎች በግጭት ውስጥ የገቡትን ባልና ሚስት እንዲግባቡ ያደርጋሉ::: በሽማግሌዎች የሚከናወነው የመግባባት ሥራ ሙሉ በሙሉ ውጤታማ የማይሆንበት ጊዜ አለ:: አንዳንድ ባልና ሚስቶች በሦስተኛ ወገን የሚሰጣቸውን ምክርና ተግሳፅ ባለመቀበልና የተጣለውን ገደብ በመጣስ ግጭት እንዲቀሰቀስ ምክንያት ይሆናሉ ወይም በሰሩት ጥፋት አለመፀፀት ያሳያሉ:: በዚህም ምክንያት የጎረቤት፤ የወላጆችና የሽማግሌዎች ድካም ከንቱ ያሆናል::

ባልና ሚስት የተጋጩበት ጉዳይ ከባድ ሆኖ በሽማግሌ ጥረት ማግባባት ካልተቻለ ጉዳዩ ትኩረት ተሰጥቶት የመግባባት ሁኔታ እንዲፈጠር ቡርጃብ በእርቅ ስነ-ስርዓት እንዲሳተፍ ይደረጋል:: ሽማግሌዎችና ቡርጃብ በጋራ ሆነው የተከሰተውን ግጭት ይመረምራሉ:: ጉዳዩን ከመረመሩና ካጣሩ በኋላ ስህተት የፈፀመው አካል ተመክሮ ከመጥፎ ድርጊቱ እንዲመለስ ይነገረዋል:: ዳግሞ ጠብ ላይጭር ቃል ይገባል:: እርቅ ተከናውኖ በሰላም እንዲኖሩ ይደረጋል:: በቡርጃብና በሽማግሌዎች አስታራቂነት መፍትሔ ካልተገኘ ባልና ሚስቶች በሰላም እንዲለያዩ ይሆናል::

በሸኮ ብሔረሰብ ባህልና እምነት መሠረት በባልና ሚስት መካከል በስውር ዝሙት ሲፈፀም ውቃቢ የተደበቀውን ምስጢር ያወጣል የሚል እምነት አለ:: የመረጃ አቀባዮች እንደገለፁልኝ አንድ የአባወራ ሚስት ቡና ልትለቅም፤ እንጨት ልትሰብር፤ ውኃ ልትቀዳ ወይም ከብት ስትጠብቅ ከሌላ ወንድ ጋር ዝሙት /ዚቲ/ ከፈፀመች ሴትዬዋ ይህ ድርጊት መፈፀሙን መናገር አለባት:: ምስጢሩን ደብቃ ዝም የምትል ከሆነ ውቃቢው የሚያሳየው ነገር አለ:: በብሔረሰቡ ባህል አንዱ ከሌላው ሚስት ጋር በስውር ዝሙት ሲፈፀም ይፋ ወጥቶ እርቅ መውረድና ጥፋተኛው መቀጣት አለበት:: ያበለዚያ ዝሙት የፈፀሙት ሰዎች ይሞታሉ ተብሎ ይታሰባል::

በባልና ሚስት መካከል አለመግባባት ሲፈጠር በአካባቢው ወደሚገኘው ቃልቻ ቤት በመሄድ የችግሩን ምንጭ ማወቅ ያስችላል የሚለው በብሔረሰቡ አባላት የሚታመንበት ነው:: ቃልቻ በስውር የሚከናወኑ ነገሮችን ማየት እንደሚችልና ውቃቢው እንደሚነግረው በማህበረሰቡ ዘንድ

ይታመናል። ስለዚህ ወንዱ ከሚስቱ ጋር አለመግባባቱን ምክንያት በማድረግ ወደ ፍቹቃ/ቃልቻ/ ቤት ሄዶ ይጠይቃል።

በቤሔረሰቡ ባህል ቃልቻ ዘንድ ሄዶ የሚጠይቅ ሰው የተፈፀመው ነገር ሁሉ ይነግረዋል። ጉዳዩ አሳሳቢና ባህላዊ ህጉን የሚጋፋ ከሆነ ቃልቻው ወደ አካባቢው የጎሣ መሪ ያስተላልፋል። ዬጎሣ መሪውም ጉዳዩን በህዝብ ፊት በእርግማንና በውግዘት እንዲጋለጥ ያደርጋል። በብሔረሰቡ ባህል ቃልቻ ቤት ሄዶ እውነቱ የተነገረው ሰው በጠንቋዩ ጠቋሚነት ጥፋት በሰሩ አካላት ላይ አደጋ ማድረስ የተከለከለ ነው። በብሔረሰቡ ህግን የሚተላለፍና በስውር ወንጀል ለሚሠሩ ሰዎች የሚቀጡበት ማህበራዊ ህግ አለ።

በቤሔረሰቡ ባህል የዝሙት ሥራ በስውር ተፈፅሞ ይፋ ሲወጣ የሴቷ ቤተሰቦች ወደ የጎሣ መሪው ቤት በመሄድ ዝሙት የሠራውን ወንድ በመጠቁም ያሳውቃሉ። ምክንያቱም ከባሏ ጋር እርቅ መፈፀም አለበት። ነገሩ ይፋ ወጥቶ እርቅ ካልተከናወነ ባህላዊ ህጉን በመጣስ በስውር ዝሙት የፈፀሙ ሰዎችን የኩይናብ የቃልቾችና የጎሣ መሪዎች አምላክ ተቆጥቶ ያጠፋቸዋል ተብሎ ስለሚታሰብ የልጅቷ ወላጆች ወደ ባላባት ዘንድ ሄደው ማሳወቅና በባላባቱ ፊት እርቅ መፈፀም አለበት።

በቤሔረሰቡ ባህል የሰው ሚስት የደፈረው ሰው አንድ ወይፈንና አንድ ጊደር ካሣ ይሰጣል። ስለዚህ የሰው ሚስት የደፈረው ሰው ወይፈንና ጊደር በማምጣት በባላባቱ ፊት ያስረክባል። ሚስቱ የተደፈረችበት ሰውየም ካሳውን ይቀበላል። ባላባቱ ሁለቱ ሰዎች ታርቀው በሰላም እንዲኖሩ ያደርጋል። በክፋ ላይተያዩ ቃል ገብተው በባላባቱ ምርቃት ተካሂዶ ተሰነባብተው ወደየቤታቸው ይሄዳሉ።

ባልና ሚስትም በዚያው በባላባቱ ፊት ቀርበው እንዲታረቁና በሰላም እንዲኖሩ ምክር ይሰጣል። ሚስትየዋም ከዚህ በኋላ የዚህ አይነት ጥፋት እንዳትፈፅም ማስጠንቀቂያ ይሰጣታል። እሷም ጥፋቷን አምና ይቅርታ ትጠይቃለች። ከዚህ በኋላ በሰላም መኖር ይጀምራሉ። በሸኮ ባህል በዝሙት ምክንያት ከቤቷ ወጥታ እርቅ ተፈፅሞ ሴቷ ወደ መጀመሪያ ባሏ ቤት ስትመለስ ስኩማበየማ/ በክብር መመለስ ይባላል።

ባልና ሚስት በስውር በተፈፀመው ዝሙት ምክንያት ውቃቢው ከልክሎ የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዳይፈፅም ስውዩውን/ባልየውን/ አግዷል። ባህላዊ ህጉ በሚፈቅደው መሠረት እርቅ ተፈፅሟል። ባልና ሚስት የተቋረጠውን ግንኙነት እንዲፈፅሙ በባላባቱ ፊት የሚከናወን ሥርዓት አለ። ይህም ጨዋ ከተፈላ በኋላ ከቅል በተሠራ ስፊ አፍ ያለው መጠጫ ውስጥ ያፈሔመራል ባልና ሚስት በአንድ ላይ ሆነው እንዲጠጡ ይደረጋል። ባላባቱም የአባቶቻችን

አምላክ ሆይ፣ክይናብ ንጉሳችን ሆይ፣ አድባራትና አገር ሆይ ባህላዊ ህጉ የሚፈቅደው ሁሉ የተከናወነ ስለሆነ ይቅር በላቸው ብሎ ይማፀናል:: ከዚህ ስነ-ሥርዓት በኋላ ባልና ሚስት እንዳይገናኙ የከለከለው ውቃቢ ይለቃል:: ባልና ሚስት ተግባብተው ሰላማዊ ኑሮአቸውን ይጀምራሉ:: ከዚህ የእርቅ ስነ-ስርዓት በኋላ በባልና ሚስት መካከል ጥሩ ግንኙነት ይኖራል::

በስውር የሚከናወን ድርጊት በቃልቻ አማካይነት ይጋለጣል ይህም ሰዎች ተደብቀው ወንጀል እንዳይሠሩ ይከለክላል:: ባህላዊ ህጉ የተከበረና አይነኬ ሆኖ እንዲቀጥል ያግዛል:: በድብቅ ዘሙት የሠራው በባላባት ፊት መቀጣቱ ለሌሎችም ትምህርት ይሆናል:: ቃልቻውም ይህን የተደበቀ ምስጢር በማውጣቱ በስውር ወንጀል የሚፈፅሙ አካላት መጋለጣቸው የማይቀር መሆኑን ስለሚረዱ ጥሩ የማስተማሪያ ስልት ነው::

በባልና ሚስት መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶች ተባብሰው አደጋ እንዳያስከትሉ በጎረቤት፣ በወላጆች፣ በአገር ሽማግሌዎች፣ በቡርጃብ፣ በቃልቾችና ባላባቶች እርቅ እንዲከናወን ይደረጋል:: እስከ መጨረሻው ተሞክሮ መግባባት ከሌለ በሰላማዊ መንገድ እዲለያዩ ይደርጋሉ:: ይህም ግጭቱ እንደተወገደ ተደርጎ ይቆጠራል::

### 4.2.5 በስርቆት የሚፈጠር ግጭት

በሸኮ ብሄረሰብ ከሚፈጠሩ የተለያዩ ግጭቶች መካከል በስርቆት ሰበብ የሚከሰተው አንዱ ነው:: የስርቆት ወንጀል የሚፈፀመው በገንዘብ፣ በከብት፣ በእህል በቤት ቁሳቁስ፣ እንዲሁም በውጭ አካባቢ ባሉ አትክልት፣ አዝርዕት፣ ፍራፍሬዎች ቡናና በሌሎችም ላይ ነው:: ደፋ ቀና ብሎ ያፈራውን ሀብት የሚሰረቅ ግለሰብ ወይም ቡድን ከሚሰርቀው አካል ጋር ግጭት ይፈጥራል:: ንብረቱን የተሰረቀው አካል ሰራቂውን ነጠቀው ንብረቱን እንዲመልስለት ይጠይቃል:: ሌባው የሰረቀውን ለመመለስ ፈቃደኛ ካልሆነ በሁለቱ መካከል ግጭት ይፈጠራል:: ግጭቱ ከድብድብ እስከ መገዳደል ይደርሳል:: ሌባው ካልታወቀና በስውር የፈፀመው ከሆነ ደግሞ ባህላዊ ህግና ሥርዓቱ በሚያዘው መሠረት እንዲከናወን የተሰረቀው ክፍል ለቃልቻና ለጎሣ መሪ ይናገራል::

በሸኮ ብሔረሰብ ስርቆት በጣም ነውርና የሚወገዝ ነው:: የሚሰርቅ ሰው ከዚህ እኩይ ተግባር እንድመለስ ይመከራል:: አሻፈረኝ ብሎ መስረቁን የሚገፋበት ከሆነ ከጋብቻና ከሌሎችም በጎሣ መሪዎች፣ በቃልቾች፣ ማህበራዊ ግንኙነቶች እንዲገለል ይደረጋል:: በቡርጃብ፣በባቡ/ሽማግሌች/ አማካይነት ቦራ/እርግማን/ ስለሚደረግ ሌባው ከነዘርማንዘሩ ይጠፋል ተብሎ ስለሚታመን በስርቆት የሚሰማሩ ሰዎች በጣም ጥቂት ናቸው:: እነዚህም ቢሆኑ የቦርቱሳን ስነ-ስርዓት ስለሚያከብሩ በግጭቱ ውስጥ እንደገቡ አይቀሩም::

የስርቆት ወንጀል አፈፃፀሙ በሦስት መልክ የሚታይ ነው:: የመጀመሪያወ ሰው በተኛበት ሰዓት ጨለማን ተገን በማድረግ ወይም አካባቢው ጭር ባለበት ሰዓት በቀን ጫካን ከለላ አድርጎ የሚከናወን ስርቆት ነው:: ሁለተኛው በማን አለብኝነት በገሃድ የሚፈፀም ዘረፋ ነው:: ሦስተኛው በልጆች አማካይነት የሚፈፀም ነው::

በስውር ንብረቱን/ የተሰረቀ ሰው በቀጥታ ወደ ቃልቻ ዘንድ ይሄዳል:: ወደ ቃልቻ ቤት ሲሄድ የተሰረቀበት በሬ ከሆነ የበሬውን ማሰሪያ ገመድ በመያዝ ነው:: በቃልቻ ዘንድ እንደደረሰም ው ቃቢ አደባይ ሆይ፤ የአገር አምላክ ሆይ፣ ንጉሳችን ኮይናብ ሆይ፣ የአድባራትና የአባታችን መንፈስ ሆይ ይኸውላችሁ ተዘርፌ ቀረሁ ብሎ ይናገራል:: ወደ ቃልቻ ቤት ሲሄድ ከአካባቢው ነዋሪዎች ሦስት ሰዎች አብረው ይሄዳሉ:: እነሱም ለመረጃነት እዲያገለግሉ ነው::

ከስ የቀረበለት ቃልቻ ንብረቱ የጠፋበትንና አብረውት የመጡትን ሰዎች ያነጋግራል:: የሰረቀውን ሰው እገሌ ብሎ ባይጠራም ሰዎችና ባለንብረቱ እንድጠረጥሩ በሚያስረዳ መልኩ አንዳንድ ምልክቶችን በመጠቆም ፍንጭ ይሰጣል:: ከቃልቻ የተሰወረ ነገር ሊኖር እንደማይችል ቢታወቅም በቀጥታ ሌባው እከሌ ነው ብሎ አይናገርም:: ባህላዊ ህጉ አይፈቅድም:: የጠንቋዩ በቀትና ኃይል የሚገለፀው በሰረቀው ሰው ላይ ምልክት በማሳየት ነው:: ቃልቻ የተሰያዩ ጥቆማዎችና ጠቋሚ ምልክቶችን ከሰጠ በኋላ ወደ አካባቢው የጎሣ መሪ ሄደው በዚያ በኩል ችግሩ እንዲቃለል ያሻል::

ከቃልቻው መልዕክት የደረሰው የጎሣ መሪ ስርቆቱ የተፈፀመበት አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች በሙሉ እንዲሰባሰቡ ትዕዛዝ ይሰጣል:: በጎሣ መሪ የስብሰባ ጥሪ የሚቀር የለም:: በስርቆት ምክንያት የሚጠራ ስብሰባ የተከበረና የማህበረሰቡ አባላት በፈቃደኝነትና በጉጉት የሚሳተፍበት ነው:: በስብሰባው የማይገኝ አንድም እንደሰረቀ ይቆጠራል:: በሌላ መልኩ የባላባቱን ክብርና ባህላዊ ደንቡን እንደጣሰ ተደርጎ ስለሚቆጠር እርግማኑን ይፈራል:: ቡርጃቦች የአካባቢ ታዋቂ ሽማግሌዎች የስብሰባው ተሳታፊዎች ብቻ ሣይሆኑ ዋና አስተባባሪዎች ናቸው::

የተጠራው ህዝብ ተሟልቶ ሲሰበሰብ የጎሣ መሪው ከህዝብ ፊት ለፊት በተዘጋጀው መቀመጫ በቡርጃቦችና በታዋቂ የሀገር ሽማግሌዎች መሃል ይቀመጣል:: ህዝቡም ትኩረቱን ወደ ጎሣ መሪው አድርጎ በተመስጦ ይከታተላል:: የጎሣ መሪውም ቁጣና ንዴት በተቀላቀለበት አነጋገር የአያት ቅድመ አያቶችንን ህግ የጣስ፣ ባላባቶችን ቡርጃብንና ቃልቾችን የናቀ፣ አድባራትን ያንቋሸሸ፣ ዉይናብ አልዳኘም/አልገዛም/ ያለ፣ በሀገራችንና በህዝባችን ላይ መከራ ሊያመጣ የተነሳ ሰው አጋጥሞናል:: ባህላችንን የሚያስንቅ ድርጊት ተፈፅሟል:: እኛም ከዛሬ ነገር አጥፊው ተፀፅቶ ይመለሳል በማለት ስንጠባበቅ ነበር ግን የጠፋው ንብረት አልተመለሰም::

ስለሆነም ይህን ባህላዊ ህግ የጣሰ ሰው በጋራ ሆነን የኮይናብ አምላክ አጋልጦ እንዲሰጠው በራ/እርግማን/ እንፈፅም። ይህ ክፉ ሰው «የወለደው እንዳይባረክ! የዘራው እንዳይበቅል! ጤናው እንዲታወክ! ዘርማንዘሩ የተረገመ እንዲሆን! በፈጣሪ ዘንድ የተጠላ እንዲሆን! መርገም» አለብን። ምክንያቱም የሽማግሌ ቃል ጥሷል፣ የአባቱን ወግ አፍርሷል ሞትን መርጧል፣ አያት ቅድመ አያቱ የሚያመልኩበትን ክዷል፣ የጌታውን ትዕዛዝ አልቀበልም ብሏል በማለት የተደጋገመ ግን በተሰበሰበው ህዝብ ዘንድ ተደማጭ የሆነ ባህላዊ እምነታቸውን የሚያንፀባርቅ አስተያየት ያቀርባል። ከተሰበሰበው ህዝብ መካከል አንዳዶቹ እየተነሱ እርግማን መከናወን እንዳለበት አስተያየት ይሰጣሉ። ሌሎችም ድጋፋቸውን በጭብጨባ ያረጋግጣሉ።

በተጠራው ስብሰባ ሌባውና ዘመዶቹ ተሳታፊ ናቸው። ስለዚህ በስብሰባው ላይ የቀረበውን አስተያየት ሲሰሙ መጨነቅ መጠበብ ይጀምራሉ። የሌባው ዘመዶች ተቀራርበው የሚኖሩ በመሆኑ ዘመዳቸው ሊሰርቅ እንደሚችል ጥርጣሬ ይኖራቸዋል። በስብሰባው የሚሳተፉ የአገር ሽማግሌዎች የቦራ/እርግማን/ ሥነ-ሥርዓቱ ለሌላ ጊዜ እንዲሆን ሀሳብ ያቀርባሉ። ይህም በባህሉ የተረገመ ሰው መጥፋቱ ስለማይቀር ሌባው ተፀፅቶ ራሱን ሊያጋልጥ ይችላል በሚል ነው። የጎሣ መሪውም የሽማግሌዎችን ሀሳብ ይቀበላል። የቀጠሮው ቀን ተወስኖ ስብሰባ ይበተናል። እንዲህ የሚደረገው በውስጠ ታዋቂ ጊዜ ለመስጠት ነው።

ህዝቡ በተጠራበት ስብሰባ ቦራ እንዲከናወን ተወስኗል። በቦራ ስነ-ስርዓቱ የጎሣ መሪዎች፣ በረዳቶችና ታዋቂ ያገር ሽማግሌች ይሳተፋሉ። ቦራ የሚከናወን መሆኑ ቁርጥ ሆኗል። ይህን የሚያገኘው ሌባ መጨነቅ መረበሽ ይታይበታል። ከወትሮው በተለየ ሁኔታ ከሰው መራቅ ይጀምራል። ትስሙ ይሰበራል ምክንያቱም ቃልቾች ወደ ባላባት አስተላልፈዋል የሚለውን ወሬ መስማቱ አይቀርም። ቃልቾችና የጎሣ መሪዎች ለእግዚአብሔር ቅርብ ናቸው። ስለዚህ የእነሱ እርግማን ተሰሚነት ያገኛል የሚል አስተሳሰብ አለው። ስለዚህ በጣም ይረበሻል።

የሌባው ዘመዶች በስብሰባ ከተሳተፉበት ጊዜ ጀምሮ ሁኔታዎችን ይከታተላሉ። ከውጭ የሚሰነዘሩ ሀሜቶችን ይሰማሉ። ንብረት ተሰርቆበት ወደ ቃልቻ ቤት የሄደው ሰው ጋር ለምስክርነት ከሄዱት ሰዎች የሚነገሩ ጥቆማዎችን ያደምጣሉ። የሰረቀው ሰው የሚያሳየውን መደናገጥ ከአካባቢው ነዋሪዎች ሀሜት ጋር በማጣጣም የሰረቀው እሱ መሆኑን አረጋግጠው በእርግማን እንዳይጠፋ ለማዳን ጥረት ያደርጋሉ። ቤተሰብ በጋራ እየተሰበሰቡ ይመካከራሉ። ጥርጣሬያቸው እየጎላ ከመጣ በአካባቢው ወደሚገኘው ቃልቻ ይሄዳሉ ቃልቻውም ሰውየው የተመመው ያጠፋውን ጥፋት ስለደበቀ ነው በማለት በድፍኑ ይነግራቸዋል። ከዚህ በኋላ ዘመድ ተሰብስቦ እንዲያምን ይመክረዋል። ከመሞት ማመን እንደሚሻል ደጋግመው ይመክሩታል። የሰረቀውን ንብረት ያጠፋው ከሆነና የሚከፍለው ንብረት ከሌለው እንደሚረዱት ያረጋግጡለታል። ሌባውም የሰራውን ያምናል።

በተያዘው ቀጠሮ መሠረት ህዝቡ ይሠበሰባል፡፡ የጎሣ መሪዎች ቡርጃቦችና ተዋቂ ሽማግሌዎች ከህብረተሰቡ ፊት ለፊት ይቀመጣሉ፡፡ ለቦራ/እርግማን/ ዝግጅት ይደርጋል፡፡ ከእርግማን በተጨማሪ የሚዘጋጅ መሃላ አለ ይህም በብሔረሰቡ ዘንድ የሚታወቅና ክህደት ሲፈፀም የሚከናወን ነው፡፡ ለመሃላው እንቁላል፣ አመድ፣ድንጋይ፣ጭራ፣ዛማ ጠገራ ይቀርባል፡፡ እነዚህ በአንድ ላይ ሆነው ይቀመጣሉ፡፡ የሰው ገንዘብ አልወሰድኩም ሥርቆት አልፈፀምኩም ያለ እነዚህን በአንድ የተቀመጡ ነገሮች እንዲራመድ ይደርጋል፡፡ በብሔረሰቡ ትልቅ መሃላ ነው፡፡ እርግማኑንና መሃላውን ለመፈፀም የጎሣ መሪው ቡርጃብና ያገር ሽማግሌች በዝግጅት ላይ እንዳሉ የሌባ ዘመዶች የሰረቀውን ሰው በመያዝ ወደ የጎሣ መሪው ፊት ያቀርቡታል፡፡

ሌባው በማር ድምፅ «አገርን አድባራትን፣ ውቃቢን ኮይናብን እየጠራ ማሩኝ አጥፍቻለሁ፡፡ የሰረቅሁት እኔ ነን» ብሎ ይማፀናል፡፡ የተሰበሰው ህዝብ በማጨብጨብ እና እልል በማለት የደስታ ድምፅ ያሰማሉ፡፡ ምክንያቱም አምላክ ሌባውን ስላጋለጠ ባህላዊ ሥርዓታቸውን የሚጥስ እንደሚዋረድ በማረጋገጣቸው ነው፡፡ የጎሣ መሪው ወደ ህዝቡ በመመልከት ፈገግታ ያሳያል፡፡ የአካባቢውን ፀጥታ የሚያናጉ፣ የሚሰርቁ፣ የሚክዱና ባህላዊ ህጉን የማያከብሩ ከጎሣ መሪዎችና ከህዝቡ አያመልጡም፡፡ በስውር ደባ ቢሰሩም ይጋለጣሉ፡፡ አምላካችን ከእኛ ጋር ነው በማለት ይናገራል፡፡

ህዝቡ በተሰበሰበበት ሌባው ራሱን አጋልጧል፡፡በስራው ተፀፅቶ ማሩኝ ብሏል፡፡ ስለዚህ ቦራ/እርግማንና/ መሃላ አይፈፅምም፡፡ ነገር ግን ባህላዊ ህጉን ባለማክበር ከጎሣ መሪው እስከተራው ህዝብ በስብሰባ እንዲንገላቱ አድርጓል፡፡ የጎሣ መሪው በስህተትህ ከተፀፀትክ የአባቶችህን ህግ ስለጣስክ፣ አድባራትን ስላንቋሸሽክና ንጉሣችንን ስለተዳፈርክ ካሳቸው ደም አፍስሰህ ስርዮት አደርግ ይለዋል፡፡ ይህን ካደረግህ አንተም ልጅህም በሰላም ትኖራላችሁ ብሎ ይነግረዋል፡፡ የዚህ አይነት ክደት ለሚፈፅም ሰው ባህላዊ ህጉ አንድ ላምና በግ እንዲቀጣ ያዛል፡፡ ስለዚህ በግና ላሚቱ ቀርበው ይታረዳሉ፡፡ በመጨረሻ ከአገሩ ባላባት፣ከህዝቡና ንብረቱን ከሰረቀበት ሰው ጋር ይታረቃል፡፡ የወሰደውንም ንብረት ይመልሳል፡፡

የተጣሉ ሁለቱ ሰዎችም ይታረቃሉ፡፡ ግጭት ይቆማል፡፡ ተባብረውና ተከባብረው በሰላም ይኖራሉ፡፡ ሽማግሌቹም አንተም ልጆችህም ዘመዶችህም በሰላም ትኖራላችሁ ብለው ይመርቃሉ፡፡

በብሔረሰቡ አንድ ሰው ንብረት የሚጠፋበት ወይም የሚሰረቅበት ከሆነ የጠፋን ሀብት የሰረቀውን ሰው ሊጠረጥር ይችላል፡፡ ለጥርጣሬው መነሻ የሚሆነው የተለያ ምክንያቶች ይኖራሉ፡፡ ተበዳዩ በንብረቱ መጥፋት የጠረጠረውን ሰው ወደ ጎሣ መሪ ኮይበሲንታ/ደጅ/ በመሄድ ክስ ያቀርባል፡፡ ተከሳሹም በባላባት ደጅ ይጠራል፡፡ በባላባቱ ከቀረበ በኋላ የሰረቀውን ነገር እንዲመልስ

ይጠየቃል። በአደባባይ መመለሱ የማያስፈራው ከሆነ ለባለንብረቱ ሊታይ በሚችልበት ቦታ እንዲያስቀምጥ ይነገረዋል። ጊዜም ይሰጠዋል። ተጠርጣሪውም የባለንብረቱ ጥርጣሬና የጎሣ መሪው እርግጠኛ ሆኖ መልስ ማለት ያስደነግጠዋል። አልታወቀብኝም ብሎ ቢክድ በአካባቢው የዚህ ዓይነት ክህደት ፈፅመው የተጋለጡ ሰዎችን አይቷል።

ስለዚህ በጎሣ መሪ፣በቡርጃብ፣ በአገር ሽማግሌና በቃልቾች ቦሬ ተከናውኖ ተጨማሪ ቅጣት ውስጥ ላለመግባትና በቦሬ የሚደርስበትን ስቃይ በመፍራት የታዘዘውን ይፈፅማል። የጎሣ መሪ በዳይና ተበዳይን አቀራርቦ ግጭቱ እንዲወገድ ያደርጋል። ታረቀው በሰላም እንዲኖሩ ያመክራል። እነሱም የጎሣ መሪውን ቃል በማክበር እንደዱሮአቸው ተግባብተው ይኖራሉ።

በሸኮ ቤተሰብ ልጅን በስነ-ምግባር እንዲታነፅ፣ ቅንና ታታሪ እንዲሆን፣ የአባትና የእናቱን ወግና ባህል የሚያከብርና ከእኩይ ተግባር የራቀ ሆኖ እንዲያድግ ማድረግ ከወላጆ የሚጠበቅ ግዴታ ነው። በስርቆትና በክህደት በብልግና፣ በዋልጌነትና በአጉል ሱስ የሚሰማሩ ልጆች የተጠሉና የሚወገዙ ናቸው። ቤተሰቦቻቸውም በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ክበሬታ የላቸውም።

በብሄረሰቡ ወግና ባህል መሠረት አንድ ልጅ የሰውን ንብረት ከሰረቀ አባቱ እንዲከፍል ያደረጋል። አባቱ ቆንጥጦ ባለማሳደጉ ጥፋተኛ ነው። ስለዚህ መቀጣት አለበት የሚል ነው። በመሆኑም ስርቆት የፈፀመ ልጅ የወሰደውን/የሰረቀውን/ መመለስ ካልቻለ ተጠያቂው አባቱና እናቱ ናቸው። አባትና እናቱ አልከፍልም የሚሉ ከሆነ በባላዊ ህጉ መሠረት እርግማን ስለሚደረግና ከማህበራዊ ግንኙነት የሚያስገልል ስለሆነ መክፈላቸው የማይቀር ነው። ወላጆችም የሚመጣባቸውን ቅጣት ስለሚያውቁ ልጆቻቸውን ይቆጣጠራሉ። ከቁጥጥራቸው ውጭ ሆኖ የሚሰርቅ ልጅ ካለ የጠፋውን ንብረት ከፍሎ ግጭት የሚወገድበትን መንገድ ማከናወን የተለመደ ነው። ግጭቱም በአካባቢ ሽማግሌዎች ጠንክር ካለም በቡርጃብ በጣም የጠነከረ ሲሆን በጎሣ መሪዎች አስፈፃሚነት እርቅ ይከናወናል። የተጋጩት ሰዎች በሰላም እንዲኖሩ ይደረጋል።

# 5. የበርቱሳ ባህላዊ የግጭት አፈታት ፋይዳዎች

በየኪ ወረዳ ውስጥ በሸኮ ብሄረሰብ በባህላዊ መንገድ የሚከናወነው በርቱሜ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ማህበረሰቡን በተለያየ መንገድ ይጠቅማል:: በወረዳው የሚኖረው የሸኮ ብሔረሰብ የሚከሰቱ ግጭቶችን ለማስወገድ የሚጠቀመው ራሱ በፈጠረውና ጠብቆ ባቆየው ባህላዊ የዳኝነት ሥርዓት ነው::

ብሔረሰቡ በበርቱሜ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት የሚያገኘውን ፍትህ አምኖ ተቀብሎ በሰላም ይኖራል:: በማህበራዊ ኑሮው ሂደት ውስጥም ባህላዊ ተቋሙ ሳይበረዝና ሳይከለስ በቀጣይነት እንዲያገለግል የማህበሩን ደንብ ማክበር፣ የተፈቀደውንና የተከለከለውን በመለየት የፈጥሚነት ተግባሩን በመወጣት የተቋሙን ህልውና ያረጋግጣል:: ባህላዊ ተቋሙ በማህበረሰቡ መካከል የሚከሰቱ ግጭቶችን በማስወገድ በባህሉ ባለቤቶች ህልውና አግኝቶ በቀጣይነት እንዲተገበር ሁኔታዎችን ያመቻቻል::

የሸኮ ብሄረሰብ በማህበራዊ ግንኙነቶች ሰበብ በተለያዩ አነሳሽ ምክንያቶች የሚቀሰቀሱ ግጭቶችን በባህላዊ መንገድ ያረግባል:: ሙሉ በሙሉ እንዲወገዱም ያደርጋል:: ብሄረሰቡ በባህላዊ መንገድ ግጭቶች እንዲፈቱ የሚመርጥበት ምክንያት

1. በባህላዊ መንገድ የሚከናወነው የግጭት አፈታት ሥርዓት ትኩረቱ በማግባባት ላይ በመሆኑ ግጭቶች በእርቅ እልባት ስለሚያገኙ፣
2. ባህላዊ በሆነ መንገድ የሚፈፀሙ እርቆች በመሃላ፣ በእርግማንና በማህበራዊ መገለል ስለሆነ እርቁ ፀዳቂና የማይፈርስ እንዲሆን ማገዙ፣
3. የህዝቡን ወግ ባህልና እምነት መሠረት አድርገው የሚፈፀሙ የግጭት አፈታት ዘዴዎች በግልፅ ውይይት፣ በጋራ መግባባት የሁለቱንም ወገን ሀሳብ ፊት ለፊት በመቀበል በገሃድ ስለሚከናወኑና ማህበረሰቡ በሚያከብራቸው የእርቅ አስፈፃሚ አካላት ስለሚዳኝ ከአድሎ የፀዳ፣ ሙስና የሌለበት ነው ተብሎ ስለሚታሰብ
4. በብሔረሰቡ ውስጥ የሚፈፀሙ ስውር ወንጀሎች ማህበረሰቡ በሚያምንበትና ተቀባይነት ባለው ቃልቻ፣ ቡርጃብና የጎሣ መሪዎችን ፍራቻ ተሰውረው እንዳይቀሩ የማድረግ ብቃት ስላላቸው፣
5. የብሔረሰቡ አባላት የራሳቸው የሆነና አምነው የተቀበሉት የግጭት መፍቻ ተቋም ስላላቸው ፍትህ ፍለጋ ወደ ሩቅ ቦታ አይሄዱም:: ኃይማኖታዊና ባህላዊ ማዕረግ ባላቸው አካላትና በሽመዱትና በሚያውቁት ቦታ መዳኘት ጠቀሜታው የጎላ መሆኑ ስለሚታመንበት፣

ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች በባህላዊ መንገድ የሚፈፀመው የግጭት አፈታት ብሔረሰቡ ማህበራዊ ህይወቱን በተረጋጋ ሁኔታ እንዲመራ ያስችለዋል። በርቱማ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ከዘመናዊ የህግ ሥርዓት በላቀ ሁኔታ ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት። የብሄረሰቡ ኑሮ የተመሰረተው በግብርና ላይ ሲሆን ማህበራዊ ግንኙነቶችም ከዚሁ ጋር የተያያዙ ናቸው። በነዚህ ግንኙነቶች ምክንያት የተለያዩ ግጭቶች ይፈጠራሉ። በተፈጠሩት ግጭቶች ሰበብ ማህበራዊ ግንኙነት ይቋረጣል። የተቋረጡ ግንኙነቶችን እንደገና ለማደስ ደግሞ በርቱማ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

በርቱማ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ሁለት የተጋጩ አካላትን በማስታረቅ የሻከረው ግንኙነት እንዲታደስና መግባባት እንዲፈጠር ያግዛል። በብሄረሰቡ የከረረ ግጭት የሚባለው የነብስ ግድያ ነው። ስለዚህ በነብስ ግድያ ምክንያት የተፈጠረ ግጭት ጥፋት የፈፀመው ሰው እንዲቀጣ ይደረጋል። ከቅጣቱ በኋላ ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅሎ ማህበራዊ ተሳትፎ እንዲያደርግ የበርቱማው ሥርዓት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። ባህላዊ ተቋሙ ጥፋት የፈፀመው አካል ባህላዊ ህጉን መሠረት አድርጎ ቅጣት በመስጠት ማህበራዊ ግንኙነቱን አጠናክሮ በሰላም የመኖር ዋስትና እንዲያገኝ ያስችለዋል። በርቱማ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት በግጭት ውስጥ በገቡ አካላት መካከል እርቅ ወርዶ ዘላቂ ሰላምን ፈጥረው በአንድነት ተረዳድተውና ተግባብተው እንዲኖሩ በማድረግ ረገድ የጎላ ሚና አለው። ባህላዊ ተቋሙ የተባንቱ ማህበራዊ ግንኙነቶች ተቃንተው ማህበራዊ ህይወት እንዲጎለብት ያግዛል።

በርቱማ ባህላዊ የግጭት አፈታት በሽኮ ብሔረሰብ አሁንም በስፋት እየተሰራበት ነው። ስለሆነም ህዝቡ ፍትህ ፍለጋ ወደ ሩቅ አካባቢ አይሄድም። ግጭቶች ሳይባባሱ በአንጭጩ በመቀጨት በሚያው በሚኖሩበት አካባቢ መፍትሔ ይሰጣሉ። ግጭቶችን በባህላዊ መንገድ ስለሚፈቱ በተረጋጋና ነፃነት በሰፈነበት አኳኋን ኑሮአቸውን የተቃና ለማድረግና ለማሸነፍ ይችላሉ። ወደ ዘመናዊ የህግ ሥርዓት በመሄድ የገንዘብ፣ የጉልበትና የጊዜ ብክነት አያጋጥማቸውም።

በርቱማ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ዘላቂ ሰላምን ለማምጣት መቻሉ ከብሔረሰቡ ተጠቃሚነት ባለፈ የወረዳው አስተዳደርና የመንግሥት አካላትን ተጠቃሚ ያደርጋል። በብሔሰቡ አካባቢ ሰላምና ፀጥታን ለማስጠበቅ በሚደረገው እንቅስቃሴ ባህላዊ ተቋሙ የላቀ ድርሻ አለው። በበርቱማ የግጭት አፈታት ሥርዓት የሚፈፀመው ግጭትን የማስወገድ ሥራ የአስተዳደር አካላትን የሥራ ጫናዎች ይቀንሳል።

የበርቱማ ሥርዓት ሲከናወን በተቋሙ ውስጥ እምነቶች፣ መሃላዎች፣ እርግማኖች፣ ማህበራዊ መገለሎች፣ የእርቅ ማስፈፀሚያ ቁሳቁሶች፣ አምልኮታዊ ሥርዓቶች ... እርቅን ለማምጣት ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። በባህላዊ ተቋሙ የተለያዩ የግጭት አይነቶችን ለመፍታት በሚከናወንበት ጊዜ የተቋሙ ደንብና ሥርዓት እውቅና እያገኘ ይሄዳል። ይህም በማህበረሰቡ

ውስጥ ስርን የመግባትና ህያው ሆኖ እንዲቀጥል ያደርገዋል፡፡ ስለሆነም ባህሉ እየገነነና እየጠነከረ ይሄዳል፡፡

## 5.1 ማጠቃለያ

በሸኮ ብሔረሰብ መካከል በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰቱ ግጭቶች በአብዛኛው መፍትሔ የሚያገኙት በባህላዊ መንገድ በሚከናወነው የግጭት መፍቻ ተቋም ነው፡፡ ብሔረሰቡ በማህበራዊ ግንኙነቶች ላይ በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች በበርቱማ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት መዳኘትን እንደሚመርጥ ከጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ በእርቅ ሥርዓቱ የጎሣ መሪዎች፣ ቡርጃቦችና ተዋቂ የአገር ሽማግሌዎችን መርጦ በእነሱ አማካይነት በመዳኘት ስነ-ልቦናዊ እርካታ ያገኛል፡፡

በርቱ ባህላዊ የግጭት አፈታት በተሰኘው ተቋም ውስጥ እርቅ አስፈፃሚ የሚባሉት ቡርጃቦና የቡርጃብ ዘሮች የሆኑ ናቸው፡፡ ቡርጃብ የባህሉን ደንብና ስርዓት ጠንቅቆ የሚያውቅ ነው፡፡ ቡርጃብ የእርቅ አስፈፃሚ ቢሆንም የአካባቢው የጎሣ መሪ በበላይነት ይቆጣጠረዋል፡፡ ግጭቶች ሲከሰቱ ቡርጃብ የእርቅ ሥርዓት እንዲያስፈፅም ትዕዛዝ የሚሰጠው የአካባቢው የጎሣ መሪ እንደሆነ ከጥናቱ የተገኘው መረጃ ያስረዳል፡፡ በሸኮ ብሔረሰብ ለግጭት መቀስቀስ ምክንያት የሚሆኑት በዋናነት መሬት፣ ሴትና በጎሣና በጎሣ መካከል የሚፈጠሩና ከባህላዊ እሴቶች ጋር የተያያዙ እንደሆኑ በጥናቱ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በመሬት የሚከሰተው ግጭት ከድንበር መገፋፋትና ከግጦሽ ቦታ አጠቃቀም ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በሴት በኩል የሚፈጠረው ግጭት በጥለፋ ላይ፣ አንዱ የሌላውን ሚስት ሲያገባና በስውር ዝሙት የሚፈፅም ሲሆን፣ እንዲሁም ከጎሳነት ውጭ በሚፈፀም ጠለፋ ግጭቶች እንደሚፈጠሩ ተረድቻለሁ፡፡

የጥናቱ መረጃዎች በምልከታና በቃለ መጠይቅ አማካይነት ከመስክ የተሰበሰቡ ናቸው፡፡ በመስክ ሥራ ላይም በርቱማ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት አውዳዊ ክዋኔን በቅንብር ተፈጥሮአዊ መቸቶች ላይ በምስል ተቀርፀዋል፡፡ የባህላዊ ተቋሙን የአፈፃፀም ሥርዓት፣ አስፈላጊነት በበርቱማ ሥርዓት የሚሳተፉትን አካላት ለማወቅ ከአውራ መረጃ አቀባዮች በቴፕሪከርደር ድምጽ ተቀርጿል፡፡ መረጃዎችም በገላጭና በይዘት ትንተና የጥናት ዘዴዎች በጥናቱ ውስጥ ቀርበዋል፡፡

በበርቱማ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት የተለያዩ ግጭቶች ይፈታሉ፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ የነብስ ግድያ፣ የባልና ሚስት ጠብ፣ በጎሣና በጎሣ መካከል የሚፈጠር አለመግባባት፣ በጠለፋ ምክንያት የሚፈጠር ግጭትና በሀብት ስርቆት የሚከሰቱ ግጭቶችና የእርቅ ሥርዓታቸው ቀርቧል፡፡ በእርቅ ወቅት የሚተገበሩ ደንቦችና ስርዓቶች በወረዳው ውስጥ ተመሣሣይ በሆነ መንገድ እንደሚከናወኑ ተረድቻለሁ፡፡

በነፍስ ግድያ እርቅ ላይ ለካሣ የሚቀርበው ሰው ነው:: የሰው ካሣ መስጠት ካልተቻለ ከ 10-12 የሚደርሱ ከብቶች መካስ እንደሚቻል ለመረዳት ተችሏል:: በእርቅ ስነ-ስርዓት ቀርድ ዋና የእርቅ ማስፈፀሚያ ተክል ነው:: የተጣሉ ሰዎች በቡርጃብ አማካይነት ቀርደው በበጠጥና በአፈር እንብርትና እግሮቻቸው ላይ ይቀባል:: ከዚያ በኋላ ቂም በቀል አይኖርም ተብሎ እንደሚታመን ተረድቻለሁ በቀርድ የተፈፀመ እርቅ ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት የሚበሉትና የሚጠጡት ያስማማቸዋል:: ነገር ግን ግጭት ተፈጥሮ በቀርድ አማካይነት ሥነ-ሥርዓቱ ተካሂዶ እርቅ ካልወረደ የሚበሉት የሚጠጡት አይስማማቸውም ተብሎ ስለሚታመን እርቅ የሚፈፀመው በግጭት ውስጥ የገቡ አካላት የሚበሉትና የሚጠጡት እንዲስማማቸው እንደሆነ ታስቦ መሆኑን በጥናቱ ተመልክቷል::

በነፍስ ግድያ እርቅ ላይ የገዳይና የሟች ቤተሰቦች አብረው እንዲበሉና እንዲጠጡ በእርቅ ስነ-ስርዓት ወቅት በወንዝ ዳር በግ ታርዶ የበጉ ደም በጎርፍ እንዲወሰድ ሲደረግ የበጉ አንጀት በሁለት እንጨቶች ተወጥሮ ሁለቱ ቤተሰቦች እጅ ለእጅ ተያይዘው በቡርጃቡ መሪነት በአንጀቱ መካከል ያልፋሉ:: ከዚያም እንጨቱ ሲጣል አንጀቱ ይረግባል:: በወራጅ ውኃ ውስጥም ይጣላል ጥሉ ያረገበ፣ የልዩነት መንፈስ በውኃ ተጠራርጎ ይሂድ፣ በአንጀቱ ውስጥ ሾልከን ስላለፍን አለመግባባታችን በዚሁ ይለፍ ማለት እንደሆነ ተገንዝቤያለሁ:: በሁለተኛ ደረጃ በዚያው ወንዝ ዳር እያሉ የእህል ዓይነት ከቀረበ በኋላ በቡርጃብ ቀማሽነት የሁለቱ ቤተሰቦች እየተቀባበሉ የቀምሱታል:: አንዱ ለሌላው እየቀመሰ ይሰጣል:: ቀጥሎ ያለውም ለሌላው ቀምሶ ያስተላልፋል ይህም ከዚህ በኋላ አንድነታችን ተረጋግጧል:: በጋራ በሰላም መኖር እንችላለን ማለት እንደሆነ ተስተውሏል::

በርቱሳ ባህላዊ የግጭት አፈታት የሸኮ ብሔረሰቦች በሚኖሩበት አካባቢ ስለሚፈፀም ወደ ሌላ አካል ሳይሄዱ እዚያው ታርቀው መፍትሔ ያገኛሉ:: በመሆኑም የአካባቢው ህዝብ ፍትህ ፍለጋ ወደ ሩቅ ቦታ በመሄድ ለተለያዩ ወጪዎች አይጋለጥም:: በርቱሣ ባህላዊ የግጭት አፈታት በሸኮ ብሔረሰብ ዘንድ ከዘመናዊው የፍትህ ሥርዓት በተሻለ ሁኔታ በተግባር የፈፀማል:: ባህላዊ እርቅ ስርዓቱ ብዙ ጊዜ የሚሠራበት ነው:: ስለሆነም በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዳለው ተገንዝቤያለሁ:: ይሁን እንጂ የወረዳው የአስተዳደር አካላት ተገቢውን ትኩረት እንዳልሰጡት በጥናቱ ተመልክቷል::

የጎሣ መሪዎች፣ ቡርጃቦችና ታዋቂ የአገር ሽማግሌዎች ኑሮአቸው የተመሠረተው በግብርና ላይ ነው:: የግብርና ሥራ ደግሞ ጥንካሬን የሚጠይቅና እረፍት የለሽ ነው:: ዕለታዊ ክትትልን የፈልጋል:: እነዚህ አካላት እርቅ ለማስፈፀም ከቦታ ቦታ ይንቀሳቀሳሉ: ብዙውን ጊዜያቸውን በእርቅ ሥራ ላይ ያሳልፋሉ:: በዚህም ምክንያት የግብርናውን ሥራ ለመሥራት ይቸገራሉ:: ስለሆነም ኑሮአቸውን በአግባቡ ለመምራት ያዳግታቸዋል:: ይህን ችግር በምልከታ ወቅት በሸሻ በቀርጫና በምቼ የጎሣ መሪዎች ላይ አረጋግጫለሁ: ስለዚህ ባህላዊ ተቋሙን በኃላፊነት የሚያስተዳድሩት አካላት በተፈጠረባቸው የኢኮኖሚ ድቀት በስጋት ላይ ናቸው:: ሌሎችም

በተራቸው ተቀብለው ለትውልድ ለማስተላለፍ የማይችሉበት አጋጣሚ እየተፈጠረ ነው። ስለዚህ የባህላዊ ተቋሙ ህልውና አደጋ ላይ ነው። ባህላዊ እሴቶችም በዚያው ልክ እየጠፉ ይሄዳሉ።

## 5.2 የመፍትሔ አቅጣጫዎች (ይሁንታዎች)

ከላይ የቀረቡትን ሃሳቦች መነሻ በማድረግ ቀጥሎ የቀረቡት ጉዳዮች በተግባር ላይ ቢውሉ ቀጣይነት ያለው ሰላምና አስተማማኝ ልማት ሊመጣ ይችላል።

- በህዝቦች መካከል በተለያዩ ማህበራዊ ግንኙነቶች ላይ የሚፈጠሩ ግጭቶችን በባህላዊ መንገድ በማስወገድ የተረጋጋና ሰላማዊ ግንኙነቶችን ለመፍጠር የሚመለከታቸው አካላት ጥናት በማካሄድ ቀጣይነት ያለው የገንዘብ፣ የማቴሪያልና የሙያ ድጋፍ የጎሣ መሪዎች፣ ለቡርጃቦችና ለታዋቂ የአገር ሽማግሌዎች ቢሰጡ መልካም ነው።

- የሸኮ ቤተሰብ የውስጥ ችግሮቻቸውን የሚፈቱት በባህላዊ መንገድ እየተጠቀሙ ነው። እንደዚህ አይነት የራስን ችግር በራስ የመፍታትና ግጭትን የማስወገድ ስልት ቢጠናከር፣

- በቂም በቀል የሰው ህይወት እንዳይጠፋና ሁከትና ብጥብጥ እንዳይፈጠር በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው ልማድ ሰዎች እንዲግባቡና እንዲስማሙ የሚያደርግ ስልት በመሆኑ መጠናከር አለበት። በሰው ካሳ የሚደረገው እርቅ ሌላ ግድያን ሳያስከትል በጋብቻ በመተሳሰር የሚቋጭ ስለሆነ መዳበር አለበት

- ችግሮችን ባህላዊ በሆነ መንገድ መፍታት ጊዜን የሚቆጥብ፣ ወጪን የሚቀንስ፣ ከሙስናና ከአድሎ የፀዳ፣ በባህሉ ባለቤቶች ስነልቦናዊ እርካታን የሚያስገኝ በመሆኑ ትልቅ ጠቀሜታ አለው

- በወረዳው ውስጥ ያሉ የዘመናዊው ፍትህ አስፈፃሚ አካላት በተጠናከረ ሁኔታ ከጎሣ መሪዎችና ከቡርጃቦች ጋር የሁለትዮሽ የሥራ ግንኙነቶችን በመፍጠር ተግባራዊ ማድረግ ይገባቸዋል

- በመንግሥትና በፖሊሲ አውጭዎች ዘንድ ግጭትን በመፍታት ዘላቂ ሰላምን ለማስፈንና የተፋጠነ የልማት ባለቤት ለመሆን ባህላዊ የግጭት መፍቻ ሥርዓቶች ያሏቸው ብሔረሰቦችና ህዝቦች ማትኮር ተገቢ ይሆናል።

- በበርቴማ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዙሪያ ጥናታዊ ፊልም በማዘጋጀት ባህሉ አሁን ባለበት መልኩ ቀርጾ ለማስቀመጥና ለሌሎች ለማስተዋወቅ ጠቃሚነት አለው።

## ዋቢ መጻሕፍት ዝርዝር

Aklilu Yilma (1988). **The Phonology of Sheko** A.A.U. Thesis M.A

Bender, M.L.(1976). **Language in Ethiopia**. London, Oxford University Press,

Bliss, F (2002). **Managements of Conflicts on Communal Level**. GTZ GALPO. Project. Training Mannual. Addis Ababa.

Cervenka, Ldenek.(1977). **The unfinished Quest for Unity**. African and OAU London: Julian Friedaman Publisher Ltd.

Central Statistics Authority (CSA) 1994 Census Report.

Coser, Lewis A. (1970). **Continuities in the study of social conflict**, the free press, New York

Deng, Francis M. and Zartman, I. William (eds) (1991). **Conflict Resolution in Africa**. Washington DC: Brooking Institution.

Desalegn Chemeda Edossa, and Others. (2005). **Indigenous Systems of Conflict Resoluation in Oromia, Ethiopia.** (dchemeda @yahoo. com, st029119@ait.ac.th.

Deutsch, M.(1973). **The Resolution of Conflict**. New Haven: Yale University Press.

Fisher, Ronald J. (1982). **Social Psychology, An applied approach**, St. Martins's press, New York.

Goldstein, Kenneth (1964). **A Guide for Field Workers in Folklore**. The American Folklore Society: Folklore Associates. Inc.

Habtamu Wondimu, (1998) **Conflict Resolution in the Families of Nine Ethnic Groups in Ethiopia**. The Ethiopian Journal of Education. Vol. XVIII.

Ismail Essa Abrar (2001). "**Traditional conflict resolution mechanisms Their Relevance for conflict Resolution and peace boundiong in Somaliland**". In Emmanuel D. Mbennah.

Traditional Instituations for conflict resulution and promotion of peace in the Great lakes and Horn of Africa Regions Univeristy of Bujumbura. Brundi.

Katz, and lawyer (1985). **Communication and Conflict Resolution Skills**. Dubugue, lowa: Kendall Hunt.

Kreidler, W. (1984). **Creative Conflict Resolution**: More Than 200 Activities for Keeping Peace in the Classroom. Glenview, IL: Scott, Foresman and Company.

Martin, Guy.(1998) **Conflict resolution in Africa**, In: Conflict Resolution, Early Warning and Information Exchange, Controlling Small Arms Proliferation and Reversing Cultures of violence in Africa and the Indian Ocean, monograph No 30 Section three.

Orjiako Desmond (2005) **The Africa Union: Our common Home**. (un published) Boston North Eastern Univeristy press.

Pelton, H. Leroy (1974). **The Psychology of Non Violence**. New York. Pergamon Press Inc.

Riches, David (1986).**The Anthropology of Violence**, Oxford, UK.

Seyoum Gebre Selassie and Yacob Arsano,(2003). **Resource Scarcity and Conflict management in the Horn of Africa:** The Case of North Shoa and the Adjacent lowlands, Ethiopia. Institute For African Alternatives. Addis Ababa University. Addis Ababa.

Simma, Bruno(ed)(1995) **The charter of the united Nations: a Commentary.** New York Oxford University Press.

Teshome Haile (1998) **Population pressure, Agricultural Holding and production in yeki woreda.** B.A thesis E.C.S.C.

Toelkon, Barre (1996). **The Dynamics of Folklore**. Utah State University Press, Longa Utah.

Utne, B brock (2000) "**Indigenous Conflict Resolution in Africa**". University of Oslo, Institution for Educational Research.

Yacob Arsano(2001). **Traditional Capacity for Conflict management: The Case of Boran of Southern Ethiopia,**: "Traditional institutions for conflict Resolution and Promotion of peace in the great Lakes and the horn of Africa Regions" Bujumbura, Burundi, 5-8.

Yohannis Birhanu (1998). "**Conflict Resolution among the People of Chihera**". MA Thesis. A.A.U.

መስጌታ ነጋሳ (1997)፣ «በአድአ ሊበን ወረዳ የኦሮሞ ሲሪ ጨፌ ከግጭት አንጻር»፤ የኢም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ትምህርት ክፍል።

ሰለሞን ሳህሉ(1998)፤ «ባህላዊ የግጭት አፈታት በሲቡ ሲሬ ኦሮሞዎች»፤ የኢም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ትምህርት ክፍል።

ነጋት መኮንን(1998)፣ «አቢጋር ባህላዊ የግጭት አፈታት በተሁለደሬ» የኢም ኤ ዲግሪ መሟያ ጽሑፍ፤ አ.አ.ዩ፣ የኢ.ት.ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፉ ትምህርት ክፍል።

አምሳሉ አክሊሉ (1976)፤ «አጭር የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ታሪክ»፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

ኢፍሬም አሰፋ (1992) አዲሱ የአማርኛ መዝገበ ቃላት አ.አ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል (1993)፤ አማርኛ መዝገበ ቃላት፤ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ደላጋ ተፈራ (1998)፤ «የሽምግልናና ዕርቅ ሥርዓት በወላይታ»፤ የኢም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፤አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል።

ደስታ ተክለ ወልድ (1962)፤ ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት፤ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት

ፈቃደ አዘዘ (1991)፤የስነ ቃል መምሪያ፤አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የመፃህፍት ማዕከል።

------------ (1949)፤ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ፤ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

------------(1952)፤ ፍትሐብሔር ህግ፤ አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

------------(1980)፤ የኢትዮጵያ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት፣አዲስ አበባ

------------ (1987)፤ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት፤ አዲስ አበባ።

------------(1987)፤ ነጋሪት ጋዜጣ፤ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ሪፐብሊክ መንግሥት፣ አዲስ አበባ።

# አባሪ አንድ

## የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር

| ተ.ቁ | የመረጃ አቀባዩ ስም | ፆታ | ዕድሜ | የመረጃ አቀባዮች ሥራና በማህበር ውስጥ ያላቸው እርከን/ደረጃ/ | ቀበሌ | ቃለ-መጠይቅ የቀረበበት ቦታ | መረጃው የተሰበሰበበት ወርና ቀን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | [illegible] | ወ | 80 | ኢያኡ/የጎግ መሪ/ | ሾሻ | መኖሪያ ቤት | ተህሳስ 1999 |
| 2 | [illegible] | » | 47 | የመንግሥት ሠራተኛ | ቱፒ | ቢሮ | ተህሳስ 1999 |
| 3 | [illegible] | » | 67 | ኢያኡ/የጎግ መሪ/ | ሞቼ | መኖሪያ ቤት | ተህሳስ 1999 |
| 4 | [illegible] | » | 92 | ኢያኡ/የጎግ መሪ/ | ቆርጫ | መኖሪያ ቤት | ተህሳስ 1999 |
| 5 | [illegible] | » | 50 | የመንግሥት ሠራተኛ | ዝንኪ | ቡና ቤት | ጥር 1999 |
| 6 | [illegible] | » | 52 | ገበሬ/ ስለሺ፡ ባህል ዕውቀት ያለው/ | ሾሻ | መጠጥ ቤት | ተህሳስ 1999 |
| 7 | [illegible] | » | 40 | የመንግሥት ሠራተኛ | ቱፒ | በመዝናኛ ቦታ | ተህሳስ 1999 |
| 8 | [illegible] | » | 36 | የመንግሥት ሠራተኛ | ዣና | ቢሮ | ተህሳስ 1999 |
| 9 | [illegible] | » | 75 | ገበሬ/ሀገር ሽማግሌ/ | ዳረሙ | መጠጥ ቤት | ሚያዚያ 1999 |
| 10 | [illegible] | » | 53 | ገበሬ/ የቀበሌ አመራርና ሀገር ሽማግሌ/ | ሾሻ | ቤተክርስቲያን | የካቲት 1999 |
| 11 | [illegible] | » | 35 | የቀበሌ አመራር/ገበሬ/ | ሾሻ | በቀበሌው ቢሮ | ህዳር 1999 |
| 12 | [illegible] | » | 45 | ገበሬ | ቆርጫ | አባሸዋ ቆርጫ ቤት | ጥር 1999 |
| 13 | [illegible] | » | 42 | ገበሬ | 08 ቀበሌ | በመኖሪያ ቤት | የካቲት 1999 |
| 14 | [illegible] | » | 49 | ገበሬ በርጃብ/አስታራቂ/ | ምቼ | በመኖሪያ ቤት | ታህሳስ 1999 |
| 15 | [illegible] | » | 37 | መምህር | ኩኪ | ቡና ቤት | ሚያዚያ 1999 |
| 16 | [illegible] | » | 52 | ገበሬ/ሀገር ሽማግሌ/ | ሾሻ | በቡና ውስጥ | የካቲት 1999 |
| 17 | [illegible] | » | 54 | ገበሬ | ሾሻ | ወንዝ ዳር | ጥር 1999 |
| 18 | [illegible] | » | 52 | ገበሬ/ሀገር ሽማግሌ/ | ሾሻ | ቡና ቤት | ታህሳስ 1999 |
| 19 | [illegible] | » | 50 | ገበሬ | ቆርጫ | የቀበሌ ጽ/ቤት | ጥር 1999 |
| 20 | [illegible] | » | 38 | ገበሬ | ቆርጫ | መኖሪያ ቤት | የካቲት 1999 |
| 21 | [illegible] | » | 48 | ገበሬ | ዣና | ሾሻ ቀበሌ | ታህሳስ 1999 |
| 22 | [illegible] | » | 75 | ኢያኡ/የጎግ መሪ/ | በጨኪ | በገበያ ቦታ | ተህሳስ 1999 |
| 23 | [illegible] | » | 45 | በርጃብ /አስታራቂ/ | ሾሻ | መጠጥ ቤት | ተህሳስ 1999 |
| 24 | [illegible] | » | 60 | ሀገር ሽማግሌ | ሞቼ | በመኖሪያ ቤት | ተህሳስ 1999 |
| 25 | [illegible] | » | 37 | የመንግሥት ሠራደተኛ | ቱፒ | መኖሪያ ቤት | ጥር 1999 |
| 26 | [illegible] | » | 30 | የግብርና ባለሙያ | ዣና | በቡና ውስጥ | ጥር 1999 |
| 27 | [illegible] | » | 48 | መምህር | ሾሻ | ት/ቤት | ሚያዚያ 1999 |
| 28 | [illegible] | » | 50 | ገበሬ | ሾሻ | መኖሪያ ቤት | ተህሳስ 1999 |
| 29 | [illegible] | » | 48 | ገበሬ/ሀገር ሽማግሌ/ | ሾሻ | ቡና ውስጥ | ተህሳስ 1999 |
| 30 | [illegible] | » | 38 | ገበሬ | ሾሻ | ወንዝ ዳር | ጥር 1999 |


# አባሪ ሁለት

የመረጃ አቀባዮችንና በዕርቅ ሥርዓት የተሳተፉ ሰዎችን

የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ




ዋና የመረጃ አቀባይ አቶ አርማ ቤት



የጉዳይ ቤተሰብ ወደ እርቅ ቦታ ሲሄዱ



እርቅ አርጎት በኋላ በርቹበ መስዕዋውን መርቆ በባሉ
መሠረት ሲያበሩውን



አጥኚው ከመረጃ አቀባዮች መረጃ ሲሰበስብ



ፀርጃብ የገዳይና የሟች ቤተሰቦችን ወደ ዕርቅ ቦታ ሲያመጣ



ፀርጃቦና የአገር ሽማግሌ እርቅ እንዲፈፀም ሲያግቡ



# አባሪ ሦስት

## በሸኮ ብሔረሰብ በቦራ/እርግማን/ ምክንያት የታዩ ጥፋቶች/የደረሱ እልቂቶች/

ጋርኩሳ የተባለ ሰው በቡቶ አካባቢ/በአሁኑ 08 የሚባል ቀበሌ/ ይኖር ነበር። ግለሰቡ በአካባቢው ያሉትን ነዋሪዎች፣ እንስሳት፣ አዝዕርት፣አትክልትና ሌሎችንም ንብረቶች እየሰረቀ አስቸገረ። ከጥፋቱ እንዲመለስ የአካባቢው ሽማግሌዎች፣ የጎሣ መሪዎችና የራሱ የቅርብ ዘመዶች መከሩት። አስመከሩት። አቶ ጋርኩሳ ግን በሌብነቱ በመቀጠል የሠው በግና ፍየል መስረቅ፣ በህይወት ያለን በግ ላቱን ብቻ እየቆረጠ መብላት፣ የሠውን ቀፎ እያደባ መዝረፍ በሬ፣ በግና ፍየል በጫካ ውስጥ እያረደ መብላት፣ በሰው ቤት ውስጥ እየገባ ንብረት መዝረፍና አትክልትና አዝዕርት መስረቁን ተያያዘው።

የጎሣ መሪዎች ቡርጃብና የአካባቢ ሽማግሌዎች በጎሣ መሪው በአቶ ዱሻ ደጅ ተሰብስበው በህዝብ ፊት ለመምከርና ለማስጠንቀቅ አስጠሩት። ነገር ግን አሻፈረኝ ብሎ በስብሰባው ሳይመጣ ቀረ። የጎሣ መሪዎችን የናቀ፣ሽማግሌዎችን ያዋረደ፣ የህዝቡን ባህልና ወግ ያንቋሸሸ በመሆኑ ሁሉንም የአካባቢውን ነዋሪ አስቆጣ። ቤተሰቦቹና የቅርብ ዘመዶቹ እንዲመክሩት የተሰጠው ትዕዛዝ ተግባራዊ አልሆነም፣ የጎሣ መሪው በጠራው ስብሰባ ላይ እንዲገኝ ለራሱም ሆነ ለዘመዶቹ ተነገሮ ሊመጣ አልቻለም። ስለዚህ ቦራ እንዲከናወን ተወስኖ በአቶ ዱሻ ደጅ በ 1964 ዓ.ም እርግማን ተካሄደ።

እርግማኑ በተካሄደበት ወቅት ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ጋርኩሳ የሰው ቀፎ ሊሰርቅ ዛፍ ሲወጣ ወድቆ እዚያው ሞተ። ሚስቱም እብራው ስለነበረች ለአካባቢው ሽማግሌዎች መሞቱን ነግራ ሬሣውን እንዲያነሱ ስትጠይቅ ይኸማ እኛ የምንፈልገው ነው ምልክት /ሞጣ/ አግኝተናል። እውነቱ ተገለጠ በማለት ደስታቸውን ገለፁላት። በዚያው ዘመን ከጋርኩሳ ቀጥሎ ልጆቹ ሞቱ። ከልጆቹም ቀጥላ ሚስቱም ሞተች። ከእርግማኑ በኋላ የዚህ ሰው ዘር አለቀ። የአካባቢው ሕዝብም እግዚአብሔር መሰከረ። እውነቱን ገለጠ። በማለት ባህላዊ ህጋቸውን የጣሰውን ሰው ዘርማንዘር ማጥፋት እንደሚቻል ትምህርት ሰጠ ተብሎ ማህበረሰቡ እንደተደሰተ እኛም ከአንካቢው ነዋሪዎች መካከል ነበርን በማለት የነገሩኝ ሣያ ቡሳና አለሙ ጣማ ናቸው።

ሌላው በሸኮ ብሔረሰብ እርግማን ተከናውኖ አጥፊው የሞተበት በ1950 ዓ.ም የአቶ ባንቦይ ቡሳ የልጅ ልጅ ኒያኩ ቦርሳ ጎረምሳ ልጅ ነበር ይህ ልጅ ድብድብ የሚያበዛ፣ ሰው የተናገረውን የማይሰማ፣ የአካባቢውን ነዋሪዎች እየተደባደበ የሚያስቸግር ነበር። ይህን መጥፎ ተግባሩን እንዲተው አያቱ ብዙ ጊዜ መከሩት በሰውም አስመከሩት። ኒያኩ ግን ከሰው ጋራ መጣላቱን አላቆም አለ። እንዲውም በቀን ከሦስት እራት ሰው ጋር መጣላትና መደባደብ ጀመረ። አያቱና

ቤተሰቦቹ ከአካባቢው ሰው ጋር ተስማምተው እንዳይኖሩ እንቅፋት ሆነባቸው:: ከማህበራዊ ኑሮ እየተገለሉ መጡ:: በተለያዩ ሰዎች በተለያየ ጊዜ እንዲመከር ቢደረግ ከዕኩይ ተግባሩ ሊመለስ አልቻለም::

አያቱ የአካባቢዋን ሽማግሌዎችና ነዋሪዎች ሰብስበው እኔና ቤተሰቦቼ ከእናንተ ተነጥለን መኖር አንፈልግም:: እኛና እናንተን ሊያቆራርጥ የተነሳን ልጅ ኒያኩን በጋራ ሆነን እንርገም ብለው ጠየቁ:: ልጁም በአካባቢወ ህዝብ ዘንድ ብዙ አስነዋሪ ስራ መስራቱን ሁሉም የሚያውቁ ስለሆነ እርግማን እንዲካሄድ ተወስኖ በጋራ ሆነው ረገሙት:: ልጁም ሶስት ወር እንኳን ሳይቆይ ሞተ:: በማለት የነገሩኝ አቶ ሳያ ጉግሳ ናቸው::

## በጋሞ ምክንያት የተከሰተ የዝናብ መጥፋትና የተወሰደ ባህላዊ እርምጃ

የሾሻ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት አቶ ሽሎ ፈጂ እንደነገሩኝ በ 1963 ዓ.ም በሾሻ ቀበሌ ልዩ ስሙ ሻቹ በተባለ መንደር አንድ ህፃን የታችኛው ጥረስ ሳይበቅል የላይኛው ጥርስ ቀድሞ በቀለ በዚህም ምክንያት ዝናብ አቆመ:: ከፍተኛ ድረትም ተከሰተ:: የአካባቢው ነዋሪ በተከሰተው የዝናብ እጥረት ተጨነቀ:: ተጠበበ:: በዚያን ወቅት የሁሉም ሰው ሃሳብ ችግሩ ምን ይሆን እያለ ማሰላሰል ነበር:: ምክንያቱም የዚህ ዓይነት የዝናብ እጥረት በአካባቢው አጋጥሞ አያውቅም ስለዚህ የሁሉንም ሰው ትኩረት ሳበ:: የጋራ መወያያ ርዕስም ሆነ::

ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ ከሻቹ አካባቢ ነዋሪዎች አንዱ በዚያ አካባቢ ጋሞ/የታችኛው ጥርስ ሳያበቅል የላይኛው ጥርሱ የበቀለ ልጅ/ መኖሩን ተናገረ:: ይህ ዜና ከሁሉም ሰው ጆሮ ሲደርስ አንድ ውሳኔ ላይ ተደረሰ:: ሁሉም ጡሩንባ እየነፋ በነቂስ ወጥቶ ይህን ህፃን ወንዝ አሻግሮ ለመጣል ተስማማ:: ከአካባቢው ነዋሪ አንድም ሰው ሳይቀር በመውጣት ወደ ተባለው ህፃን ልጅ ቤት ሄደው ህፃኑን በመያዝ ተሰልፈው የበቆን ወንዝ አሻግረው ጣሉት:: ከዚያ በኋላ ህዝቡ ወደ ቤቱ ሲመለስ በመንገድ ላይ እያለ ዝናብ ጣለ:: በማለት ገልፀውልኛል::

# አባሪ አራት

## የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር

1. አቶ ፍትሻ ሾሻ

| | |
|---|---|
| ሥራ | ገበሬ |
| ማዕረግ | የጎሣ መሪ |
| ዕድሜ | 80 |
| አድራሻ | የኪ. ወረዳ፣ ሾሻ ቀበሌ ፣ ጉደር አካባቢ. |

ፍትሻ ሾሻ የጎሣ መሪ ሲሆኑ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ የተከበሩ ናቸው። የሽኮ ቤሔረሰብ ባህላዊ መማሪያዎች በፍትሻ ሾሻ ቤት ይገኛሉ። በሚኖሩበት ወረዳና ቀበሌ የነፍስ ገድያ ግጭት ሲከሰት እርቅ እንዲፈፀም ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ። በመስክ ሥራዬ የቤሔረሰቡን አመጣጥ፣ የበርቱማን ክዋኔ በቃለ መጠይቅ አማካይነት ገልፀውልኛል።

2. አባ ሾዋ ቆርጫ

| | |
|---|---|
| ሥራ | ገበሬ |
| ማዕረግ | የጎ መሪ፣ ቃልቻ |
| ዕድሜ | 92 |
| አድራሻ | የኪ. ወረዳ፣ቆርጫ/በቆ/ቀበሌ. |

የአካባቢው ማህበረሰብ ያከብራቸዋል። የከረሩ ጥሎች ሲፈጠሩ እርቅ እንዲወርድ በማድረግ ይታወቃሉ። በስውር የሚፈፀሙ ወንጀሎች ተሰውረው እንዳይቀሩ ወንጀሎችን ያጋልጣሉ። በአካባቢው ድርቅ፣ ረሃብ የውኃ ማጥለቅለቅ፣ አውሎ ንፋስና ሌሎች ጥፋትን የሚያስከትሉ ሁኔታዎች እንዳይከሰቱ ፀሎት በማድረግ ህዝቡን ከጥፋትና እልቂት ይጠብቃሉ። በቤሔረሰቡ ስርቆት፣ክህደትና ዝሙት እንዳይፈፀም ህዝቡን ያስጠነቅቃሉ። ባህላዊ ደንቡ እንዲከበር ጥረት ያደርጋሉ።

3. ኡርማ ዚቲ

| | |
|---|---|
| ሥራ | ገበሬ |
| ዕድሜ | 52 |
| አድራሻ | የኪ. ወረዳ ሾሻ ቀበሌ. |

ባህላዊ እረት ምን እንደሚመስል ስፉ ተሳትፎ ያደረገ ነው፡፡ በተለያዩ ጊዜያት ብሔረሰቡን በመወከል ተሳትፏል፡፡ ስለብሔረሰቡ መረጃ ለሚፈልግ ግልፅ የሆነ መረጃ የመስተት ብቃት አለው፡፡ ባህሉን ጠንቅቆ ያውቀዋል፡፡ በሸኮ ብሔረሰብ ለግጭት መቀስቀስ ምክንያት የሚሆኑትን አብራርቷል፡፡ በጎሣዎች መካከል የሚፈጠሩትን ግጭች በጎሣ መሪዎች አማካይነት ማቃለል እንደሚቻል የገለፀው አርማ ዜቲ ነው፡፡

4. ሸሙፊጆ

ሥራ ገበሬ

ዕድሜ 52

አድራሻ የኪ. ወረዳ ሸሻ ቀበሌ

የበርቱ ሥርዓት ክዋኔ በሚገባ የሚያውቅ፣ይህን ሥርዓት ከጥንት ጀምሮ እንደሚያውቅና ከቤተሰብ እንደወረሰው አባትና አያቶች በበርቱማ ሥርዓት ተሳታፊዎች እንደነበሩ የተረከልኝ፣ የሸኮ ብሔረሰብን የዘር ግንድ የገለፀልኝ፣ የጠለፋ ግጭት እርቅን ያብራራልኝ ነው፡፡

5. ሻሻ ወሽከሬ

ሥራ የመንግሥት ሠራተኛ

ዕድሜ 50

አድራሻ የኪ. ወረዳ ዝንኪ

የሸኮ ብሔረሰብን ባህል ጠንቅቆ ያውቀዋል፡፡ ስለ ብሔረሰቡ አመጣጥ፣ የዘር ግንድና የበርቱማ ሥርዓት ክዋኔን ጽሑፍ ያዘጋጀ፡፡ በትንበር ተፈጥሮአዊ መቼት ከፍተኛ ተሳትፎ ያደረገ፡፡ ስለ ጋሞ፣አንቻብ፣ሸኮንና ሸተማ፣ ሁኔታ መረጃ የሰጠኝ፡፡ በአጠቃላይ ለጥናቱ መረጃ በመስጠት ከፍተኛ እገዛ ያደረገና ግልፅ መረጃ የሰጠኝ ነው፡፡

# ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ፊርማዬን ያስቀመጥኩኝ የድህረ ምረቃ ተማሪ ይህ ጥናት የራሴ ስራና በጥናቱም ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎች ምንጭ በትክክል የጠቀስኩ መሆኑን አረጋግጣለሁ።

ስም መንግስቱ ፍስሐ አበበ

ፊርማ ፡-___________________________

አድራሻ፡- አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ሥነ-ትምህርት ኮሌጅ

የህብረ ባህልና ልሳነ ብዙ ትምህርት

የማስረከቢያ ቀን ሐምሌ 9/1999 ዓ.ም።

ይህ ጥናት በእኔ አማካሪነት ለፈተና ቦርድ እንዲቀርብ ተደርጓል።

ስም ___________________________

ፊርማ ___________________________

የማስረከቢያ ቀን ___________________